# ነፃነት

ፍኖተ

ፍኖተ ነፃነት ማክሰኛ ግንቦት 14 ቀን 2004 ዓ.ም.

ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 43 | ዋጋው፡- 6 ብር

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!




## አቶ መለስ በገጠማቸው ተቃውሞ አንገታቸውን ደፉ

13



## ኮንግረስማን ክሪስ ስሚዝ አቶ መለስ በቡድን 8 ጉባኤ መገኘታቸውን አወገዙ

11

## አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር ህክምና ማግኘት አለመቻላቸው ተገለፀ

11

## አጣብቂኝ ውስጥ የገባው መምህራን ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ ሊያደርግ ነው

13

## የግንቦት 20 ፍሬዎች

## መለስ ዜናዊና ወ/ተንሳይ

2

## አዲስ አበባችን እንዴት ነሽ? ኢህአዴግ የት ያደርስሽ ይሆን?

6

ግርማ ሰይፉ ማሩ

## ከስካይ ባስ ሰለባዎች ጀርባ ምን አለ?

8

## የግሉን ዘርፍ እያሸመደመዱ "ነፃ ገበያ አለ" ማለት ነጭ ውሸት

4

## «ነፃነት በሌለበት አገር ኪነጥበብ ህይወት አይኖረውም» ታዳሚው

« ኪነጥበብ መለኪያው እውነትና ውበት ነው» አያልነህ ሙላቱ

« ኪነጥበብ እንዳይጠወልግ መጮህ ያስፈልጋል» በቀለ መኮንን

« ኪነጥነበብ ትንቢት ተናጋሪ ነው» አበረ አዳሙ

« መጥፎ ሰውና ጥበብ የተገናኙ እለት ጥበብ ይሞታል» እሸቱ ጥሩነህ

እሁድ ግንቦት 12 ቀን 2004 ዓ.ም ብሔራዊ ቲያትር አዳራሽ «ኪነ-ጥበብ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው ሚና» በሚል ርዕስ ደማቅ ውይይት ተከናውኗል፡፡ ውይይቱ የተካሄደው አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ባዘጋጀው መድረክ ነው፡፡ በዚህ አንድነት ፓርቲ ባዘጋጀው ውይይት ላይ ተጋብዘው የሞያ ልምዳቸውን ያካፈሉት ፀሐፊ ተውኔት ገጣሚና ደራሲ አያልነህ ሙላቱ፣ ደራሲ አበረ አዳሙ፣ ቀራጺ በቀለ መኮንንና ሠዓሊ እሸቱ ጥሩነህ ናቸው፡፡ መድረኩን የመሩት የአንድነት ፓርቲ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊው ዶ/ር ኃይሉ አርአያ እንዳሉት «አንድነት የውይይቱን መድረኩ ከማመቻቸት ውጪ ሚና የለውም፡፡ ውይይቱ በነፃነት ስለ ኪነጥበብ የሚመከርበት ነው፡፡ መድረኩ የብሶት መግለጫ እንዳይሆን እንፈልጋለን፡፡ በዚህ መድረክ ስለ ኪነጥበብ ብቻ እንወያይ» በማለት ማሳሰቢያ ሰጥተው፤ የውይይቱን መነሻ ሃሳብ ያቀርባሉ የተባሉትን ተጋባዥ እንግዶችን ጋብዘውና አስተዋውቀው መድረኩን ለተጋባ የኪነጥበብ ባለሞያዎች ክፍት አድርገዋል፡፡

በእንግድነት የተጋበዙት የኪነጥበብ ባለሙያዎች ሁሉም በዚህ ዝግጅት ላይ የመጡት ማንንም ወክለው ሳይሆን ራሳቸውን ወክለው እደሆነ፤ የማንም ፖለቲካ ፓርቲ

ወደ ገፅ 11 ይዞራል....

ዳሰሳ

**ኢህአዴግ ደርግን ከስልጣን ያስወገደበት 21ኛ አመት ሰኞ ግንቦት 20 ቀን 2004ዓ.ም ይከበራል፡፡ በነዚህ ረዥም አመታት የኢህአዴግን የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ይዘዉ የቆዩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ብቸኛዉ ሰዉ ሆነዉ የወጡበት ነዉ የሚለዉ ሰለሞን ስዩም ይህ እንደሀገርም እንደታጋዮችም ክሳራ ነዉ ይላል፡፡**

# የግንቦት 20 ፍሬዎች፤ መለስ ዜናዊና ወ/ተንሳይ

ወ/ተንሳይ ገ/ዚጊ ከስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ እስከ ቅድስት ማርያም ቤ/ተክርስቲያን መካከል ባለው መንገድ ላይ አይጠፉም፡፡ ወ/ተንሳይን የሚያውቁ ሁሉ አንድ ልዩ መለያውን ለመለየት ጊዜ አይወስድበትም፡፡ የሚራመደው በሀሳቦች ሰራዊት መካከል ሆኖ አቀርቅሮ ነው፡፡ በ1982 ዓ.ም የመንግሥት ወታደሮች ከወቅቱ አማጺ የህወሓት ቡድን ጋር ባደረጉት የደብረ ታቦር ውጊያ ለህወሓት መሞትን ክብሩ ያደረገው ወ/ተንሳይ ባንድ አውደ ውጊያ ቀኝ እጁን ሙሉ በሙሉ ያጣ ሲሆን ግራ እጁ ትከሻ አካባቢ በደረሰበት የጥይት ጉዳይ ከመወዛወዝ የዘለለ ፋይዳ የለውም፡፡

በ2002 ዓ.ም በነበረው የቅድመ ምርጫ የሕዝብ ስብሰባዎች መድረክ በሚጠራቸው ላይ እየተገኘ ይጠይቃል፡፡ የወ/ተንሳይን ጥያቄ እንግዳ የሚያደርገው ጥያቄዎቹ የሚያጠነጥኑት በወቅቱ የምርጫ ጉዳይ አለመሆናቸው ነው፡፡ ወ/ተንሳይ በወቅቱ ከደርግ ጋር በተደረገው ጦርነት የተከፈለው መስዋዕትነት እኛን ጥሎናል፤ ለተባለለት አላማም አልዋለም የሚል ነው፡፡ በተለይ አቶ ስዬ አብርሃ በተገኙበት ስብሰባ “የሞትነው፣ አካላችን የጎደለው ስለምንድነው” የሚል ጥያቄ ይቀናው ነበር፡፡

በግንቦት 2004 ዓ.ም ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በቡድን 8 ሀገራት ስብሰባ ላይ ለመታደም ወደ አሜሪካ ካምፕ ዴቭድ አቀኑ፡፡ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም በሬገን የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ለተገኙ ታዳሚዎች የሀገራቸውን ልምድ ለማካፈል ዛሬም መድረክ ላይ ነበሩ፡፡ የአለም አቀፍ ጋዜጠኞች ማህበር አባል የሆነ ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ በሽብርተኝነት የተከሰሰው ጋዜጠኛ አበበ ገላው በስብሰባው እንዲታደም ተጋብዞ ነበር፡፡ አቶ መለስ ንግግር እያደረጉ እያለ «መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው፤ መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው፤ መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው፤ እስክንድር ነጋ ይፈታ . . . የሚል ከፍተኛ ድምጽ አሰማ፡፡ አቶ መለስ የአበበ ገላውን መፈክር ለመስማት የቻሉ አይመስሉም ነበር፡፡ ከፍተኛ ድንጋጤ ነበረባቸዉ፡፡ከአዳራሹ ውጭ የጠበቃቸው ደግሞ ከዚህም ይብስ ነበር፡፡»

## ለውጡ ለምን አስፈለገ?

የአጼ ኃ/ስላሴ ድህረ ጣሊያን አገዛዝ በዋነኘነት ትኩረት ያደረገው የዙፋናቸው መጠናከር ላይ መሆኑ ለ1966ቱ ዓ.ም አብዮት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደነበረው የታሪክ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ « አገዛዝ መጠናከር» ባሉት ርዕሳቸው ድህረ ጣሊያንን ተከትሎ በመጣው የንጉሱ ግርማ ሞገስ የሀገር ዜጋውም ከውጭ ሀገር የመጡ እንግዶችም መታዘባቸውን ጽፈዋል፡፡ ይህንን ይዘት በጅጉ ገርስሷል የሚባለው ወንድማማቾቹ የመሩት መፈንቅለ መንግሥት እንደነበር ፕ/ር ባህሩ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የተቀጣጠለው የህዝብ ብሶት በ1996 ዓ.ም ቢፈነዳም አምባገነኑን ወታደራዊ መንግሥት ከመውለድ አልዳነም፡፡ ሲቃወሙ የነበሩት የፊውዳል ሥርዓት በአመባገነናዊ ወታደራዊ መንግሥት መተካቱ ያልጣማቸው የለውጥ ቀስቃሾቹ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ምሩቃን መፍትሔውን በሁለት መልኩ አይተውት ነበር፡፡ የመጀሪያዎቹ የከተማ ውስጥ ትግል እንዲሁም ከደርግ ጋር በስምምነት በመስራት እያደር ማጥለቅለቅ የሚል ነበር፡፡

ሁለተኞቹና የግንቦት 20 ድልን ያስገኙት ደግሞ የትጥቅ ትግልን በብሔር መሠረት ላይ በማድረግ የሚፈታ አድርገው ወሰዱ፡፡ ተረት ቀመስ የሚመስለው የህወሓት የአጀማመር ታሪክ ይህንን «የማይሆን የሚመስለዉን ወደ መሆን» የመቀየር ያክል ያሳካ ነው፡፡ የጫካ ቡድንነቱ የማፊያ/ሽፍታ ባህሪ እንዲያንፀባርቅ ቢያስገድደውም ህወሓት የትግራይን ህዝብ ከጎኑ ለማሰለፍ ተሳክቶለታል፡፡



የህወሓት/ኢህአዴግ ድል ነው የሚባለው ግንቦት ሃያ መለስ ዜናዊን ብቻ ወደ ማፍራት የሄደበት አካሄድ የረዥም ዘመናት የተጠራቀመ ሂደት መሆኑን ፕ/ር ተኮላ ሀጎስ «Democratization Ethiopia (1991-1994) A personal view» በተባለ ጥናታቸው ይገልፃሉ፡፡ ፕ/ሩ ህወሓት በ1971 ዓ.ም ኮንግረስ ከማድረጉ በፊት ህወሓት ሁለት እርከን አመራር የነበረው መሆኑን ያወሳሉ፡፡ ግርማይ ገብሩ የተስፋይ አጽብሃን « Die positiven und Negativen Aspekete Der TPLF» የተባለ በጀርመንኛ የተሰራ ጥናት በመጥቀስ የመጀመሪያው ረድፍ ውስጥ አባይ ፀሐዬ፣ ስብሃት ነጋ፣ ግደይ ዘርዓጽዮን፣ አረጋዊ በርሔ እና ስዩም መስፍን መሆናቸውን ይዘረዝራሉ፡፡ በሁለተኛው ረድፍ ያሉት አመራሮች ደግሞ መለስ ዜናዊ፣ ስዬ አብርሃ፣ እና አታክልቲ ቀፀላ እንደነበሩ ግርማይ ይገልፃሉ፡፡ ሁለተኛው ረድፍ ላይ ያሉት ባለተስፋና ከዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ትግል የገቡ ነበሩ፡፡

በ1971 ዓ.ም በተካሄደው የህወሓት የመጀመሪያው ኮንግረስ መለስ ዜናዊ ወደ መጀመሪያው ረድፍ መሪነት ከመምጣታቸውም በላይ በስብሰባው የተላለፈው የሶሻሊስት ፓርቲ ምስረታ ውሳኔ ማእከላዊ ኮሚቴው የመምራት ኃላፊነቱን ለአቶ መለስ መስጠቱ ይነገራል፡፡ እንደ ግርማይ ትንተና ለዚህ ኃላፊነት ሲባል አቶ መለስ ዜናዊ በግንባር አውደ ውጊያዎች ላይ ከመታየት ይልቅ ወደ ማንበቡ አደሉ፡፡

ሌላው የአቶ መለስ የመግነናቸውን አጋጣሚ ያመቻቸው ከዚህ የመጀመሪያው ኮንግረስ ጀምሮ ህወሓት ውስጥ ፖለቲካ የሁሉም ነገር የበላይ መሆኑ ታወቀ፡፡ ለሶሻሊስት ፓርቲው ምስረታ ብዙ ማንበብ የተያያዙት አቶ መለስ በተፈጥሮ ካላቸው ነገሮችን አፍታቶ የመናገርና የመፃፍ ችሎታ ላይ የንባብ ክህሎቱ አግዟቸዋል፡፡

አቶ ግርማይ ገብሩ አራቱ የፖለቲካ ቢሮ አባላት ቀስ በቀስ በተለያዩ ዘዴዎች በአቶ ዓባይ ፀሐዬ ስር እንደገቡ ያወሳሉ፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ በወቅቱ የአቶ አባይ ፀሐዬ ምክትል በመሆናቸው ሁለተኛው ሰው ሆኑ ማለት ነው፡፡ ፖለቲካ በሽምቅ ተዋጊ ቡድን ውስጥ የበላይ ሲሆን የህወሓትን ጨምሮ ጥቂት ምሳሌ ነው ያለው፡፡

በ1997 ዓ.ም አቶ መለስ በ1971 ዓ.ም በኃላፊነት የወሰዱትን ማሌሊት ፓርቲ ምስረታን የሚያበስሩበት ነበር፡፡ በወቅቱ በሀሳቡ ላይ ከግዳይ ዘርየፅዮን መስማማት ያልቻሉት አቶ መለስ እና አቶ ግደይ ዘርዓፅዮን ክርክር አድርገው ነበር፡፡ በወቅቱ አቶ መለስ ያስተማሯቸውና የክርክሩ ተሳታፊ የነበሩት ካድሬዎች በከፍተኛ ሁኔታ ሲደግፏቸውና ሲሲቁላቸው እንደነበር አቶ ግረማይ ገብሩ «የመለስ መንገድ» በሚል በሰሩት መጣጥፍ ላይ ጠቅሰዋል፡፡፡፡ ለአቶ መለስ የፖለቲካ እውቀት ተቀናቃኝ የነበሩ የድርጅቱ አመራሮች በዚሁ ሁኔታ እየተለዩ አቶ መለስ እየገነኑ መምጣታቸው ይነገራል፡፡ አንዳንድ የተለየ ሀሳብ ያላቸው “ኢምፔሪያሊስትም” እና “ፕራግማቲክ” የሚሉ ቅጥያዎች እየተለጠፈባቸው “ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ያልገባቸው” እየተባሉ ከድርጅቱ ይወገዱ ነበር፡፡

## የመንግሥት ስልጣን

የኢትዮጵያ ህዝብ ለመሪዎች ስልጣን ያለውን የመቀበል ልምድ ተመራማሪዎች ይገረሙበታል፡፡ ሆላንዳዊው የኢትዮጵያ ወዳጅ ጆን አቢኒክ የህብረተሰቡ ፖለቲካዊ ባህል ለዚህ አይነት ሁኔታ ምቹ መሆኑን ያወሳሉ፡፡ አቢኒክ “ተቋማት፣ ባለሥልጣናትና ህዝብ በመንግሥት ቁንጮ ላይ ለተቀመጠው ማንኛው አካል” ተዛዥ ለመሆን እንደሚፈቅዱ ይተነትናሉ፡፡ በተጨማሪም ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር በሃገሪቷ ደረጃ አማራጭ ሀይል ሆኖ የሚያገለግል የሲቭል ሆነ የፖለቲካ ተቋም አልነበረም፡፡ በተጨማሪም የኢህአዴግ የወቅቱ ፖሊሲ የደርግ መንግሥት ተቆርቋሪነት አላቸው ብሎ የገመታቸውን ማጥፋት በመሆኑ ኢህአዴግንም መለስንም የሚቀናቀን ሊገኝ አልቻለም፡፡

## የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና 1993 ዓ.ም.

ኢህአዴግ ኤርትራን በሚመለከት እስከ 1991 ዓ.ም ድረስ ልል ፖሊሲ ያራምድ እንደ ነበር ይነገራል፡፡ ሆኖም በኢህአዴግ ውስጥም ሆኖ አቶ ስዬ አብርሃ የሚመሩት ቡድን በኤርትራ ላይ የያዘው አቋም አቶ መለስ ዜናዊ ከሚመሩት ቡድን በእጅጉ የተለየ ነበር፡፡ ሆኖም በኤርትራ ጉዳይ አጎብዳጅ ነው የሚባለው የአቶ መለስ ቡድን “ጉልበት ያበዛል” የሚሉትን የአቶ ስዬን ቡድን በስተመጨረሻው ማሸነፍ ችሏል፡፡ በዚህ ቡድን አቶ መለስን በእውቀት ሊፎካከሩ የሚችሉ ሰዎች ነበሩበት፡፡

## 2002ና መተካካት

ለረዥም ጊዜ ስልጣን ላይ መቆየቱ ሲያስወቅሰው የነበረው የኢህአዴግ ቡድን ወደ ምርጫ 2002 ዓ.ም የገባው መተካካት የሚል አዲስ መርህ በማምጣት ነበር፡፡ ሆኖም በዚህ አጋጣሚ ከዋና ዋና ስልጣን እንዲሁም ከመንግስት ባለስልጣንነት የተገለሉት ለረዥም ዘመናት የጠ/ሚኒስትርነቱን ቦታ የሚጠብቁ አሊያም ይተካሉ ተብለው የታሰቡ ነበሩ፡፡ ከነዚህም አቶ ግርማ ብሩ፣ አቶ ስዩም መስፍን፣ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀጥሎ የኢህአዴግ ሁለተኛ ሰው አሊያም ተስፋ የሚጣልበት ወጣት ተተኪ እንደሌለ ታዛቢዎች ይናገራሉ፡፡

አቶ መለስ ስልጣኔን እለቃሁ ባሉበት ቅርብ ጊዜያትም ቢሆን ስልጣናቸውን የባሰውኑ አደላድለዋል፡፡ የፖለቲካ ተንታኙ ሙክታር ሁንዴ «ስልጣንን ማደላደል ወደ አምባገነንነት የሚወስድ መንገድ መሆኑ ነው፤ አምባገነን ደግሞ “እኔ የሌለሁበት ሁሉ የለም” የሚል፤ ይህ ደግሞ “እኔ ከናንተ እንደ አንዱ ሳልሆን ከእናንተ የላቅሁ ነኝ” የሚል ነው» ይላል፡፡ ሙክታር «የ’George Orwel Piggs’ እንዲህ የሆኑት ቀስ በቀስ ነበር፡፡ አምባገነንነት ነገሮችን ብቻዬን ብወስን የማንም አበርክቶ አይጎድልብኝም ወደሚል አደገኛ ሁኔታ የሚወስድ አውራ ጎዳና ነዉ» ሲል ይሞግታል፡፡ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ዳንኤል ተፈራ በፃፈዉ የነጋሶ መንገድ መፅሃፍ ዉስጥ “...አንዳንድ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ስራ አስፈፃሚውን ሳያማክር እርምጃ ይወስድ ነበር” በማለት የመለስን ፖለቲካዊ ብቸኝነት ይገልፃሉ፡፡ አሁን ሀገርቷ ከግንቦት 20 ያተረፈችዉ ‹ብቸኛው› ሰዉ አቶ መለስ ናቸዉ፡፡

ወ/ተንሳይ ገ/ዚጊ ሻይ አንስቶ ለመጠጣት የሰው እገዛ ይጠይቃል፡፡ መደበኛ ስራ ስለሌለዉ የሰዎችን እጅ ማየት ግድ ብሎታል፡፡ ወ/ተንሳይ «ግንቦት ሀያ ለኔ መፀዳጃ ቤት ለመጠቀም እየተሸማቀቅሁ እርዳታ ለማግኘት ስል ሀፍረቴን የማሳይነት ስሆን መለስ ዜናዊም ለዘመናት ገነዉብን በመጨረሻዉ በአበበ ገላዉ ቁጣ በሀፍረት ለማቀርቀር ተገደዋል» ይላል፡፡

# የታክሲና የመንግስት ሌቦች



ነብዩ ኃይሉ

በአዲስ አበባ የሚታየው የትራንስፖርት እጥረት ተባብሷል፡፡ መንግስት ችግሩን ለመፍታት ያጸደቀው የታክሲዎች የዞን ስምሪት የተባለለትን ያክል ውጤት አላመጣም፡፡ በአማካኝ ከ8 ሺ እስከ 9ሺ የሚደርሱ ሚኒባስ ታክሲዎች በአዲስ አበባ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ ስራ ጋር በተገናኘ ገቢ የሚተዳደሩት ዜጐች ቁጥርም ከ40ሺ እንደማያንስ ይነገራል፡፡ ይህ የታክሲ አገልግሎት ዘርፍ በሌሎቹ የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ ከሚያጋጥሙት በሰፋ ደረጃ በብልሹ አሰራር የተተበተበ ይመስላል፡፡ ተጠቃሚዎች በአገልግሎት አሰጣጡ የአቅርቦትና የጥራት መጓደል የቀን ተቀን እሮሮ ያሰማሉ፤ ሾፌሮችና ረዳቶቻቸው የዞን ስምሪት አሰራሩን እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ በመጣው የነዳጅና መለዋወጫ ዋጋ ያማርራሉ፤ ባለንብረቶች ከስራው ማግኘት ያለባቸውን ያክል እንዳልተጠቀሙ በመግለፅ ያማርራሉ፤ መንገድ ትራንስፖርትና ትራፊክ ፖሊሶችም ታክሲዎችን በደንብ መተላለፍና በስነምግባር ጉድለት ይከሳሉ፤ መንግስት በታክሲ አገልግሎት ዙሪያ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችንና ችግሮችን ይፈታል ያለውን የዞን ስምሪት አሰራር ካስጀመረ አንድ አመት ቢያስቆጥርም የችግሮቹን መጠን ትርጉም ባለው ሁኔታ ለመቀነስ አልቻለም፡፡ አሁንም የትራንስፖርት እጥረቱ አልተቀነሰም፣ አሁንም ታክሲዎች አቆራርጠውና ከዞናቸው ውጪ ይጭናሉ፣ ከተተመነላቸው ታሪፍ ውጪም ያስከፍላሉ፡፡

## የተጠቃሚዎች ሰሚያጣ ጩኸት

ስምረት ትባላለች፤ ከምትኖርበት ካራቆሬ አካባቢ ተነስታ ወደ ምትሰራበት ቦሌ ለመጓዝ በማለዳ ብትነሳም አብዛኛውን ጊዜ ተሳክቶለት በመግቢያ በሰዓቷ ደርሳ አታውቅም፡፡ "በየቀኑ ከ10-30 ደቂቃ አረፍዳለሁ" የምትለው ስምረት ከስራ ሰዓቷ ላይ ከ10-30 ደቂቃ መስረቋ ከአሰሪዎቿ ጋር በተደጋጋሚ እንዳጋጫት ታስታውሳለች፡፡ እንደ ስምረት ሁሉ በጠዋት ከተለያዩ አቅጣጫዎች መጥተው ሜክሲኮ ደርሰው ወደ ቦሌ ለመጓዝ የሚፈልጉ ሁሉ እስከ 100 ሜትር የሚደርስ ችምችም ያለ ሰልፍ በግራ ወይም በቀኝ መሰለፍ ግዴታቸው ነው፡፡ ሜክሲኮ ቡናና ሻይ ፊት ለፊት ያሉ ተራ አስከባሪዎች ታክሲዎች ተራቸውን ጠብቀው እንዲጭኑ ከመቆጣጠርና ሁለት፣ ሁለት ብር ከመልቀም በዘለለ በጠዋት ወደ ቦሌ የሚጓዙ ተሳፋሪዎች ሰልፍ ይዘው ተራቸውን ጠብቀው እንዲስተናገዱ የማድረግ ኃላፊነትም ራሳቸው ላይ ጭነዋል፡፡ እነዚህ ተራ አስከባሪዎች ተሳፋሪዎችን እንደ አመጣጣቸው ተሰልፈው የሚስተናገዱበት መንገድ ባይዘይዱ ኖሮ በሌሎች አካባቢዎች እንደሚታየው ስምረትና መሰሎቿ ከ10-15 ደቂቃ ብቻ ለታክሲ ወረፋ ማጥፋት በባሰ ተሯሩጦና ተጋፍቶ መሳፈር ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ በአካባቢው የቁጥጥር ስራ እየሰራ ከሚገኝ መንገድ ትራንስፖርት ሰራተኛ እንደተረዳሁት በስፍራው ያለው ችግር የተባባሰው በቦሌ አካባቢ በመገንባት ላይ ያለው መንገድ ከተጀመረ ወዲህ ነው፡፡ "መንገዱ ስለተቆፋፈረ ታክሲዎቹ ወደ ቦሌ መሄድ አይፈልጉም" የሚለው ይህ ወጣት ታክሲዎችን በግዳጅ እንዲጭኑ በማድረግ ተጠምዶ እንደሚያረፍድ ይናገራል፡፡ የትራንስፖርት ችግር በጎላ ደረጃ የሚታየው ከስራ መውጫና ማታ ጭምር ነው፡፡ በአዲስ አበባ ካሉ ጥቂት ስፍራዎች በቀር በአብዛኞቹ አካባቢዎች ከፍተኛ የትራንስፖርት እጥረት ይታያል፡፡ አሁን አሁን ትርፍ መጫንና አቆራርጦ መጫን ህጋዊ አሰራር እንደሆኑ ሁሉ ቅሬታ ውስጥ መግባታቸው እየቀረ በቶሎ ተሳፍሮ ያሰቡበት መድረሱ በራሱ እንደ ትልቅ ነገር እየተቆጠረ መጥቷል፡፡ መንግስት ይህን የትራንስፖርት ችግር ለማቃለል ታክሲ አሽከርካሪዎችን በግዳጅና በቅጣት በመያዝ የትራንስፖርት እጥረቱን እንደሚፈታ ያመነ ይመስላል፡፡ አዲሱ የዞን ስምሪት ከወጣ ወዲህ ስምሪቱን ለሚከታተሉ በርካታ ወጣቶች የገቢ ምንጭ ከመፍጠር ባለፈ የትራንስፖርት እጥረቱ አሁንም አልቀነሰም፡፡ የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ በነዚህ ወገኖች እምነት የትራንስፖርት እጥረቱን ለመፍታት መንግስት የሚኒባስ ታክሲዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ መፍቀድን የመሳሰሉ ሁሉንም ወገን ተጠቃሚ የሚያደርጉ እርምጃዎችን ከመውሰድ ይልቅ የማስገደድ መንገድ በመከተሉ ችግሩን ከመፍታት ይልቅ አቶ መለስ አነጋገር ‹‹የመንግስት ሌቦችን›› አበራክቷል፡፡

## መንግስት ያፈራቸው ሌቦች

አቶ መለስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግስታቸው "የኔ" የሚላቸው ሌቦች እንዳሉት ለሚያስረዳ ንግግር ጣል ማድረግ ጀምረዋል፤ "የመንግስት ሌቦች" በማለት፡፡ እሳቸው አሁን ተናገሩት እንጂ ህዝቡ ይህን ከተረዳ ሰነባብቷል፡፡ የመንግስት ብልሹ አስተዳደር የፈለፈላቸው "የመንግስት ሌቦች" ጉዳዩን እንዲያስፈፅሙለት የተሟላ ሰነድ ብቻ ሳይሆን የተጨበጠ ገንዘብ እንደሚያስፈልገው ህብረተሰቡ ከተረዳ ቆይቷል፡፡ ተስፋዬ ሻሜቦ እ.ኤ.አ 2007 "anti corruption efforts in Ethiopia" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናታቸው እንዳመለከቱት በኢትዮጵያ የሙስና ምንጭ ከሆኑት ዋና ምንጮች ውስጥ ደካማ መንግስታው አስተዳደር፣ ተጠያቂነትና ግልፅነት አለመኖር፣ ዴሞክራሲያዊ ባህል በአነስተኛ ደረጃ መገኘቱ እና ቅጥ ያጣ ድህነትና ኢኮኖሚያው ኢ-ፍትሃዊነት ናቸው፡፡

ዝርፊያ ከተስፋፋባቸው ዘርፎች መሀል የትራንስፖርት ዘርፍ አንደኛው ነው፡፡ በፊት በፊት በትራፊክ ፖሊሶች አካባቢ ይታየ የነበረው ጉቦ አሁን መዳረሻው ሰፍቷል፡፡ የታክሲ ሾፌሮች እንደሚሉት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ጉቦን ያካተተ ካልሆነ ፈታኝ ነው፡፡ "ታፔላ ሊታደል አንድ ሳምንት ሲቀረው መንገድ ትራንስፖርቶችን እስከ 300 ብር ከሰጠሀቸው አሪፍ መስመር ይመድብሃል" የሚለው አስተያየት ሰጪ በታክሲ ስራ ላይ ከስድስት አመት በላይ ሰርቷል፡፡ በአስተያየት ሰጪው አባባል በትራንስፖርቱ ዘርፍ ጥቅምን ለማስከበር እጅ መንሻ መስጠት የግድ ነው፡፡ ከመስመር ውጪ መጫን ቢያስቀጣም ተቆጣጣሪዎቹን በገንዘብ ማለፍ ቀላል እንደሆነ የታክሲ ሹፌሮች ይናገራሉ፡፡ ከመገናኛ ሜክሲኮ የሚሰራው ሌላው አስተያየት ሰጪ ሰለሞን ለመንግስት አካላት የሚሰጠው ጉቦ ስርዓት እየሆነ እንደመጣ ይናገራል፡፡ እንደ አስተያየት ሰጪው ማብራሪያ አንድ የታክሲ ሾፌር በቀን አንዴ ሲከፋም ሁለት ሦስቴ ከቅጣት ለመዳን ለትራፊኮች ጉቦ ይሰጣል፡፡ በታክሲ ስራ ላይ ታሪፍ የተደነገገው ለተሳፋሪዎች ብቻ አይመስልም፤ ሹፌሮቹም ለትራፊኮች የሚሰጡት ጉቦ እንደ የጥፋታቸው ክብደት የውስጥ ለውስጥ ተመን ወጥቶለታል፡፡

"ለትራፊኮቹ የሚሰጠው ጉቦ እንደ ጥፋቱ ይለያያል፡፡ ለታክሲ ዝቅተኛው 20 ብር ከፍተኛው ደግሞ 50 ብር ነው" የሚለው ሰለሞን ከፍተኛ ጥፋት ከሆነ አንዳንዴ ከ50 ብር በላይ መክፈል እንደሚጠይቅ ያስረዳል፡፡ ‹‹ታክሲ ተራ አካባቢ ቁጥጥር የሚያደርጉት የመንገድ ትራንስፖርት ሰራተኞች ደግሞ በቀጥታ ታርጋ ሊፈቱ ስለሚችሉ ተለማምጦ ቦርሳቸው ውስጥ ሃያም ሰላሳም ብር ጣል ማድረግ የግድ ነው›› ይላሉ የታክሲ ሾፌሮችና ረዳቶቻቸው፡፡

እነዚህ ህግን ለማስከበር የተሰማሩ አካላት የሚወስዷቸው እርምጃዎች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የትራንስፖርት እጥረቱን እንዲሁም በትራንስፖርቱ ዘርፉ ያለውን ብልሹ አሰራር መቀነስ ወይም ከተቻለ ማስወገድ ይጠበቅበት ነበር፡፡ ሆኖም በተግባር የችግሮቹን ደረጃ ከማናር እና ከማወሳሰብ የተሻለ ነገር አላደረጉም፡፡ ለቁጥጥር እና ህግን ለማስከበር የሚወጡት አካላት በአብዛኛው በሚሰጣቸው ጉቦ ኃላፊነት የጐደለው ተግባር ይፈፅማሉ፡፡ ከመገናኛ አራት ኪሎ መስመር የሚሰራው ብርሃኑ ከታክሲ ስራ ጋር በተያያዘ ሁሉም ነገር በገንዘብ የሚፈፀም እንደሆነ ያምናል፡፡ "ከትራፊክ አንስተህ መንገድ ትራንስፖርት ድረስ ያለ ገንዘብ የሚያስተናግድህ አታገኝም" የሚለው ብርሃኑ በትራንስፖርቱ ዘርፍ ስር የሰደደውን ሙስና ለማሳየት ይሞክራል፡፡ የታክሲ ሹፌሮች ጉቦ ሳይሰጡ ወጥተው የሚገቡበት አጋጣሚ እጅግ የጠበበ ይመስላል፡፡ መንግስት ለመቆጣጠር ህግን ለማስከበር የሚያሰማራቸው አካላት ኃላፊነታቸውን አለመወጣታቸው የትራንስፖርት ችግሩን ካለማቃለሉም በላይ ሙስናን ስርዓት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በታክሲ ስራ ተጠቃሚ የሆነው መኪናዩ በሰላም ወጥቶ ይገባ ይሆን እያለ በጭንቀት የሚውለው የታክሲው ባለንብረት ቢሆን ትክክል ይሆን ነበር፡፡ መቀመጫው ‹‹እስኪ ቃጠል›› ሲያሽከረክር የሚውለው ሾፌር አልያም ጉሮሮው እስኪነቃ የሚጮኸው ረዳት ተጠቃሚ ቢሆኑም ያልሰራ ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ትራፊክ ፖሊሶች ከባለንብረቱም ሆነ ከሾፌሮች የበለጠ ገንዘብ በየቀኑ መሰብሰባቸው አስገራሚ ነው፡፡

## የሾፌሮቹና የባለንብረቶች ፈተና

"ሁልጊዜ ደህና ብር ይዘን አንወርድም፣ የነዳጅና የእስፔርፓርት ዋጋ ያለማቋረጥ ይጨምራል" የሚል ቅሬታ የሚያቀርበው ብርሃኑ፣ የአብዛኞቹን የታክሲ ሹፌሮች ሀሳብ ለመወከል ይጥራል፡፡ ከተለያዩ ሹፌሮች የሚሰማው ቅሬታ ባብዛኛው የነዳጅ ጭማሪውና እሱን ተከትሎ የሚጨምሩትን የመለዋወጫና የጥገና ወጪዎች

ወደ ገፅ 15 ይዞራል....

# " እኔ አንገቴን ልድፋ..."

ብስራት ወ/ሚካኤል

afrosonb@gmail.com

ከላይ እሳት ከታች እሳት መሀሉ.... የሚባል እንቆቅልሽ ትዝ አይላችሁም? መልሱን ግን እንዳትመልሱ እሺ! ምስጢር ነዋ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትራችን ጠቅልለውን እየኖሩ ሰቆቃና ምሬታችን ጆሮ ዳባ ብለው በሁለት አህዝ የኢኮኖሚ ዕድገት ለዓለም በተለይ ለነ ባራክ አባማ ሊያስበሩ መሄዳቸውን ስሰማ ደስ ብሎኝ ነበር፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ "ጸረ ልማት" ኃይሎች በሀገራችን ላይ የታየውን "ፈጣን የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት" በያዝነው ዓመት ወደ ሶስት አህዝ ማደጉን ይነግሩልናል ብለን አስበናል፡፡ who minus who!

ደግሞም መሪያችን ርሃባዊ ልማት ማምጣታቸው እየታወቀ ዜጎችን በማሰር ዴሞክራት መሆናቸው የአደባባይ ሚስጢር ሆኖ ሳለ አቤ የሰራኸው ትክክል አልነበረም፡፡አንተ የናሽናል ፕሬስ ማኅበር አባል፤ አናውቅህም!? እሳቸው በሀብታም ሀገር መሪዎች ፊት በድፍረት ምደረ ሐበሻን የሚሸውዱበትን የቁጥር ጨዋታ ቀና ብለው ሳይተነትኑ መርፌ የጠፋበት አዛውንት ይመስል አቀርቅረው እንዲቀሩ ማድረግህን እኔ አልወደድኩትም፡፡

አቤ! በነ አንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ ከነ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ጋር በ"አሸባሪነት" መከሰስህን እረሳኸው እንዴ? እንደው አዛም ሆነህ ይሄ "አሸባሪነት" አለቀቀህም? እውነት ለመናገር ዕድሜዬን በሙሉ አቶ መለስ አናደውኝ እንጂ ራሳቸው አፍረውና አሳዝነውኝ አይቼ አላውቅም ነበር፡፡ ግን ዕድሜ ለአበበ ገላው፤ የእኛን ሀዘን ክሪክ ዴቪድ ሬገን ማእከል G-8 መሪዎች ስብሰባ ተሰማልና፡፡ ወቸ ጉድ! ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም አሉ! በድላችን ግንቦት 20 ዋዜማ ወቅት አቤ ጉድ አሳየኸን፤ ትመጣለህ እሺ! ያው ሰኔ 14 ቀን 2004 ዓ.ም.ሰባት ሞት እንፈርድብሃለን፡፡ ያው በልደታ ታውቀው የለ?

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትርዬ "እኔ እንዲህ እፍር፣ፍርፍር፣ ንፍር ልበልሎት" ወይ መሪያችን.! እውነት በመድረኩ ሁኔታዎን ላየ ጥሩ የበሬ ጥሬ ስጋ አረቄ ውስጥ የገባ ይመስል ኩምትር አሉ እኮ! እኔ አተር ልብላ፡፡

ለነገሩ ብዬ እንጂ በልማታዊ መንግስታችን እመርታዊ እድገት በእኛ ሀገር በትር እንጂ አተር አላየን! እንደው ተቻኩለው " መሬት የመንግስት ነው፤ የከተማ ሊዝ አዋጅ..." ብለው ባይሳሳቱ ኖሮ እኔ አፈር ልብላ እልዎት ነበር፡፡ ግን እኛን ብቻ ሳይሆን በክፉ ቀን አፈሩንም ጠቅለለውት አርፈዋልና ምን ላድርግ ጠቅላያችን፡፡

እኔን የገረመኝ! የአሜሪካን ፖሊስ ልማታዊ አይደለም እንዴ! ጠቅላይ ሚኒስትራችን በተከበሩና በታፈሩ መሪዎች ፊት ሲዘለፉ እንዴት ዝም ብሎ ያያል? አቤ! ማዕከላዊ የሚባል ፖሊስ ጣቢያስ እዛ አሜሪካ የለም ማለት ነው? አባማንም ቢሆን በእጅጉ ታዝቤያቸዋለሁ፡፡ ምክንያቱም በኢኮኖሚ ዕድገት የላሸቀችውን አሜሪካ እንደ ኢትዮጵያ በፈጣን ሁኔታ እንድትበለጽግ ራርተን "ደጉ ዲሞክራትና ልማታዊ መሪያችንን" ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ብንልካቸው አቀርቅረው ያፈረ ህጻን ያስመስሉብናል? ሁለተኛ አበባ ገላውም ሆንክ ባራክ ኦባማ እኔ በህይወት እያለሁ ኢትዮጵያን እነኳን መርገጥ ታሽታላችሁ! ቀን አለ!

አቤ! ጎበዝ ከሆንክ ኢትዮጵያ ውስጥና ታንዛኒያ እያለህ አትናገርም ነበር? ቢያንስ አዲስ አበባ በሚገኘው ማዕከላዊ ( 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ) የ4 ወር ምርመራ ጠይቀንብህ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት እንጥልህ ነበር፡፡ ላቅ ካለም ከአራዳ እስከ ልደታ እናመላልስ ነበር፤ አመለጥከን፡፡

ደግሞስ ፕሬዝዳንት አባማ በፀረ ሽብር ትግሉ ተባባሪ አልነበሩም እንዴ! እንዴት እኛ በ"አሸባሪነት" የከሰስነው ሱፋን ሽክ አድርጎ እንዲዘግብ ይፈቀድለታል? ፖሊሶቹስ ቢሆኑ?

አቤ! ጠቅላይ ሚኒስትራችንን "መለስ" አምባገንን ነው፤ የብዙኃን ገዳይ ነው፤ እስክንድር እና የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!...." እያለክ በመሪዎች ፊት እሳቸውን በመዝለፍህ አበሳጭተኸኛል፡፡ በተለይ ያ የአሜሪካ ፖሊስ ጀርባህን በእጁ ቸብቸብ እያደረገ "you made a point" "ትክክለኛውን ነገር ተናግረሃል" ማለቱ የባሰ አበሳጭቶኛል፡፡ ምክንያቱም እንደ እኛ ሀገር ፖሊሶች ማዕከላዊ አስሮ መደብደብ ሲገባው አንተን መልቀቁ ልማታዊ ፖሊስ አለመሆኑን እንድረዳ አስችሎኛልና፡፡

ይበልጥ የሚያናድደው የመድረክ መሪው ነው፡፡ መሪያችን አፍረውና ደንግጠው የእንቅልፍ ኪኒን ውጠው የደነዘዙ መስለው፤ በዝምታ አቀርቅረው ልማታዊ ያልሆነው ጋዜጠኛ አበበ ገላው እንደፈለገ እንዲዘልፍ ከፈቀዱ በኋላ አበበን "Thank you" በእኛ "አመሰግናለሁ!" ማለቱ ይገርማል! መሪያችን ሲዘለፍ አመሰግናለሁ ይላል እንዴ? እሱ እራሱ "በሽብርተኝነት" ሊከሰስ ይገባ ነበር፡፡

ወደ ገፅ 5 ይዞራል....

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሰረተ፡ ፡ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነዉ፡፡ ማንኛዉም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡ ፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን አለዉ የሚባለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነዉ፡፡

ዋና አዘጋጅ፡-
ሰለሞን ስዩም
አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 1
የቤት ቁ.028
ስልክ ሞባይል፡- 09 26 81 46 81

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ስልክ ሞባይል፡- 09 22 11 17 62
ብስራት ወ/ሚካኤል
ስልክ ሞባይል 09 23 11 93 74

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መስፍን
ስልክ ሞባይል 09 13 05 69 42

አምደኞች፡-ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ቀለሙ ሁነኛዉ
በለጠ ጎሹ
አንዷለም አራጌ
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ወንድሙ ኢብሳ

ኮምፒዩተር ጽሁፍ፡-
ብርቱካን መንገሻ
ህትመት ክትትል፡-
ወንድወሰን ክንፈ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ
አሳታሚዉ፡-አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
አድራሻ፡-አራዳ ክ/ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁ. አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ ከተማ ቀበሌ 07 የቤት ቁ.984
የዝግጅት ክፍሉ ስልክ፡-01 11249659
ፖ.ሳ. ቁ. 4222
ኢሜይል fnotenetsanet@yahoo.com
ujdparty@gmail.com
andinet@ andinet.org
ፋክስ ቁጥር ፡-+251-111226288

# ርዕሰ አንቀፅ



# የግሉን ዘርፍ እያሽመደመዱ “ነፃ ገበያ አለ” ማለት ነጭ ውሸት

በአንዲት ሀገር ውስጥ ነፃ እና ጠንካራ ማህበራዊ እንዲሁም የዴሞክራሲ ተቋማት እንደሚያስፈልጉ ሁሉ፤ ጠንካራ የግል ንግድ ዘርፉም ያስፈልጋሉ፡፡ የግል ንግድ ተቋማት ባልተጠናከሩበት የመንግስት ወይም በመንግስት የሚደገፉ የንግድ ተቋማት አይለው ይወጣሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በሀገራችን በኢትዮጵያ ጐልቶ ይታያል፡፡ በኃይለ ሥላሴ ዘመን በአንፃራዊነት በነፃነት እያበበና እየተጠናከረ መጥቶ የነበረው የግሉ ዘርፍ በደርግ ዘመን ተንኮታኮተ፡፡ የኢህአዴግ መንግስት ባህርይ ባይፈቅድለትም ዘመኑ በፈጠራቸው በአለማቀፋዊ ምክንያቶች አስገዳጅነት የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርዓትን ቢያውጅም፣ እስከ አሁን መንግስት እጁን ከገበያው ውስጥ አላስወጣም፡፡ መንግሥት “የልማት ድርጅቶች” በሚላቸው ጠንካራና አንጋፋ የንግድ ድርጅቶቹ ያልተጠናከሩትን የግል ተቋማት ይፎካከራል፡፡ በተጨማሪም የገዢው ፓርቲ ንብረት የሆኑት የንግድ ተቋማትም ከመንግስት የተለየ ድጋፍ እያገኙ ከግሉ ዘርፍ ነጋዴዎች ጋር ይፎካከራሉ፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፤ ከመንግስት ጋር የተለየ ቅርበት ያላቸው እንዲሁም ከከፍተኛ ባለስልጣናቱ ጋር በጥቅም የተሳሰሩ ነጋዴዎች የተለያዩ ያልተገቡ ጥቅሞችን እያጋበሱ ከግሉ ዘርፍ ነጋዴዎች ጋር ይፎካከራሉ፡፡ ከላይ ያየናቸው ሦስቱም አሰራሮች የግሉን ዘርፍ የሚያሽመደምዱ ናቸው፡፡ መንግስት ነጋዴ በሆነበት፣ የገዢ ፓርቲ የንግድ ድርጅቶች በገበያ ውስጥ ቁልፍ ቦታ በያዙበት፣ ከመንግስት ጋር የተሞዳሞዱ ነጋዴዎች ከመንግስት ህገወጥ ድጋፍ በሚያገኙበት ነባራዊ ሁኔታ ነፃ ገበያ አለ ማለት ነጭ ውሸት ነው፡፡ የአቶ መለስ መንግስት ዴሞክራሲን እና ሰብአዊ መብትን በወረቀት ላይ አስከብሮ፣ በተግባር ፀረ ዴሞክራሲያዊና ኢሰብአዊ እንደሆነው ሁሉ የነፃ ገበያን ስርዓት “ ገንብቻለሁ” እያለም በኢኮኖሚው ውስጥ እንዳሻው ያዝበታል፡፡ ለዚህም ነው ነፃ ገበያ በሀገራችን አለ የሚለውን ለመቀበል የተቸገርነው፡፡ ፍኖተ ነፃነት በሀገራችን እውነተኛ የዴሞክራሲ እና እውነተኛ ሰብአዊ መብቶች ተከብረው ማየት እንደምትፈልገው ሁሉ፤ እውነተኛ ነፃ ገበያ በሀገራችን ኢትዮጵያ እንዲኖር ትፈልጋለች፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት ባንኮች ባከማቹት የተቀማጭ ገንዘብ (Deposit) እጥረት ምክንያት እንዲሁም መንግስት የግል ባንኮች ላይ ባስተላለፈው ኢፍትሃዊ መመሪያ ምክንያት ባንኮች አደጋ ውስጥ በመግባታቸው ለነጋዴዎች ይሄ ነው የሚባል ግልጋሎት እየሰጡ አይገኙም፡፡ ይህ ሁኔታ የተለያዩ መሰናክሎችን ተቋቁሞ በማበብ ላይ የነበረውን የግሉን ዘርፍ ድባቅ የሚመታና የሚያሽመደምድ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ ሊፈታ ይገባዋል፡፡ መንግስት “ለልማት” በሚል ሰበብ ስልጣኑን ለማራዘም ሲል ከኢኮኖሚው ላይ የሚመጣው ገንዘብ ያለ በቂ ምክንያት ለፖለቲካዊ ቁማር ያለ አግባብ የሚበትነው ገንዘብ እንዲሁም የተሳከረው የኢኮኖሚያዊ ፖሊሲው በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚታይ ችግር ፈጥሯል፡፡ መንግስት ከፍተኛ ወጪ የሚያወጣው ባከስልጣናቱ እንደሚሉት ለልማት ስራ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ልማታዊ መንግስት ነኝ በሚል ሰበብ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም በማሰብ ሊያሳካ የማይችለውን የተለጠጠ እቅድ በማዘጋጀት፣ እዚህም እዛም በአንድ ጊዜ ለማልማት በመወጠሩ ነው፡፡ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት መንግስት በአምስት አመት አሳካዋለሁ የሚለው እቅድ የሚሳካ ባይሆንም ለከፍተኛ ወጪ ዳርጐታል፡፡ ኢህአዴግ እንደሚለው ጥያቄው የማልማትና ያለማልማት ሳይሆን፣ ልማት ለህዝብ ጥቅም ወይስ ልማት ለስልጣን ማራዘሚያ የሚል ነው፡፡ እርግጥ ነው ኢትዮጵያ ደሃ አገር እንደመሆኗ ብዙ መልማት ይገባታል፡፡ ሆኖም ኢህአዴግ የሚያደርገው እያለማሁ ነኝና ገንዘቦች ሁሉ ወደኔ ይምጡ” የሚልበት መንገድ አሁን እንደሚታየው የግሉን ንግድ ዘርፍ በማሽመድመድ ላይ ይገኛል፤ በዚህ ብቻም ሳያቆም ሀገሪቱን ወደ ከፋ የኢኮኖሚ ቀውስ ሊከታት ይችላል፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት እንዲሁም በዘላቂነት የነፃ ገበያ ስርአትን ለመገንባት መንግስት፣ የንግድ ምክር ቤቶች እና የንግዱ ማህበረሰብ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ እንዳለባቸው ፍኖተ ነፃነት ታምናለች፡፡

መንግስት ከላይ ለተጠቀሱት ችግሮች አድራጊና ፈጣሪ እንደመሆኑ የመጀመሪያው እርምጃ ስህተት እንደፈጠረ ማመን ነው፡፡ ስህተቱን ካመነና ለማስተካከል ከወሰነ አሁን ለተፈጠረው ችግር መንስኤው የሆነውን ከኢኮኖሚው ውስጥ የሚመጣውን ገንዘብ ማቆም እንዲሁም ለዚህ አላማው ይጠቀምበት የነበረውን ከግል ባንኮች የሚሰበሰበውን የግዴታ ዋጋ ያላቸው የቦንድ ግዢ ማስቆም ይጠበቅበታል፡፡ የግል ንግድ ባንኮችን ህልውና ለማስጠበቅም የሀገሪቱን ከ75 በመቶ በላይ የባንክ እንቅስቃሴ የተቆጣጠረውንና ከመንግስት ልዩ ድጋፍ የሚያገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ወደ ግል እንዲዞር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ከባለስልጣናት ጋር ህገወጥ ትስስር አድርገው የተለየ ጥቅም የሚያገኙ ጥቂት ነጋዴዎች ኢኮሚውን እንደተቆጣጠሩት መንግስትም አምኗል፤ በመሆኑም ይህን ችግር ሊፈታ የሚችል እርምጃ ለመውሰድ ከፈለገ ዋንኛው መፍትሄ በመንግስት አሰራር ውስጥ ይህንን ህገ ወጥ ድርጊት በር የሚከፍት አሰራር መዝጋት ነው፡፡ በተጨማሪም ይህን ሀገርንና ህዝብን የሚጐዳና ጥቂቶችን ባለፀጋ የሚያደርግ ተግባር ላይ የተሰማሩ ባለስልጣናት እና ነጋዴዎችን በህግ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

በመርህ ደረጃየንግድ ምክር ቤቶች የንግዱን ማህበረሰብ ወክለው ጥቅሙን የሚያስከብሩ እንዲሁም ጥቅሙን ከአደጋ የሚከላከሉ ናቸው፡፡ ሆኖም በሀገራችን ያሉት የንግድ ዘርፍ ማህበራት ነፃነታቸው ያልተጠበቀ ከጊዜ ወደ ጊዜ አቅማቸው የተዳከመ በመሆናቸው የንግዱን ማህበረሰብ ከማገልገል ወርደው የመንግስት አገልጋይ ከመሰሉበት ደረጃ ደርሰዋል፡ ፡ በአሁኑ ወቅት ያለውን የንግዱን ማህበረሰብ የገንዘብ እጥረትም ሆነ የግል ንግድ ባንኮች ላይ በመንግስት የተላለፈውን ኢፍትአዊ መመሪያ አስመልክተው ያደረጉት አንዳችም ነገር የለም፡ ፡ ሆኖም ከንግድ እና ዘርፍ ምክር ቤቶቹ መንግስትን የንግድ ምክር ቤቶች የንግድ ማህበረሰብ ያሉባቸውን ችግሮች በመረዳት ብቃታቸውን ለማስከበር ቁርጠኛ መሆን እንዲሁም ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ራሳቸውን መጠበቅና መከላከል አለባቸው፡፡

የንግዱ ማህበረሰብም ከመንግስትና ከንግድና ዘርፍ ምክር ቤቶች ሊያገኝ ይገባው የነበረውን ጥበቃ ባያገኝም፣ መብቱን ለማስጠበቅ ከእነዚህ አካላት ውጪ መብቱን በራሱ ለማስከበር መጣር አለበት፡፡ ምክር ቤቶቹ በሚያምንባቸው ወኪሎቹ እንዲመሩ ማድረግ እንዲሁም የመብት ጥሰቶችን በዝምታ ከማለፍ ይልቅ በተለያዩ መንገዶች ተደራጅቶ ርምጃ መውሰድ ይገባዋል፡፡

ፍኖተ ነፃነት እነዚህ ማስተካከያዎች እንዲወሰዱ የእየጠቆመች፤ መንግስት ለጉዳዩ አንገብጋቢነት ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጥ ታሳስባለች፡፡

# ይችን ሀገር ለመታደግ ጊዜው አሁን ነው



አንዳርጌ መስፍን

በሚቀጥለው ዓመት በ2005 ዓ.ም የአዲስ አበባ ምርጫ ይካሄዳል፡፡ ኢህአዴግ ለዚህ ምርጫ ከፍተኛ ዝግጅት እያደረገ እንዳለ ይታወቃል፡፡ የሕዝቡን ልብ ለመማረክም ሡፈር ለሰፈር ያሉ መንገዶችን በኮብል እስቶን ከማንጠፍ ጀምሮ እናቶችን አንድ ላምስት በመጠርነፍ ተጠምዷል፡፡ ገዥው ፓርቲ በዚህ ሁኔታ በሚባክንበት ወቅት ተቃዋሚዎችስ ምን እየሰሩ ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡

ተቃዋሚዎች አንድ ሆነው ኢህአዴግን መታገል ሲገባቸው እሱ በቀደደላቸው መንገድ እየተጓዙ በፓርቲዎች ጋጋታ እንደ ገመድ ጉተታ ጨዋታ ከገዥው ፓርቲ በከፋ መልኩ ሕዝቡን ወዲያና ወዲህ ሲጎትቱት እናስተውላለን፡፡ አንዱ በሌላው ላይ ጣቱን በመቀሰር ተግጦ በተጣለ አጥንት እርስ በርሳቸው እንደሚቧጨቁ ዉሾች ሲናከሱ ማየት ህሊናን ያቆስላል፡፡

በዚህ 20 ዓመታት ውስጥ ሁለት ሦስት እየሆኑ የፖለቲካ ፓርቲ መመሥረት ቀላልና ወጭን የማይጠይቅ የፈጠራ ሥራ ሆኗል፡፡ የቀልድ ጨዋታም እየመሰለ መጥቷል፡፡ ለምሳሌ፡-

የኦሮሞ ሕዝብ የመገንጠል ጥያቄ ይዞ የተነሳውን ኦነግን ሳይጨምር አሥር የፖለቲካ ድርጅቶች እንወክለዋለን በማለት እንደ ቅርጫ ሥጋ ለመቀራመት፣ አንዱ ሌላውን ጥሎ ለማለፍ በመጠላለፍ ሲወነጃጀሉ እናያለን፡፡ በሌላ አነጋገር የኦሮሞ ህዝብ በገዛ ልጆቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ቤተ ሙከራ ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡ “ዘጠኝ ሴሪ ከመን አያድንም” እንዲሉ የፓርቲዎች ቁጥር መንጋጋት የኦሮሞን ህዝብ መብት ሊያስከብሩለት አልቻሉም፡፡ የሚችሉም አይደሉም፡፡ እንዲያውም “የአህያ ባል ከጅብ አያድንም” እንዲሉ መከራና እንግልቱ፣ እሥራቱና ስደቱ እንዲባባስና የሰቆቃው ዘመን እንዲራዘም የድርሻቸውን እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ አሥር የፖለቲካ ድርጅቶች ባንድ የፖለቲካ ጥላ ሥር ሆነው ቢታገሉ ኖሮ ታምር ሊሰሩ በቻሉ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ቅንነቱም፣ ፍላጎቱም፣ ብቃቱም፣ እውቀቱም የላቸውምና ኢህአዴግ ከሚሰራው በላይ በህዝብ ህልውና ሲቀልዱ ይስተዋላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ብል እንደበላው ጨርቅ ተበሳስከው እንዴት ብለው ነው ኢህአዴግን ተፎካክረው ሊያሸንፉት የሚችሉት? ቀጥለው የተዘረዘሩት የፖለቲካ ድርጅቶች የድራማውን አሳዛኝነት ቁልጭ አድርገው የሚያሣዩ ናቸው፡፡

1. የኦሮሞ ህዝብ ነፃነት ግንባር (ኦህነግ)
2. የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ (ኦህኮ)
3. የኦሮሞ ፌደራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን)
4. የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ)
5. የኦሮሞ አቦ ነፃነት ግንባር (ኦአናግ)
6. የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ)
7. የኦሮሞ ነፃነት ብሔራዊ ፓርቲ (ኦሕፓ)
8. የኦሮሞ ነፃነት ፓርቲ (ኦነፓ)
9. ገዳ ሥርዓት አራማጅ ፓርቲ (ገሥአፓ)
10. የመላው ኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መኦሕዴፓ)

እነዚህ እንግዲህ ከኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ እውቅና አግኝተው ሰርትፊኬት የተቀበሉ ናቸው፡፡ ገና በሂደት ላይ ያሉ በኦሮሞ ህዝብ ስም ሊቋቋሙ የታቀዱ ሁለት ድርጅቶችም እንዳሉ ለማወቅ ችለናል፡፡ መታደል ወይንስ መታገል? ብሎ መጠየቅ አግባብ ነው፡፡ ለጊዜው የድምፁን መከፋፈል እንተወውና አንድ የኦሮሞ ዜጋ በምርጫ ወቅት የቱን የፖለቲካ ድርጅት ከየትኞቹ አውቆና ለይቶ ነው መብቴን ሊያስከብርልኝ የሚችለው፤ ይሄኛው ፓርቲ ነው ብሎ ሊመርጥ የሚችለው? ፍርዱን ለባለቤቱ ለኦሮሞ ህዝብ መተው ነው፡፡

በመሠረቱ የፖለቲካ ፓርቲ መሥርቶ አንድን ጨቋኝ ሥርዓት መታገል መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታው ጭምር ነው፡፡ ችግሩ አንዱን ብሔር ወይንም ጎሳ እንደ ገና ድፎ መቆራረሱ ላይ ነው፡፡ ርግጥ ነው የግለሰቦቹ የኑሮ ደረጃ መቀየሩና የሥልጣን ጥም ያለባቸውን ማርካቱ እውነት ነው፡፡ ያንዳንድ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ከ84 ዓ.ም ጀምረው ከተቀመጡበት የመሪነት ሥልጣናቸው እስካሁን ድረስ በሌሎች አልተተኩም፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ የፖለቲካ መሪዎች ጠ/ሚንስትር መለስን “ሥልጣን ላይ ቆዩ፣ ሥልጣን አለቅ አሉ፣ በሥልጣን ባለጉ” ብለው የመውቀስና የመተቸት ምን የሞራል ብቃት ሊኖራቸው ይችላል?

እነዚህ ፓርቲያቸውን እንደ ግል ርስተ ጉልት ወይንም ኩባኒያ የሚቆጥሩ መሪዎች አንድ ጊዜ ሥልጣን ላይ ከተቀመጡ በኋላ ሥልጣን አለመልቀቃቸው ብቻ ሳይሆን በሥራቸው ተተኪ ኃይል ማፍራት አለመቻላቸው ነው፡፡ አብራካቸው መካን ነው፡፡ ከኢህአዴግ የበለጠ ፀረ ወጣት አቋም አላቸው፡፡ ያለነሱ አዋቂ፣ ያለነሱ በስተቀር ለዚች ሀገር ተቆርቋሪ አለ ብለው አያምኑም፡፡ በመሆኑም በሚያስደንቅ ሁኔታ እነሱ ፕሬዚዳት፣ ም/ፕሬዝዳንት፣ ዋና ፀሐፊ፣ ፋይናንስ ክፍል ኃላፊ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ባጠቃላይ ሁሉንም ናቸው፡፡ ለዚህ እውነታ ምሳሌ የሚሆኑን ነፍሳቸውን ይማረውና አቶ ክፍሌ ወዳጆ ናቸው፡፡

አቶ ክፍሌ ወዳጆ ለፓርቲያቸው ሊቀመንበር፣ ም/ሊቀመንበር፣ ዋና ጸሐፊ፣ የፋይናንስ ኃላፊ አድርገው ራሳቸውን በመሾማቸው በመጨረሻ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ እሳቸውን ተክቶ የሚመራ በመጥፋቱ ፓርቲያቸውም ሞቶ አብሯቸው ተቀበረ፡፡ እንግዲህ የሳቸውን ዓይነት ምሳሌዎች ባሁኑ ወቅት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በሌሎች ያልተተኩ፣ የማይተኩ በርካታ ውዝፎች ሥልጣን ከተባለ ዛሬም ሥልጣን ላይ ተቀምጠው አሉ፡፡ በበኩሌ የሥልጣን ምስጢርነቱና ረቂቅነቱ አይገባኝም፡፡ ሊገባኝም አይችልም፡፡

በመሠረቱ የኦሮሞን ህዝብ እንወክላለን የሚሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ ማሳያ ጠቀስኳቸው እንጂ እያንዳንዱ ብሔርና ጎሳ ቢያንስ በአራትና በአምስት የፖለቲካ ድርጅቶች የተከፋፈለ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ሲደማመሩ እውቅና ያለገኙትን ጨምሮ ወደ 94 የሚጠጉ ፓርቲዎች እንዳሉ ፍንጮች ይጠቁማሉ፡፡ አሁን በቅርቡ እንኳን ምርጫ ቦርድ “መሥፈርቱን ያሟሉ 68 ፓርቲዎች ናቸው፡፡” ብሎ ከገለጸ በኋላ መስፈርቱን ያላሟሉ ዘጠኝ ፓርቲዎች እንደ ጠፉበት በቴሌቪዥን ያፋልጉኝ ማስታወቂያ አስነግሯል፡፡ እነዚህ ሁሉ ሲደማመሩ 77 ፓርቲዎች ይሆናሉ፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬ የሚያስፈልጓት 77 ፓርቲዎች ሳይሆኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢንዱስትሪዎችን መገንባት ነበር፡፡ ላገር እድገትና ለፉክክር ከሆነ ሁለት ወይንም ሦስት ፓርቲዎች ይበቋት ነበር፡፡ እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነው ተቃዋሚዎች የ2005 የአዲስ አበባን ምርጫ የሚቀበሉት፡፡ ገዥው ፓርቲ ለፍጡራኖቹ ብሩን እንደ ደረጃቸው አከፋፍሎ ለይምሰልም ቢሆን የምረጡኝ ቅድመ ክርክር በኢቴቪ በሚያካሄድበት ወቅት ተቃዋሚዎች ገና ከገመድ ጉተታ ጨዋታ አልወጡም፡፡

እንግዲህ እስከአሁን ለመዳሰስ የሞከርኩት የፓርቲዎችን ብዛት ወይንም መንጋጋት ነበር፡፡ ቀጥየ ደግሞ ዓይነታቸውን ለማስቃኘት እሞክራለሁ፡፡

## የፓርቲዎች ዓይነት

ቀደም ሲል ጥራት እንጂ የፓርቲዎች መንጋጋት ምንም እንዳልፈየዱና እንደ ማይፈይዱም ባሳለፍናቸው 20 ዓመታት ውስጥ አይተናል፡፡ ህዝባችን ቃል እንደተገባለት በቀን ሦስት ጊዜ መብላት ቢቀርበት ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ ጠግቦ መብላት ነበረበት፡፡ ግን አልሆነም፡፡ የጠገበው ነገር ቢኖር ውሸትና ክህደት ማጭበርበር፣ ማታለል፣ እብለትን የመሳሰሉትን ነው፡፡ ስደቱ፣ ርዛቱ፣ ርሃቡ፣ ከመኖሪያ ቀየው መፈናቀሉ በከፋ መልኩ እንደ ቀጠለ ነው፡፡ ሙስና ስርዓት ነው፡፡ በሥልጣን መባለግ ህሊናን አሳውሮ መርህና ሥርዓት ሆኗል፡፡ ዛሬ ህዝባችን የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጥቶ የኮሰመነ ኑሮ እየኖረ ደንዝዟል፡፡ ከድንዛዜው የሚያነቁት፣ ፍርሃቱን የሚገፉለት፣ ውርደቱ የሚከነክናቸውን የቁርጥ ቀን ልጆች ከፍ ሲልም ፓርቲዎች ማግኘት አልቻለም፡፡ ባለመቻሉም የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች ከጓዳው ድረስ በመዝለቅ እየቀለዱበት ይገኛሉ፡፡ ይህንን ሀቅ ለማሳየት ከፓርቲዎች ብዛት ጎን ለጎን ዓይነታቸውንም አበጥሮ ማወቁ ጠቃሚ ነው፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ፈላጭ ቆራጩ የሆነው ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ፤
2. በኢህአዴግ ቋንቋ “አጋር ድርጅቶች” የሚላቸው፤ የአፋር፣ የሶማሌ፣ የሐረሪ፣ የጋምቤላና፣ የቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ግዑዝ የነገድ ፓርቲዎች፤

ወደ ገፅ 12 ይዞራል....

# “ እኔ አንገቴን ...

ከ ገፅ 3 የዞረ....

“ገና ጉድ ይሰማል ከሀገር ከወጡ ....” ያለችው ማን ነበረች? አቦ! ይህችን የዘፈነችውን ሸልሙልኝማ! ካልሆነ ልማታዊ ዘፋኝ ትባል! እነ ኢ-ቲቢ(ኢቴቪ አላልኩም፤የለንማ!) የዚህ ዘፈን ወቅቱ ነውና በደንብ ልቀቁልን እና በደንብ እንስማ! ፐ!

ምክንያቱም አዲስ አበባ 4 ኪሎ ያለውን ፓርላማ ጠረጴዛ እየደበደቡ የሚያስፈራሩና አንበሳ የሚሆኑት መሪያችን ያለወትሮአቸው አፍረው፤ ተሸማቀውና አኩርፈው በዝምታ ማቀርቀራቸውን ሰምተናላ!

እኔ ያልገባኝ፤ መቼ ይሆን ጠቅላይ ሚኒስትራችን ውጭ ሀገር ሲሄዱ ኢትዮጵያውያን በያሉበት ተሰብስበው በደስታ የሚቀበሉአቸው? ለምንድ ነው? እሳቸውን መከራ የሚያሳዩብን? እነዚህ ኪራይ ሰብሳቢ የሆኑ የመንግስትና የግል ሌቦች እንዲሁም “ፀረ ህገ መንግስትና ፀረ ልማት ኃይሎች” የሚያበሳጩአቸው ሳያንስ ዲያስፖራውም እንዲህ ይሁን? ወይ ጉድ!

በርግጥ እሳቸውም “አንዳንዴ ያጠፋሉ” ልብ በሉ “አንዳንዴ” ነው ያልኩት፡፡ ይህንንም ያልኩት የሰው ፍጹም ( ስም አይደለም ተግባር) የለም በሚል የዕድገት ትሩፋት፤ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት ጥበቃ ለዲያስፖራውም ትንሽ ጉርሻ ጣል ቢያደርጉ ይህ ሁሉ አይመጣም ነበር፡፡ እኛማ ምን ጎድሎብን! ጌታዬ፡፡

አንዳንድ “ፀረ ልማት ኃይሎች” እርስዎ ደፋ ቀና ብለው ያመጡትን ልማት ያልበሰሉ ጥሬ ካድሬዎች “የመንግስት ሌቦች” እና ስለ እርስዎና ድርጅትዎ ኢህአዴግ ሲነሳ የሚያነፋንፉ ደህንነቶች ናቸው የሚደነፉበት ይላሉ፡፡ አቤት ወሬ.... አቤት፣አቤት ....፡፡ ይሄስ የምቀኛ ወሬ ነው፡፡

ደሞ እኮ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም. የቡድን 8 የበለጸጉ ሀገሮች ስብሰባ ላይ በኦባማ ተጋብዘዋል፡፡ እርስዎም በአሜሪካ ካም ዴቪድ ሬገን ማዕከል መድረክ ላይ ሊናገሩ ሲሉ ቀበኛው አበበ ገላው ዘልፎ አንገቶትን ያስደፋውን ምስል “ልማታዊ ያልሆኑ ዩ-ቲዩብ እና ሌሎች መገናኛ ብዙሃን ለዓለም ማሰራጨታቸው ምን ይሁን ብለው ነው?

የሚገርመው በርስዎ ልማታዊ መንግስት ጥረት በሀገራችን ድህንት ቀንሶ ከቁምሳ ወደ ቁምራ ተሸጋግረናል፡፡ ይሄም ያልተዋጠላቸው “ፀረ ልማት ኃይሎች” በየቀኑ ቁጥራቸው እየጨመረ በየጎዳናው ይለምናሉ፤ ተመስገን! እድሜ ለልማታዊ መንግስታችን፡፡

ሌላው በርስዎ ዴሞክራትነት ለቁጥር የሚታክቱ ብዙ ዜጎች ልክ እንደኔ በልክ ባለመተንፈሳቸው “ አሸባሪ” ተብለው ከቃሊቲ እስከ ዝዋይ፤ ከሸዋ ሮቢት እስከ ደዴሳ እና በሌሎች እስር ቤቶች ታስረዋል፡፡ ይሄም ቢሆን፣ አንዱ የዴሞክራሲያችን ትሩፋት ነው፡፡ እና ምን ይጠበስ ብሎ ነው ጋዜጠኛ አበበ እንዲህ የሚያሳፍሮት ? መቼም ልማታዊ ባለመሆኑ ይመስለኛል፡፡ ግን ለክስተቱ ለምን ብሔራዊ ሀዘን አይታወጅም?

ውይ በሞትኩት ( ደልቶኝ)! እርስዎ ስለ ኢኮኖሚ ዕድታችን ሊተነትኑ መሄዶትን እያወኩ እኔ ስለ ዴሞክራሲና ልማት መተንተን ጀመርኩ፡፡ ምነው ሸዋ! እሱንም እርስዎ መጥተው ለኛ ይተንትኑልን እንጂ! ባይሆን በዛ ቀበኛ ጋዜጠኛ አበበ ገላው የተፈጠረብዎት ... “እኔ አንገቴን ልድፋ...” የሚለውን የሞክሼን ዘፈን ጀባ ብየዎታለሁ፡፡እፎይ ጌታዬ! በርግጥ ይህች አለም ፍትሃዊ ባለመሆንዋ የበላ እያለ ያባላና የተመለከተ አንገቱን እንዲደፋ ይደረጋል፡፡ ቢሆንም እኔ በእርስዎ ከራበው ጨጓራዬ፣ ንጹህ ውሃ ከጠማው ኩላሊቴ እዲሁም በንዴት ከጠቆረው ጉበቴ ከምር ሙዚቃውን ጋብዤዎታለሁ፡፡

ይቅርታ! አንድ የረሳሁት ነገር አለ፡፡ እኔምለው! ኢትዮጵያ ውስጥ የእርስዎ ስም ሲነሳ ግስላ የሚሆኑት ደህንነቶና ካድሬዎችዎ እንዴት አማሪካን ሆነው አልታደጎትም? ኡ... በቃ ጌታዬ! አብረዎት የሄዱት ደህንነትዎ ልማታዊ ጠበቂ ሆነው አልተገኙምና በስሱ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እርምጃ ይወሰድባቸው፡፡ ምክንያቱም በእኛ በዜጎች ግብር የምንቀልባቸው ደህንነትዎና ካድሬዎ እንዴት መሪያችንን መጠበቅ ያቅታቸዋል? ስለዚህ ክቡር ሆይ ይታሰብበት! በተለይ አበበ ገላው አንተ እዛ አማሪካን ሆነህ ማንን ልታስጨርስ ነው መሪያችንን የምታስከፋብን? ያው ላንተም ቢሆን ለሰራኸው ስራ ሶስት የአንቦ ውሃ ጠበል ጋብዤሃለው፡፡

አሁን የሆነ አንዴ ሆኗል! እያንዳንድሽ ላልተወሰነ ጊዜ ምድረ ኪራይ ሰብሳቢ፣ የመንግስትና የግል ሌቦች፣ ጋጠወጥ ጋዜጠኞች፤ በተቃውሞ ፖለቲካ ጎራ ያላችሁ “ፀረ ህገ መንግስትና ጸረ ልማት ኃይሎች” እና አሸባሪዎች ሰሞኑን ከመሪያችን ጋር እሳፈጣለሁ ብትሉ ውርድ ከራሴ! ምክንያቱም አንባገነኖቹ አማሪካኖች ዴሞክራት መሪያችንን አበሳጭተውብናልና፡፡



# አዲስ አበባችን እንዴት ነሽ?

## ኢህአዴግ የት ያደርስሽ ይሆን?



ግርማ ሰይፉ ማሩ

ብራዚሎች "ብራዚሊያ" የምትባለው የፌዴራል (በነሱ አጠራር የዩኒየን) ከተማ ለመገንባት ሲወስኑ ብዙ አሳማኝ ምክንያቶች ነበሯቸው፡፡ ዩኒየን በሚሉት ሀገር ላይ የሚኖረውን የብራዚል ህዝብ አንድ የማድረግ እና የጋራችን የሚሏት የአስተዳደር ማዕከል እንዲኖራቸው ፍላጎት ነበራቸው፡፡ ለዚህም ቀድመው ከነበሩት ትላልቅ ከተሞች በሺ ኪሎ ሜትር ርቀት በንፅፅር አማካይ በሚባል ቦታ ከተማ መገንባት የጀመሩት የዛሬ 52 ዓመት ነበር፡፡ እስካሁን በሚፈልጉት ደረጃ ያልተሳካው በነጭና-ጥቁር (ብላክዲሴንደንት) መካከል ያለውን ልዩነት ማቀራረብ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን በጋራ ጉዳይ ላይ እንደ አንድ ሆነው ሰርተው ድንቅ የምትባል የፌዴራል መንግስቱ መቀመጫ የሆነች ከተማ ሰርተዋል፡፡

የዛሬ 52 አመት ብራዚሊያ የምትባል ከተማ ተቆረቆረች፤ ብራዚሎች ከተማ የመገንባት ልምድ እንዳላቸው በኩራት ነው የሚናገሩት) የሚገርመው ልክ የናንተው ምኒልክ አዲስ አበባን እንደመሰረተው ብለው ያወራሉ፡፡ እኛ ለዚህ ጉዳይ ካለን ክብር ይልቅ እነርሱ አላቸው፤ለአፍሪካ በተለይ ለኢትዮጵያ ያላቸው ምልከታ ልዩ ነው፡፡ ንጉሱ (ቀዳማዊ ኃይለስላሴ) ሀገራቸውን መጎብኘታቸውን በጥቁር ህዝቦች መካከል ለነበረ ግንኙነት መልካም ጅምር አድርገው ይገልፁታል፡፡ ይህም የታሪካቸው አካል ነው፡፡ ስለ አድዋ ድል ያውቃሉ፤ ስለ ሉሲ የሰው ልጅ እናትነት ያውቃሉ፡፡ የኛም መገኛ ነው ብለው የሚያምኑ አሉበት፡፡ ይህ የምነግራችሁ የተጠና ዲፕሎማሲ ሳይሆን በእውነት ከልብ እንደሆነ በማመን ነው፡፡

ምንሊክ አዲስ አበባን ሲቆረቁሩ (ማገዶና ውሃን ማእከል ማድረጋቸውን እንጂ ከተማው ምን መምሰል እንዳለበት ያስቀመጡት ዕቅድ መኖሩን አላውቅም) አሁን ያለችበትን ውጥንቅጥ ከተማ ለመስራት ግን አይሆንም የሚል እምነት አለኝ፡፡ ከቤት እስከ ከተማ የሚል ፕሮግራም አዘጋጅ የሆነው አርክቴክት ይህችን ችግር ተረድቶ ማብራሪያ ይሰጠኛል ብዬ አስባለሁ፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ከቤት እስከ ከተማ የተባለውን ፕሮግራም በብራዚል ቆይታዬ ቢያንስ በቀን አስር ጊዜ አሰታውስ እንደ ነበር ግን መግለፅ ይኖርብኛል፡፡ ብራዚሊያ የአረንጓዴ ከተማ ግንባታ ምሳሌ ነች፡፡ ብችል በሬዲዮ ብተርክላችሁ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ በዚያ ፕሮግራም የሰማኋቸው የአዲስ አበባ ወንዞች ማፅዳት ጉዳይ፤ ስለ ህዝብ መናፈሻና መዝናኛ፤ የህዝብ ስፖርት ማዘውተሪያዎች፤ ወዘተ...

ብራዚሊያ የተባለችው ከተማ የተገነባችው ከጅምሩ በዕቅድ ነው፡፡ የከተማው ፕላን ሲታይ የአውሮፕላን ቅርፅ ነው ያለው፡፡ በአውሮፕላኗ መብረሪያ ክፍል በሚመሰለው የከተማው ክፍል በጫፉ ላይ የዩኒየኑ ፕሬዝደንት መኖሪያና መስሪያ ቤት ይገኛል፤ በአጠገቡ ትልቅ ሰው ሰራሽ ሐይቅ ይገኛል፡፡ በዙሪያው የመንግሥት ተቋማት በሚያስደስት ስርዓት ተገንብተዋል፡፡ ቀሪው የከተማዋ ክፍል በማስተር ፕላን መሰረት ለሚሰሩ ዜጎቻቸው ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ለማመን በሚያዳግት ፍጥነትና ጥራት ያለው ትልቅ ከተማ በአጭር ጊዜ በዜጎች ተሳትፎ ገንብተዋል፡፡ አዲሱን ከተማ ለመገንባት ሲነሱ የቀድሞ ከተሞች ማደስ የሚለውን ሃሣብ የከተቱበት ምክንያት አንደኛው የመሬት ባለይዞታዎች ለይዞታቸው የሚጠይቁት ክፍያ መብዛቱ የሚጠቀስ ሲሆን፤ይህ ግን እንደኛዎቹ መሪዎች አዋጅ አውጥተው በመውረስ ሳይሆን አዋጭ የሆነ በተመጣጣኝ ዋጋ ቦታ የሚገኝበትን መላ በመፈለግ ነው የተወጡት፡፡ ጥበበኛ የሚባሉ መሪዎች ናቸው፡፡ የቀድሞውን ሳያጠፉ አዲስ መገንባት እንደሚቻል አሳይተዋል፡፡

መንግስት አዲስ አበባን ለማልማት በሚል የሚፈጥረውን ትርምስ ሳስበው በዓለም ላይ እንዲህ ያለ ምርጥ ተሞክሮ መኖሩን ሳያውቅ ነው ወይ የሚል ጥያቄ ማንሳቴ የማይቀር ነው፡፡ እንደምታውቁት ልማታዊ መንግሥታችን ሁሉንም እራሱ ሊሰራው ቢችል ደስ ይለዋል፡፡ ቢችል ምሳና እራታችንን እየመጣ በጉርሻ ቢያደርግልን ይመርጣል፡፡ ይፈልጋልም፡፡ ድርሻችንን ቀምቶ ላይሰራው ያበላሸዋል፤ የሠው መሬት ካልቀማሁ ልማት አይመጣም እየተባልን ነጋ ጠባ የፕሮፓጋንዳ ሰለባ ሊያደርጉን ይፈልጋሉ፡፡ በህዝብ ጥቅም ስም ህዝብ ያንገላታሉ፤ ከህዝብ ይቀማሉ፡፡ "ለህዝብ ነው" ይሉናል፡፡ አንድ ዜጋ እራሱን ችሎ የሚኖርና በጥቃቅን ማዕቀፍ መግባት ካልፈለገ፤ ህዝብ ከሚባለው ጎራ ይሰረዛል፡፡ ኪራይ ሰብሳቢ ምንትሴ የሚል ቅፅል ይለጠፍለታል፡፡

በነገራችን ላይ አዲስ አበባን ማልማት በሚል ለሚደረገው እንቅስቃሴ ድጋፍ አለኝ፡፡ አዲስ አበባ የአሮጌ ቤቶች (በተለይ ባለቤት የሌላቸው ቀበሌ ቤቶች) መከማቻ እንድትሆን አልፈልግም፡፡ የቀበሌ ቤት እንደሚታወቀው ባለቤት የለውም፡፡ "የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም" እንደሚባለው ማለት ነው፡፡ ልማቱ ግን ተካሂዶ አዲስ አበባችን ምን ዓይነት ከተማ እንደምትሆን፤ እየተሰራ ያለው ከተማ ምን እንደሚመስል እንኳን እኛ መደዴዎቹና ህዝብ አይደላችሁም የምንባለው ቀርቶ ዋና ነን የሚሉት የከተማና የመንግሥት ሹሞች አያውቁትም፡፡ ከንቲባውን ኩማ ደመቅሳን ጨምሮ፡፡ አሁንም ጊዜው ቢረፍድም ከሚቀር ስለሚሻል ምን ዓይነት ከተማ በምን ዓይነት የህዝብ ተሳትፎ እንደሚገነባ ሊነገረን ይገባል፡፡ የማናውቀው የከተማ ግንባታ ውስጥ በምንም መልኩ ደስ ስላለን ብቻ መሳተፍ አይቻልም፡፡የግልና የመንግሥት ድርሻ የሚባለው ተለይቶ ታውቆ መንቀሳቀስ የግድ ይላል፡፡

መንግሥት የመሰረተው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ልብ መግዛት ያለበት ይመስለኛ፤

- በአንድ ቀለበት መንገድና ጎተራ ማሳለጫ 3 ምርጫ መወዳደርና ማሸነፍ ይፈልጋል (ማሸነፍ የምትለዋን ገልብጣችሁ አንብቡት)፤ ይህ ምን ያህል ራዕይ የሌለው ፓርቲ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ብራዚሊያ በ52 ዓመት ለቁጥር የሚታክቱ የኛን የቀለበት መንገድ የሚያስንቁ መንገዶችና ማሳለጫዎች ሰርታለች፡፡ በዕቅድ የተመራ የከተማ ልማት ማካሄድ ችለዋል ብራዚሎች፡፡ ኢህአዴግ አሁን ባለው ፍጥነት የብራዚሊያ ተመጣጣኝ ከተማ ለመስራት 500 ዓመት አይበቃውም፡፡
- የዛሬ አምሳ ሁለት ዓመት የአማዞን ደን ባለቤት የሆነች ሀገር ስለ አረንጓዴ ከተማ ስታስብ እኛ ዛሬ የሲሚንቶ ቁልል እናስባለን፡፡ ብራዚሊያን ያየ የአዲስ አበባ ቦሌና ካዛንችስ ህንጻዎች እንዴት እንደሚያስጠሉ ይገባዋል፡፡
- ኢህአዴግ ልብ እንዲለው ጭምር መረሳት የሌለባቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ በብራዚል መሬት የማን ነው? ኮንዶሚኒየሞች የማን ናቸው? ወዘተ .... መልሱ በሙሉ የግል የሚል ነው፡፡ ይህ የኒዎሊብራል አመለካከት አይደለም፡፡ ዜጎች ይታመናሉ፤ ልማት ያመጣሉ፤ ይህም ለሀገራቸው ጥቅም ይውላል፡፡ "ኪራይ ሰብሳቢ ብሎ ስድብ የለም"፡፡ በተቃራኒው መንግሥት በአግባቡ ግዴታውን እንዲወጣ በህዝብ ጫና ይደረግበታል፡፡ ከኛ ሀገር ጋር በተገላቢጦሽ ማለት ነው፡፡ በእኛ ሀገር መንግሥት በህዝብ ላይ ጫና ያሳድራል፡፡

በነበረኝ ጊዜ ልብ ያልኩት እና ያስቀናኝ ነገር አረንጓዴ ከተማ የሚገነባ ህዝብና መንግሥት፤የመንግሥት ሌባ እንዳይኖር የሚጠብቅ ፓርላማ ማየቴ አንዱ ነው፡፡ በብራዚል የህዝብ ወኪሎች የሚያስቆጣቸው የገንዘቡ ቁጥር መብዛት አይደለም፡፡ የህዝብ ገንዘብ መሆኑ ነው ዋናው ጉዳይ፡፡ የህዝብ ሀብት የህዝብ ነው ይላሉ፡፡ (Public Fund is Public)

እንደ ብራዚሊያ ያለን ከተማ የሚመስል ፕሮጀክት ለማሰብ ከቡድን አስተሳሰብ ተላቀን ኢትዮጵያ ስለምትባል ትልቅ ፕሮጀክት ማሰብ የሚጀምር መንግሥት ሲኖር የሚመጣ ራዕይ ነው፡፡ ፍርሃቴ ለምሳሌ ሰላሌ ሜዳ ላይ የዚህ ዓይነት ፕሮጀክት ያለው መሪ ቢመጣ የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ እንዴት ይታያል? የሚል የማደናቀፊያ ጥያቄ እንደማይመጣበት ማሰቡ ላይ ነው፡፡ ይህ እንደማይሆን እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ጎጠኞች አደርጉን እኮ ጎበዝ፡፡ የራዕይ ያለህ !!

በቅርቡ የተከበሩ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ አንድ ግሩም ነገር ሲናገሩ አደንቋሪ በሆነው ኢቴቪ ሰምቻቸዋለሁ፡፡ ላሊበላን፣ አክሱምን፣ ሶፎሞር ዋሻን.፣ ወዘተ ለመጎብኘት አንድ ኢትዮጵያ የመጣ ሰው እዚያው መሄድ ግድ ይለዋል፡፡ እነዚህን የሚወክል ምሳሌ በከተማችን የለም የሚል ነበር፡፡ ድንቅ ሀሳብ ብየዋለሁ፡፡ ኢትዮጵያ ከሰማኒያ በላይ ብሔሮች የሚኖሩባት ሀገር እንደሆነች ይታወቃል፡፡ ሰማኒያ ወረዳ ያለው ምርጥ የከተማ ፕሮጀክት ማሰብ አይቻልም ወይ? የኦሮሚያ ባህል ማዕከል ብሎ በአንድ ሕንፃ ስር ከመወሸቅ፡፡ የዚህ ዓይነት አካሄድ ድሮ ነበረን፤በዕቅድ የተመራ ባይሆንም፡፡ ወሎ ሰፈር፣ ጎጃም በረንዳ፣ ወሊጋ በረንዳ፣ አሥመራ መንገድ፣ ወዘተ...... የሩቁን አቅርቦ ማሳየትም ያይል ነበር፡፡

# ኢትዮጵያዊነት ትናንት፣ ዛሬና ነገ

መ/ር ቀለሙ ሁነኛው

በቴዲ አፍሮ አዲሱ አልበም ውስጥ የአልበሙ መጠሪያ የሆነው "ጥቁር ሰው" የተሰኘው ሙዚቃ በሙሾ የዜማ ቅላፄ ታጅቦ በትዝታ ፈረስ የኋሊት አስጋልቦን ታሪክንና ታሪክ ሰሪዎችን እንድናስታውሳቸው ያስገድደናል፡፡ አዎን የዛሬዋ ኢትዮጵያ ህልውና አሳሳቢነት ከሙሾም በላይ ሙሾ ነው፡፡ ትናንት በዘር በሀይማኖት ሣይከፋፈሉ ኢትዮጵያን ከባዕድ ወራሪዎች ጠብቀው ለትውልድ ያበቁትን አርበኞቻችንን ህያው ተጋድሎ ህያው ያደረጉ ስንኞችን ከአልበሙ እናገኛለን፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያዊነትን ማዜም በኢህአዴጋውያን ዘንድ መናፍቅነት ነው፤ የዘር ጉዳይ እንጂ ኢትዮጵያዊነት በኢህአዴግ ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡ የትናንትናዋ ኢትዮጵያ ወልጋዳና ሸውራራ የዛሬዋ ግን ቀናና ብሩህ ተደርጋ ትሰበካለች፤ የሶስት ሺህ ዓመታት ታሪክዋ ወደ 100 ዓመት አጥሮና ባንዲራዋም ተራ ጨርቅ ተደርጎ ይፌዝበታል፡፡ የትናንትናዋ ኢትዮጵያ መሪዎች ጨቋኞች፣ አምባገነኖችና ነፍጠኞች፤ የዛሬዎቹ ደግሞ ብፁአን፣ ፃድቃን፣ ጠቢባን ተደርገው ይወደሱባታል፡፡ የትናንቱን ታሪክ እየካዱ ዛሬ ታሪክ ለመስራት ማሰብ ባጥን ያለ ግድግዳ ለማቆም እንደማሰብ ነው፡፡ የእኔነት ልክፍት ነው፡፡

በዓለማችን ከተነሱ የአገር መሪዎች መሀከል በክፉ ሥራቸው ለዘለአለም ከሚረገሙ እና ከሚወገዙት አንዱና ዋነኛው ፋሺስቱ ሂትለር ነው፡፡ ዓለማችንን እጅግ ለከፋ ጦርነት የዳረገ ከ6 ሚሊዮን በላይ አይሁዶችን እጅግ ሰቅጣጭ በሆነ መንገድ የገደለ መሪ ነው፡፡ "የአሽዊትዝ ሚስጥርን" ያነበበ ሂትለርን የሰይጣናት አለቃ ብኤል ዜቡል አድርጐ ይቆጥረዋል፡፡ ይህ ሰው በውስጡ የሰነቀው በእኩይ ምግባር የተከበበች አንዲት ሰናይ የምትመስል ቅናት ነበረችው፡፡ ጀርመንንና ሕዝቦቿን ታላቅ የማድረግ አባዜ፡፡ ዜጎቿ ከሰው ዘሮች ሁሉ ልቀው የተመረጡ እንዲሆኑ በተለይም እ/ር በቅዱስ ቃሉ "ህዝቤ" ብሎ ከሚጠራው የአይሁድ ህዝብ በላይ ስማቸው እንዲገኝ ምኞቱ ነበር፡፡ ትልቁ ጥፋቱ ግን ይህንን ምኞቱን ለማሳካት የመረጠው መንገድ ነው፡፡ ሌላውን ዓለም አጥፍቶ ጀርመንን ታላቅ ለማድረግ መሞከር የለየለት እብደት ነው፡፡

የዛሬዎቹ የአገራችን መሪዎች ደግሞ ጥፋት የኢትዮጵያን የትናንት ገፅታ አጠልሽተው የቀደሙት ህዝቦቿ በደም በአጥንታቸው ያዋቀሯትን ኢትዮጵያን፣ በዘርና በጐሣ ፖለቲካ ከፋፍለው ዜጎችን በጥላቻ ገመድ ተብትበው፣ ታሪኳን አንኳሰው ትውልዱን ለባዕድ አገር ስደት ዳርገው አንድነቷን ለመናድ መጣራቸው ነው፡፡ ሶማሊያ ምንም እንኳን የአንድ ቋንቋ ተናጋሪና የአንድ እምነት ተከታይ ቢኖራትም ዘርን ለፖለቲካ መሳሪያ በማድረጓ በጐሣ ፖለቲካ ከተናወጠች ሁለት አስርት አመታት አለፉ፡፡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቿ የሞት ሲሳይ ሆኑ፡፡ ስደትና እንግልት የሶማሊያውያን እጣ ፈንታ ሆነ፡፡ የጥንቶቹ ኢትዮጵያውያን የዘር ጉዳይን ቸል ብለው ኢትዮጵያዊነትን ያስቀድሙ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ከትናንት የተሻለ መሆን ሲገባው የከፋ አደጋ በአገሪቱ ላይ እያንዣበበባት መጥቷል፡፡ ዛሬ ዛሬ ኢትዮጵያውያን ያለፉትን መሪዎች ለማድነቅ እየተገደድን ነው፡፡ ትውልዱ ያልኖረበትን ትናንትና ከታሪክ እየቀዳ ለማድነቅ ተገዷል፡፡ ለዚህም ነው ተወዳጁ ኢትዮጵያዊ ብላቴናና የዘመናችን የሙዚቃ ፈርጥ ቴዎድሮስ ካሣሁን በጥቁር ሰው ሙዚቃው ምኒሊክን፣ ባልቻ አባነፍሶን፣ አሉላ አባነጋን፣ ራስ መንገሻን ወዘተ ጀግንነታቸውንና ድንቅ ኢትዮጵያዊነታቸውን እያወጋ ያቀነቀነው፡፡

### አያቶቻችንና የትናንትናዋ ኢትዮጵያ

እንደ ዛሬው ዘመናዊ ስልጣኔ ባልዳበረበት ወቅት በቤተ እምነቶች በሚሰጡ ትምህርቶች ብቻ በአመራር ብቃታቸውና በአገር ፍቅር ስሜታቸው ዛሬም አለም የሚያደንቃቸው መሪዎች ነበሩን፡፡ ቴዎድሮስ ለዘመናት ታሪክ የሚያስታውሳቸው ንጉስ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ለመግዛት በከፈሉት መስዋዕትነት በዘመኑ ስማቸው ከገነነው ከነ ታላቋ ብሪታንያ (Great Britain) እኩል የአገራቸውን ስልጣኔ ለማጉላት የነበራቸው ርዕይ በታላላቅ የታሪክ ድርሳናት ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ሞታቸው እንኳን የጀግና ሞት ነበር፡፡

ይህን ጽሁፍ ልፅፍ ስዘጋጅ ከ "ebs" ቴሌቪዥን ጋር ቃለ ምልልስ ያደረገችውን አርቲስት መሠረት መብራቴን ተመልክቻት ነበር፡፡ አድናቂዎቿ ለጠየቋት ጥያቄዎች ከሰጠችው ምላሽ በብርቱ ያስደመመኝ አንድ ነገር ነው፡፡ ከሞቱ ሰዎች አፄ ምኒሊክን በህይወት ካሉት ደግሞ ኔልሰን ማንዴላን አግኝታ ብታነጋግራቸው ደስታዋ ወደር እንደሌለው ተናገረች፡፡ ምክንያቶቿም አንጀት አርስ ነበሩ፡፡ ምንሊክ የኢትዮጵያ የሥልጣኔ አባት ዘመን በማይሽረው የአድዋው ድላችን ብርቱ የጦር መሪና የኢትዮጵያዊነት ፍቅርን

ወደ ገፅ 12 ይዞራል....

## ኢኮኖሚ

# ፕ/ር በፍቃዱ ደግፌ የገንዘብ ህትመት ፖሊሲን በመደገፍ የኢህአዴግን ልብ እያደነደኑት ነው

በለጠ ጐሹ ወ/ሚካኤል

ሚያዝያ 24/2004 በወጣው ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ፕ/ር በፈቃዱ ደግፌ ስለ ነፃነት እና ልማት የተናገሩትን አነበብኩ፡፡ "ነፃነት ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ነጻነታችን ይወስድብናል እንጂ አይሰጠንም፡፡ ማሰብና መናገር ተፈጥሮአዊ ነው" ያሉትን ወድጄላቸዋለሁ፤ ግን በነፃነት እና በልማት መካከል ያለውን ትልቅ ነገር አልነገሩንም፡፡ በነጻነት እና በልማት መካከል ዕውቀት አለ፡፡ በአእምሮአችን በነጻነት አስበን ዕውቀት ላይ እንደርሳለን፡፡ ዕውቀትን ደግሞ ወደ ልማት እንቀይረዋለን፡፡

ማሰብና መናገር ተፈጥሮአዊ ናቸው፡፡ ማሰብን ማንም ሊከለክለን አይችልም፡፡ ልንከለከል የምንችለው መናገርን ነው፡፡ ለዚህም ነው ኢህአዴግ ሕዝባዊ የንግግር (የውይይት) መድረኮችን ለመከልከል የቻለው፡፡ ሕዝቡ በማሰብ ያገኘውን ዕውቀት እርስ በእርሱ እንዳይለዋወጥ ኢህአዴግ ከልክሏል፡፡ ለምን? መልሱ ቀላል ነው፡፡ አስበን አስበን ባገኘነው ዕውቀት መሠረት፣ ኢህአዴግ የዘረጋው ሥርዓት ትክክል አለመሆኑን ደርሰንበታል፡፡ ስለዚህ፣ ሕዝቡ ሕገወጥ እና ኢፍትሐዊ በሆነው የኢህአዴግ መንግሥት ላይ የጋራ አቋም ይዞ፣ "አንፈልግህም፤ ከጫንቃችን ላይ ውረድ" እንዳይለው ይፈራል፡፡

ኢህአዴግ የሚፈራው ሕዝቡ አስቦ አስቦ የደረሰበት ፀረ ኢህአዴግ ዕውቀት ሊያስከትል የሚችለውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ነው፡፡ በሰሜን አፍሪካ ዓረብ ሀገሮች የተከሰቱትን ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮቶችን ያስታውሳል፡፡ ኢህአዴግ የሚፈራው በሕዝባዊ ማዕበል ተጠራርጎ እንዳይወሰድ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በነጻነት ለማሰብ የምንታገለው ትክክለኛውን ዕውቀት አግኝተን በልማት ጐዳና ለመገስገስ ነው፡፡ በነፃነት የማሰብ ተግባሩን ሕዝቡ የሚያካሄደው በጋራ ስለሆነ ከዚህ የማሰብ ሂደት የሚገኘው ዕውቀት የሚያስከትለው የጥቂት ሰዎችን ልማት ሳይሆን፣ ሕዝባዊ ልማትን ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ኢህአዴግ ሕዝቡ በነጻነት እንዳያስብ ሊከለክል አይችልም፤ ሊከለክል የሚችለው ያሰበውን እንዳይናገር፣ እንዳይፅፍ፣ ከወገኖቹ ጋር እንዳይወያይ፣ ያሰበውን ወደ ፖለቲካ ፕሮግራም ቀይሮ እንዳይደራጅና እንዳይታገል ነው፡፡

ይህን ሕዝባዊ በነፃነት የማሰብ፣ የማወቅ እና ሕዝባዊ ልማት የማምጣት ትክክለኛ መስመር ወደ ጐን በማድረግ ኢህአዴግ ራሱ በተለመው ‹የልማት› ጐዳና ሕዝቡን ለመምራት እየተፍጨረጨረ ነው፡፡ እስካሁን ካየነው ውጤት አኳያ ስንገመግመው ኢህአዴግ ያስገኘው ልማት ጥቂት ኢህአዴጐችን እና ደጋፊዎቻቸውን ብቻ የጠቀመ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ላይ ኢህአዴግ የሠራውን ነገር ብናይ እንኳን ለዚህ አባባል ጥሩ ማስረጃ እናገኛለን፡፡ ኢህአዴግ የሰፊውን ደሀ ሕዝብ መሬት በሊዝ ሽፋን ነጥቆ፣ ለጥቂት አባላቱና ደጋፊዎቹ በመስጠት ትላልቅ ሕንጻዎችን አሰርቷል፡፡ በአጠቃላይ ኢህአዴግ በአሥር ሺህ ደሀ ዜጐች ላይ ቤታቸውን አፍርሶ ለአስር ደጋፊዎቹ መሬት የሚሸጥና አላግባብ የሕዝብ ገንዘብና ንብረት የሚዘርፍ ወታደራዊ የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ ሕንፃዎቹን የሚሰሩት የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ገንዘቡን ያገኙት ሰርተው ሳይሆን፣ "ከበላይ አካል" በሚሰጥ ትዕዛዝ ከባንክ በሚያገኙት ብድር ነው፤ ብድሩን መክፈል ካቃታቸው ኢህአዴግ ሊሰርዝላቸው ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ፕ/ር በፍቃዱ ደግፌ በንግግራቸው ላይ "በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የተከሰተው የዋጋ ንረት የመጣው ገንዘብ ስለበዛ አይደለም" ብለው ይከራከራሉ፡፡ ፕሮፌሰር እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎት፡፡ ኢህአዴግ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሰባ ሚሊዮን ብር (70 ሚሊዮን ብር) ብድር እንዲያገኙ ለባንኩ ትዕዛዝ ቢሰጥለዎትና በአራት ኪሎ አካባቢ አንድ ሺህ ካሬ ሜትር (1000 ካ.ሜ) በድሆች ተይዞ የነበረን ቦታ ቢሰጥዎ፣ ፎቅ ሠርተው ለመጠቀም ፈቃደኛ ይሆናሉን? ለእርሶ የተሰጠው ሰባ ሚሊዮን ብር ምንም ዓይነት የምርት አስተዋፅዖ ሳያደርጉ ስለሆነ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን የገንዘብ አቅርቦት በመጨምር የዋጋ ንረት እንደሚያስከትል ጥርጥር የለውም፡፡ እርሶ አምርተው፣ ያመረቱትን ሸጠው፣ ካገኙት ገንዘብ ላይ የተወሰነ መጠን ቆጥበው ልዩነቱን ብቻ የተበደሩ ቢሆን ኖሮ፣ በዋጋ ንረት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ አነስተኛ ይሆን ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ የእርሶ አስተሳሰብም የገባኝ ይመስለኛል፡፡ ገንዘብ ሀብት ማሰባሰቢያ መሣሪያ (resource mobilizing instrument) ስለሆነ፣ በባንክ ብድር መልክ ኢኮኖሚው ውስጥ የሚገባው ገንዘብ፣ መሬት፣ የሰው ኃይል ካፒታል እና የቢዝነስ ዕውቀትን (enterprise) በማሰባሰብ የምርት ሂደት እንዲፈጠር ያደርጋል ነው፣ እርሶ የሚሉት፡፡ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ይህ ትክክል ነው፤ ግን መንግሥት በተለይ በብሔራዊ ባንክ በኩል ገንዘብ እያሳተመ በብድር መልክ የሚወስደው ገንዘብ በከፊል ምንም ለማያመርቱ ቁጥራቸው ከመጠን በላይ ለበዛ ሰላዮች፣ አፋኞች፣ ፖሊሶች፣ ወታደሮች፣ ካድሬዎችና አሸቃባጮች በልዩ ልዩ ሌሎች ጥቅማጥቅሞች መልክ የሚከፈል ገንዘብ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ይህን ገንዘብ ይዘው ገበያ ሲወጡ የሚፈጠረውን የዋጋ ንረት በዓይነ ህሊናዎ ይመልከቱት፡፡ እዚህ ላይ የገንዘብ መብዛት ጠቃሚ ነው ሊሉ አይችሉም፡፡

መደበኛ የባንክ ብድር ለምርት ዕድገት አስተዋፅዖ ሊያደርግ የሚችለው የቢዝነስ እውቀት፣ መሬት፣ በሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ቁሳዊ ካፒታል እንደ ልብ በሚገኙበት ኢኮኖሚያዊ አውድ ውስጥ ነው፤ እንደሚታወቀው በኢህአዴግ መንግሥት መሬት ማግኘት የሚችሉት የተወሰኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ቁሳዊ ካፒታል ሊገኝ የሚችለው ደግሞ በሀገሪቱ በቂ የውጭ ምንዛሪ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ በትምህርት እና ሥልጠና የጥራት ደረጃ መውደቅ ምክንያት የሰለጠነ የሰው ኃይል ማግኘትም ከባድ ነው፡፡ በተመሳሳይ፣ እነዚህን ሁሉ የምርት ኃይሎች የሚያቀናጀውንም የቢዝነስ ዕውቀት ለማግኘት ቀላል አይደለም፡፡ የአክስዮን ገበያም የለም፡፡ እናም በዚህ ሁኔታ "ገንዘብ ቢበዛም" ምንም ችግር አይፈጥርም ማለት ስህተት ይመስለኛል፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ የሚረጭ ገንዘብ ውጤቱ አንድ እና አንድ ብቻ ነው፤ ከጊዜ በኋላ ከቁጥጥር ውጪ የሚወጣ የዋጋ ንረት (hyperinflation or galloping inflation) ነው የሚፈጥረው፡፡

ፕ/ር በፍቃዱ ደግፌ እስኪ ገንዘብ ቢበዛም ችግር የለውም የሚለውን አባባልዎ ትንሽ ጠለቅ ብለን እንመርምረው፡፡ ከቋንቋ አጠቃቀም አኳያ (semantics)፣ በዛ ማለት ከመጠን አለፈ እንደማለት ስለሆነ ከልክ ያለፈ የገንዘብ መጠን እድገት ጥሩ ሊሆን አይችልም፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ገንዘብ የሚጨምረው በሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው፡፡ የሀገር ውስጥ ባንክ ብድር ሲጨምር፣ የተጣራ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ሲኖር እና ብሔራዊ ባንክ ገንዘብ አትሞ ለመንግሥት ሲያበድር ነው የገንዘብ መጠን የሚጨምረው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ዋናዎቹ መደበኛ የባንኮች ብድር እና የገንዘብ ህትመት መጨመር ናቸው፡፡ ንግድ ባንኮች የጥሬ ገንዘብ መጠንን መጨመር ባይችሉም፣ በቼክ የሚንቀሳቀስ ገንዘብ ይጨምራሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ለምሳሌ አንድ ሰው አንድ መቶ ብር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቁጠባ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ ቢያደርግ ባንኩ መቶ ብሩን መጠባበቂያ ይዞ አንድ ሺ ብር ሊያበድር ስለሚችል ነው፡፡ አንድ ሺ ብሩ በጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ ሳይሆን፣ በተንቀሳቃሽ ሂሳብ ውስጥ የሚቀመጥ በቼክ የሚንቀሳቀስ ገንዘብ ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የጥሬ ገንዘብ እጥረት ከደረሰበት፣ ከብሔራዊ ባንክ ሊበደር ይችላል፡፡ ይህ ገንዘብ ከማተም ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በአጠቃላይ እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ንግድ ባንኮች አዲስ ገንዘብ የመፍጠር ችሎታ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

ጠቅላላ ገንዘብ (broad money) የሚባለው ከጥሬ ገንዘብ ሂሳቦችን (savings, demand and time deposits) ያጠቃልላል፡፡ ብሔራዊ ባንክ ለመንግሥት የሚያበድረው አዲስ ገንዘብ እያሳተመ ጭምር በመሆኑ፣ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን የጥሬ ገንዘብ መጠን ያሳድገዋል፡፡

የባንክ ብድር ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ እንደሆነ በሚገባ ይታወቃል፡፡ ይሁንና የባንክ ብድር ሀብት የማሰባሰብ ሚናውን ተጫውቶና ምርት አስመርቶ ተመልሶ ለባንክ ካልተከፈለ ውጤቱ የዋጋ ንረት ነው የሚሆነው፡፡ ፕ/ር በፍቃዱ ደግፌ ይህንን ሳያረጋግጡ ነው "የገንዘብ መጠን መብዛት ችግር አያመጣም" ብለው የሚናገሩት፡፡ በተለይ መንግሥት ከብሔራዊ ባንክ በብድር መልክ የሚወስደውን ገንዘብ መልሶ መክፈሉን ማረጋገጫ ዘዴ ያለ አይመስለኝም፡፡ ውስጥ አዋቂዎች እንደነገሩኝ ከሆነ የመንግሥት የብድር ሂሳቦች እንደተፈለገው የሚለዋወጡ ናቸው፡፡ በግልጽ ቋንቋ ለማስቀመጥ የማጭበርበር ድርጊቶች ይፈፀማሉ፡፡ መንግሥት ከሀገር ውስጥ የሚበደረውን ገንዘብ ዓመታዊ በጀቱ ውስጥ ይጠቀምበታል፡፡ እዚህ ውስጥ ከላይ የጠቀስኳቸው ምንም ዓይነት የምርት ወይም የተጨባጭ አገልግሎት አስተዋፅዖ ለማያደርጉ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ሰላዮች እና ሌሎች መዥገሮች የሚከፈለው ደመወዝ አበል እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ይካተታሉ፡፡ በዚህ ላይ በሙስና የሚቀሸብ ብዙ ገንዘብ አለ፡፡ በአንድ ጥናታዊ ግምት ከመንግሥት በጀት በዓመት ከ10-15 ቢሊዮን ብር በሙስና ይዘረፋል፡፡ በመንግሥት የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ወጪ የሚደረገው ገንዘብ በአጠቃላይ ለዋጋ ንረት አንዱ መንስኤ ሲሆን በተለይ በፍጆታ ዕቃዎች (ጤፍ፣ ዳቦ፣ ዘይት፣ ወዘተ) ዋጋ ላይ ከባድ ተፅዕኖ ያደርጋል፡፡ በመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች የሚከፈለው ደመወዝና አበል በፍጆታ ዕቃዎች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው፡፡

ፕ/ር በፍቃዱ፣ ሕዝቡ በማሰብ ነፃነቱ ተጠቅሞ ለኢትዮጵያ የሚበጀውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት አውቋል፡፡ ይህንን ኢህአዴግ ሊከለክለው አልቻለም፤ አይችልምም፡፡ የምናስበውን የምናውቀው እግዚአብሔር እና እኛው ብቻ ነን፡፡ ኢህአዴግ የከለከለን የማሰብ ነፃነትን አይደለም፤ ኢህአዴግ የከለከለን ያሰብነውን መናገር፣ መጻፍ፣ ተሰብስበን መወያየትንና የጋራ አቋም ይዘን ይህን በፖለቲካ ፕሮግራም መልክ ቀርፀን እንዳንደራጅ እና ሰላማዊ ትግል እንዳናካሂድ ነው፡፡ እኛ ይህንን ማድረግ የምንፈልገው ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰ ሕዝባዊ ልማት ለማምጣት ነው፡፡ በሌላ በኩል ኢህአዴግ ለእኛ ነጻነት ባይሰጠንም፣ ኢትዮጵያዊና ሕዝባዊ የሆነ ልማት የሚያስገኝልን ከሆነ የእኛም መዳረሻ ዓላማችን ከዚህ የተለየ ስላልሆነ፣ ከኢህአዴግ ጋር የምንጋጭበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ክፋቱ ኢህአዴግ የሚሰራው ሁሉ የዚህ ተፃራሪ ነው፡፡ ኢትዮጵያን እያጠፋት ነው፡፡ ልማቱንም የጥቂት ሰዎች ልማት እያደረገው ነው፡፡ ፕሮፌሰር፣ በዚህ ሁኔታ የገንዘብ መብዛት ችግር አያመጣም ማለት በበኩሌ በሕዝብ ላይ እንደመቀለድ አድርጌ ነው የምወስደው፡፡ ያለን ብቸኛ አማራጭ በሰላማዊ መንገድ ኢህአዴግን ከሥልጣን ማስወገድ ነው፡፡ በሰላማዊ መንገድ ያልኩት በሁለት ምክንያቶች ነው፤ አንደኛው ሕዝቡ የራሱ የሆነ ተዋጊ ሠራዊት የለውም፡፡ ሁለተኛ በጥቂት ሰዎች በተደራጀ ሠራዊት የሚያዝ ሥልጣን ሕዝባዊ መሠረት ስለማይኖረው አሁን ካለው የተሻለ መንግሥት ለማስገኘቱ ምንም አይነት ማረጋገጫ የለም፡፡

የተቀናጀ ሰላማዊ ትግል ያሸንፋል!!

# መምህራን የስራ እገዳና የስንብት ደብዳቤ እየደረሳቸው ነው

ከሚያዚያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም የጠ/ሚ/ሩ ከፓርላማ ውሎ በኋላ ት/ት ቤቶች መምህራንን በሰበብ አስባቡ እያባረሩ መሆኑን ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡ በደረሰን መረጃ መሠረት የእርከን እና የደሞዝ ጭማሪውን የጠየቁ መምህራንን ሲያስተባብሩ ነበር የተባሉት መምህራን ጠንሳሽ (master mind) በሚል ስም ተለይተው ከማስተማር ስራቸው እየተሰናበቱ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከየካ ክ/ከተማ የት/ት ጽ/ቤት ቢሮ የወጣ አንድ የስንብት ደብዳቤ "የተጣለበትን ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው ከ17/7/2004 ዓ.ም ጀምሮ በት/ቤት ያሉ መምህራንን በማስተባበር የሥራ ማቆም እንዲመታ" አድርገዋል ካለ በኋላ "ይህ ተግባር በህግ የሚያስጠይቅዎ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከስራዎ የተሰናበቱ መሆንዎን እንገልፃለን" ይላል፡፡ በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡት ተሰናባች መምህራን "ህገ መንግሥታዊ መብት የሚሆነው ለገዥዎች ሲሆን ብቻ ነው" ያሉ ሲሆን "ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ ስርዓቱ የሚፈቅድ አይደለም" ሲሉ ተናግረዋል፡፡ አማራ ክልል ውስጥ ከሚገኝ አንድ ት/ት ቤት የተባረሩት መምህራን በበኩላቸው "ሚያዝያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መብታቸውን የጠየቁ መ/ራንን አውግዘው ነበር፤ ብቃት የሌላቸውና የማስተማር ፍላጐቱ የሌላቸው እንዲሁም በተማሪዎችና በወላጆቻቸው የማስተማር ብቃት የሌላቸው ናቸው ተብለው በሌሎች መ/ራን እንዲተኩ ጥያቄ ሲቀርብ መልስ አለመስጠታችን ነበር ክፍተቱ የተፈጠረው›› ሲሉ ሀላፊነት የሌለዉ ቃልመናገራቸዉን ይገልጻሉ፡፡ አስተያየት ሰጪዎቹ የመምህራንን አከርካሪ ለመስበር ስውር ስትራቴጂ እንደነበር አስታዉሰዉ ልክ ለጋዜጠኞችና ለፖለቲከኞች ‹አሸባሪ› የሚል ሴራ እንደተሴረላቸው ሁሉ ለመምህራንም ይህ መዘጋጀቱን ይናገራሉ፡፡ በያዝነው ሣምንት መገባደጃ በአዲስ አበባ አንድ ት/ቤት የደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው ለአንዳንድ መ/ራን ከስራ እንዲታገዱ የሚገልጽ ደብዳቤ ደርሷቸዋል፡፡ የዚህ ደብዳቤ ይዘት እንደሚገልፀው የመማር ማስተማሩ ሥራ ጉዳት እንዳይደርስበትና የግቢውን ፀጥታ ከማስጠበቅ አኳያ እንዲሁም የመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በመፍጠር የተከሰሱበት ክስ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ የመማር ማስተማሩን ሥራ እንዲያቆሙና በውጭ ሆነው የዲሲፕሊኑን ውሳኔ እንዲጠብቁ ት/ቤቱ ያሳውቃል የሚል ነው፡፡ ይህንን ዘገባ እየሰራን እስካለንበት ድረስ እነዚህ መ/ራን ት/ቤት ግቢ ውስጥ ሳይገቡ በውጭ ሆነው ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡

# ከስካይ ባስ ሰለባዎች ጀርባ ምን አለ?



ብዙአየሁ ወንድሙ

ግንቦት 2 ቀን 2004 ዓ.ም ረፋዱ ላይ ሁለት ተከታታይ የስልክ ጥሪ ደረሰኝ፡፡ "ዛሬ በ8 ሰዓት የስካይ ባስ ሰለባ ቤተሰቦች 6 ኪሎ በሚገኘው የስብሰባ ማዕከል ስብሰባ ስለምናደርግ እባክህ እንድትገኝልን" የሚል ነው፡፡ ጥሪዬን አክብሬ ተገኘሁ፡፡ አዳራሹ አጠገብ ስደርስ ግቢው ጭር ብሎአል፡፡ ሦስትና አራት ሰዎች አዳራሹ በር ላይ ይታያሉ፡፡ በተጠራሁበት ሰዓት ብደርስም ቀድሜ መጥቼአለሁ ማለት ነው ብዬ ግቢው ውስጥ ያሉትን ማስታወቂያዎች እየተዘዋወርኩ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ እያነበብኩ ሳለ አንድ አስተባባሪ በትህና ቀርቦ "የኔ ወንድም ከየት ነው የመጣኸው" ሲል ጠየቀኝ፡፡ "ከፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ" አልኩት፡፡ "እንኳን ደህና መጣህ፤ ግባ የጋዜጠኞች ቦታ ላሳይህ" ብሎ ወደ አዳራሹ ይዞኝ ዘለቀ፡፡

አዳራሽ ውስጥ አንዳችም ድምጽ አይሰማም፡፡ ወደ ውስጥ ስንገባ ግን በሁለትና በሦስት መቶዎች የሚቆጠሩ በጠቅላላ ጥቁር የሐዘን ልብስ የለበሱ ተሰብሳቢዎች አዳራሹን ሞልተውታል፡፡ ያላሰቡት ነገር ሲገጥምዎት የሚፈጠር የድንጋጤም የሐዘንም ስሜት እየተቀላቀለብኝ የተያዘልኝ ወንበር ላይ ተቀመጥኩኝ፡፡ ታዳሚውን በእርጋታ ለመቃኘት ሞከርኩኝ፡፡ ሁሉም በሐዘንና በሐሳብ ተውጠዋል፡፡ ሁሉም በየራሱ የሐሳብ ማዕበል ይዋኛል፡፡ ወደ መድረኩ ዞርኩኝ፡፡ ከ4 ወር በፊት ጥር 8 ቀን 2004 ዓ.ም የጥምቀትን በዓል ለማክበር ከአዲስ አበባ ወደ ጐንደር በመጓዝ ላይ የነበረው ሰካይባስ አውቶቢስ በመገልበጡ በአደጋና በቃጠሎ ህይወታቸው ያለፋ 42 ሰዎች ፎቶ ግራፍ ተደርድሯል፡፡ የሟቾቹን ፎቶ ግራፍ በቅርብ ርቀት ለመዳሰስ ሞከርኩ፡፡ የመመረቂያ ገዋናቸውንና ቆብ እንዳደረጉ የተለያዩ ሞያ ምሩቃን ፎቶ በብዛት ይታያል፡፡ የተወሰኑ የሙሽራ ልብስ የለበሱ የወጣቶችና የጐልማሳዎች ፎቶዎችም አሉ፡፡ በመጠኑ ከዳሰስኩ በኋላ የዕለቱን ፕሮግራም መከፈት መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡

ከአስተባባሪዎች አንዱ የዕለቱን የስብሰባ ዓላማ የያዘ ፕሮግራም መሠል ወረቀት ሰጠን፡፡ ወረቀቱ እንዲህ ይነበባል፡፡

"የዚህ ፓናል ውይይት ዋንኛ ዓላማዎች፡-

1. "ይህንን ችላ ተብሎ ሊቀር የሚቃጣውን አደጋ አስከፊነትና መንስኤውን ህብረተሰቡም ሊማርባቸው የሚገቡ ቁም ነገሮችን አጉልቶ ማውጣትና ማሳየት
2. አደጋው ከተከሰተ አራት ወር ሊሞላው ስድስት ቀናት ብቻ ቀርተውታል፡፡ ተጎጂዎች እንደ ዜጋ ኃላፊነቱ ከሚመለከተው አካል የሚጠብቁት የምርመራ ውጤት እንዳለ ሆኖ እስከመቼ መጠበቅ እንደሚኖርብን ለመጠየቅ ነው፡፡ ፀፀትን በይፋ ካለመግለጽም አልፎ እያደር በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል እንደሌለ ያህል ጉዳቱን አድራሹ ኩባንያ እራሱን ከምንም ኃላፊነት በግልጽ አያሸሸ እንዳለ ስለተረዳን በሁኔታው ግራ ተጋብተናል፡፡ ከህግና ከሞራል አኳያ ላሉትም፤ ለሞቱትም፤ መፍትሄው ምን ስለመሆኑ የባለሙያ አስተያየት ለማግኘት በማሰብ ነው፡፡
3. በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚገባው / የሚችል ወገን ካለ በይፋ ለመጠየቅና፤ ለደረሰው የአካል ጉዳትና የህይወት መጥፋት ለተጎጂዎች በተቻለ ፍጥነት ያለ ተጨማሪ ቢሮክራሲያዊ እና ውጣውረድ ፍትሃዊ ካሳና የህክምና ወጪ ሽፋን እንዲያገኙ ድምጻችንን ከፍ አድርገን ለማሰማት ነው፡፡
4. የተጎጂ ቤተሰቦች ለሞቱባቸው ወገኖች ማስረጃዎችን ለማግኘት በሚሄዱባቸው አንዳንድ ቦታዎች እንግልት ይገጥማቸዋል፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ከአደጋው አስከፊነት የተነሳ አስከሬናቸው ሙሉ ለሙሉ ተቃጥሎ ያለቀ ከመሆኑም በላይ ቀብራቸው አብዛኛው ቤተሰብ ባልተገኘበት ከዘመድ አዝማድ መኖሪያ አካባቢ ርቆ በጥድፊያ የተፈፀመ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የአሟሟታቸውን ሁኔታ ለየትኛውም ተቁዋም ለማስረዳት አስቸጋሪ በመሆኑ እንደሆነ የሟች ቤተሰቦች ያምናሉ፡፡ ስለዚህ መንግስት ይህን ሁኔታ እንዲረዳና ስለአደጋው አፈፃፀም በሁሉም ዘንድ ተገቢው ግንዛቤ እንዲፈጠር ማሳሰቢያ እንዲሰጥልን፡፡
5. በመጨረሻም በአደጋው የሞቱት ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ቢሆኑም የአሜሪካ፤ የእንግሊዝ፤ የአውስትራሊያ፣ የእስራኤልና፣ የሱዳን ዜግነት ያላቸው ወገኖች አሉበት፡፡ በመሆኑም የተጎጂ ቤተሰቦች የነዚህን አገር ኤምባሲዎችና በጎ ፈቃደኛ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር በመካነ ቀብራቸውና በሌሎች ቦታዎች ለመስራት ላቀድነው መታሰቢያ እንተጋገዝ ዘንድ ጥያቄ ለማቅረብ ነው" ይላል፡፡

የሰለባው ቤተሰቦች ተወካይ የሆኑት አቶ ጥላሁን መኮንን ንግግር አደረጉ፡፡ አቶ ጥላሁን በርካታ ጉዳዮችን አንስተው ተናግረዋል፡፡ ከብዙ በጥቂቱ እንዲህ ብለው ነበር፡፡ "መገናኛ ብዙኃን የሞያውን ሥነ ምግባር ጠብቃችሁ ውይይታችንን ለህዝብ ይፋ እንደምታደርጉልን ተስፋ አለን፡፡ ዛሬ እዚህ እፊታችሁ የተሰበሰብነው ጥር 8/2004 ዓ.ም ከአ/አ ወደ ጐንደር ሲጓዝ አባይ በረሃ ገደል ውስጥ ገብቶ ከሰል ሆነው ስለቀሩት ወገኖቻችን ነው፡፡ ጥቂት ሚዲያዎች ሽፋን ቢሰጡትም በህዝብ በሚሰበሰብ ግብር የሚተዳደሩት የመንግስት ሚዲያዎች ተገቢውን ሽፋን አልሰጡትም፡፡ ዛሬም እዚህ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ተጠርተው አልመጡም፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ በተሽከርካሪዎች ላይ የነበሩትን የተሳፋሪዎች ቁጥር፣ የሟቾች ቁጥር፣ በህይወት የተረፉትን ቁጥር፣ የደረሰውን የንብረት ውድመት መጠን እንድናውቅ አልተፈለገም፡፡ የአደጋውን መንስኤ እስካሁን አልተገለጠም፡፡ ስካይ ባስ ኢ.ማ ኃላፊነቱን አልወሰደም፡፡ እንዲያውም አደጋው ከተከሰተ ከወር በኋላ ስካይ ባስ አ/ማ ምንም እንዳልተፈጠረ አስተማማኝ ምቾት ያለው የፍጥነት መቆጣጠሪያ የተገጠመላቸው የሚል ማስታወቂያ አስነገሯል፡፡ ያለፈውን ጣጣ ሳይወጣ ዛሬም ያለከልካይ ያስነግራል፡፡ ጉዳት ስለ ደረሰባቸው ዜጐች ምንም መተንፈስ አለመፈለጋቸው በርካታ ጥያቄዎችን እንድንጭር አድርጐብናል፡፡ ተጐጂ ቤተሰቦች ድንገተኛ አደጋ ለምን ደረሰ የሚል ጭፍንና የተሳሳተ ግንዛቤ የለንም፡፡ አደጋው ዳግመኛ እንዳይከሰት የአደጋውን መንስዔ መርምሮ ማወቅና ይፋ ማድረግ ይገባል የሚል እምነት ግን አለን፡፡ ተጐጂዎች ተገቢውን ህክምናና አስፈላጊ ድጋፍ ማግኘታቸውን የአካልና የአእምሮ መረበሽ የገጠማቸውን ዜጐች ማረጋጋት ግዴታ ነው ብለን በጽኑ እናምናለን፡፡

- አደጋው ለምንና በምን ምክንያት ተፈጠረ?
- ለአደጋው መፈጠር ተጠያቂ ሊሆን የሚችል ወገን ማን ነው?

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

## የአደባባይ ምስጢሮች

### ኢቴቪ አጥፍቶ ጠፊ ሆነ እንዴ?

በኢህአዴግ መንግስት እንደ ሞያ ብቃት የሚታይበት ከጊዜ ወደ ጊዜ የህዝብ አመኔታ ያጣው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሰሞኑን ደግሞ "አጥፍቶ ጠፊ" የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶት እየሰማን ነው፡፡ እስከ አንገቱ በሙስና የተነከረው የኢህአዴግ አምባገነናዊ ሥርዓት ገበናው እየተጋለጠ ይገኛል፡፡ ዛሬ በየደረጃው ከሚገኙት የኢህአዴግ አባላት መካከል በሙስና ያልተጨማለቀው ማነው? ብሎ ከመፈለግ፤ ከባዱ ሥራ ከሙስና ጋር ያልተነካካ የኢህአዴግ አመራር ማግኘት ነው፡፡

ባለፈው ሳምንት አንድ የውጭ ቴሌቪዥን የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ዘርፈው በውጭ አገር ባንኮች ገንዘብ የሸሸጉ ባለሥልጣናት ስም ዝርዝር ከነብር መጠኑና ብሩ የሚገኝበት ባንክ እየቀረበ ነበር፡፡ ኢቴቪ መረጃውን ከህዝብ የሸሸገ መስሎት የቴሌቭዥኑን ጣቢያ ለመዝጋት የስርጭት ሞገድ ለመዘርጋት ሲሞክር ራሱም አብሮ ተዘጋ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ኢቴቪን በዲሽ /በመቀበያ ሳህን/ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ኢቴቪ እንደባለቤቱ አጥፍቶ ጠፊ ሆነ ማለት ነው?

### ነፃነት ቃሉ እንዲህ ይርከስ?

መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ፡፡

ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ፣

በተባለላቸው ስመጥሩ አርበኛ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ ስም የሩሲያው ቀይ መስቀል ማህበር ሆስፒታል ከፍቶ ሥራ ከጀመረ ግማሽ ምዕተ አመት ዘሏል፡፡ በተጨማሪም ለእኚህ የትውልድና ሀገር መመኪያ አዋሽ ኢ/ባንክ ከሆስፒታሉ በቅርብ ርቀት በስማቸው ለቅርንጫፍ መ/ቤቱ አገልግሎት የሚውል ህንፃ ሊገነባላቸው ነው፡፡ ይገባቸዋል፡፡ ገንዘብ ያለው አደባባይ በሚከልልባት አገር ለደጃዝማች ቢያንሳቸው እንጂ አይበዛባቸውም፡፡

ይልቅስ የኔን ትኩረት የሳበው ሚያዚያ 27 ቀን 2004 ዓ.ም ያውም በነፃነታችን (በባንዲራችን) ቀን በባልቻ መታሰቢያ ሆስፒታል በአውቶቡስ ፌርማታው በኩል በሚገኘው በሩ ግራና ቀኝ በሰቀለው ባነር ላይ ተጽፈው የሚነበቡት መልዕክቶች ናቸው፡፡ "በነፃነት መግባት ይቻላል!" የሚል፡፡

ኧረ ለመሆኑ! ፀሐፊዎቹ ሌላ ቃል ጠፍቷቸው ነው ነፃነትን የመረጡት? ወይስ የነፃነትን ቀን ታስባላችሁ እንጂ በርካታ ነፃነቶች በራሳችሁ ለራሳችሁ አሳጥታችኋል ለማለት ይሆን በነጻነት ቀን እጅግ ደቃቃ የሆነውን መብት ነፃነት ብላችሁ ያመላከታችሁን? ለማንኛውም ግን እናንተ ሌሎች ነፃነቶች እንደሚቀሩን እየነገራችሁን ነውና እባካችሁ በነካ እጃችሁ ሌሎቹንም አሳውቁን፡፡ ጐበዝ እንዲህ እንተጋገዝ እንጂ፡፡

## ህያው ለትንሳኤ ፊልም ፌስቲቫል ተዘጋጀ

ህያው ለትንሳኤ የተባለ የፊልም ፌስቲቫል መዘጋጀቱን አስተባባሪዎቹ ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡ አስተባባሪዎቹ እንደሚሉት ከግንቦት 6-16 በአዲስ አበባ ትያትርና ባህል አዳራሽ ይቀርባል ተብሎአል፡፡ በዚህ ዝግጅት በቅርቡ ለእይታ የቀረቡ 10 ፊልሞች የሚቀርቡ ሲሆን የጐላ አስተዋጽኦ ላደረጉ ደግሞ ሽልማት ይሰጣል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

## የኪነጥበብ ዝግጅት ተከናወነ

የአገሪቱ ታዋቂ ድምጻዊያን ሲዘፍኑበት የነበረው በአልማዝ ላሊበላ ከፌና ሬስቶራንት 30ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ባለፈው ቅዳሜ ልዩ የኪነ ጥበብ ዝግጅት ተከናወነ፡፡ የሙዚቃው ንጉስ ጥላሁን ገሠሠ፤ ኩኩ ሰብስቤ፤ ከተማ መኮንን፤ አመልማል አባተ፤ ኤልያስ ተባበል በርካታ ድምፃውያን ይጫወቱበት በነበረው አልማዝ ላሊበላ ሬስቶራንት ደማቅ ዝግጅት ቀርቧል፡፡ የአርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ልጅ የሆነው ዳንኤል ጥላሁን ዝግጅቱን ያቀረበ ሲሆን ኮሜዲያንም ታዳሚውን አዝናንተዋል፡፡

## "ጋጋሪው" አዲስ ፊልም ሊመረቅ ነው!

በኬብሮን ፊልም ፕሮዳክሽን ከአንስታይል ፊልም ፕሮዳክሽን ጋር በመተባበር ያቀረበው በደራሲና ዳይሬክተር ብሩክ ሞላ የተሠራውና "ጋጋሪው" በአይነቱ ለየት ያለ አስቂኝ የፍቅር ፊልም ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም በልዩ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር ቤት በ11፡00 ሰዓት ጥሪ የተደረገላቸው ሚኒስትሮች፣ አምባሳደሮች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ አርቲስቶች፣ ጋዜጠኞች እና የኪነጥበብ ቤተሰቦች በተገኙበት በደመቀ ሥነ ስርዓት ይመረቃል፡፡ በዚሁ ፊልም ላይ አርቲስት ሰይፈ አርአያ፣ መለሰ ወልዱ፣ ፋንቱ፣ ዊንታና ባራኪ፣ አላዛር ሳለልየ ዮሴፍ ጌታቸው፣ ቢኒያም ገረመው፣ አዝመራው ሙሉሰው ዳምጠው ታሪኩ፣ አይዞህበለው፣ ፋንታሁን እና ሌሎችም ተሳትፈውበታል፡፡ ፊልሙን ሰርቶ ለማጠናቀቅ 2 ዓመት ያህል ጊዜ ሲወሰድ 1፡30 ደቂቃ ይፈጃል፡፡

አንድ ያለ ፍላጐቷ ጋብቻ እንድትፈጽም የተገደደች ሴት ከፍቅረኛዋ ጋር ለመገናኘት የምታደርገውን ጥረት ያሳያል፡፡ ከገንዘብ ይልቅ ፍቅር አሸናፊ መሆኑን የምንገነዘብበት ፊልም ነው፡፡ ፊልሙ ከተመረቀ በኋላ በሁሉም የግል ሲኒማ ቤቶች ለተመልካች ይቀርባል፡፡

## በኢቴቪና በአንድነት ፓርቲ መካከል ስላለው ክስ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጠ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ፓርቲ በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት እና ጋዜጠኛ አብዲ ከማል ላይ በስም ማጥፋት ፍትሐ ብሔር ክስ መመስረቱ ይታወቃል፡፡

የፌዴራሉ የመጀሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 9ኛ የፍታብሔር ችሎት በተመሠረተው ክስ እና በነ አንዱዓለም አራጌ የክስ ሂደት አለው ስለተባለው ግንኙነት ለማወቅ የነ አንዱዓለም የክስ መዝገብ ቁጥርና የቀጠሮ ቀን እንዲቀርብለት ለግንቦት 10 ቀን 2004 ዓም ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር፡፡

ፍ/ቤቱም በሰጠው ትእዛዝ መሠረት በእለቱ የክስ መዝገብ ቁጥሩና የቀጠሮ ቀን ቀርቦለታል፡፡ በዚህም መሠረት የነ አንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ ጉዳይ አንድነት በኢቴቪ ላይ ከመሰረተው ክስ ጋር መገናኘት አለመገናኘቱን ለመመርመርና ትእዛዝ ለመስጠት ፍ/ቤቱ ለግንቦት 17 ቀን 2004 ዓም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ተለዋጭ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

## የመኢአድ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ለምርጫ ቦርድ አቤቱታ አቀረቡ

ታህሣሥ 17-18/2003 ዓ.ም በተደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤው ተሳታፊ የነበሩ አባላት በትላንትናው ዕለት ለምርጫ ቦርድ አቤቱታ ማቅረባቸውን የዜና ምንጮቻችን ገለጹ፡፡ የጠቅላላ ጉባኤው አባል ነኝ ያሉት አቶ ታጠቅ አሰፋ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት መረጃ "በትላንትናው ዕለት ቁጥራቸው ከመቶ በላይ የሆኑ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ለምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት አቤቱታ አቅርበዋል" ብለዋል፡፡

አቶ ታጠቅ እንደሚሉት "አቤቱታ አቅራቢዎች ያቀረብነው አቤቱታ በፓርቲያችን የተፈጠረውን አለመግባባት ጠቅላላ ጉባኤው ተጠርቶ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበትና እንዲቋጭ ጠይቀን መልስ ባለማግኘታችን የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡ ምርጫ ቦርድን ወክለው ያነጋገሩን አቶ ኤርሚያስ አሰፋ ጉዳዩን ዝም ብለን አልተውነውም፡፡ እየተከታተልነው ነው፡፡ በትግስት ጠብቁን በሚቀጥለው ሳምንት የመጨረሻ ውሳኔ እንሰጥበታለን፡፡ ብለውናል፡፡" ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡ በጉዳዩ ላይ የምርጫ ቦርድ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደረግነው ጥረት ለጊዜው አልተሳካም፡፡

ምልከታ

# ደርግ ለመምሰል መሞት ባልተገባን ነበር



ሰለሞን ስዩም

የደርግን ጦረኝነት ለመኮነን የሚያንገራግር ብዙ አይደለም፡፡ የደርግ ሁሉን ወደ ጦር ግንባር ፖሊሲ፣ ለመኮነን አይዳርገውም አያስብልም፡፡ ነገር ግን የሳንቲሙን ሌላኛው ገፅ እስቲ እንመልከት፤ ለመሆኑ ደርግ የኢትዮጵያን ወጣቶች ወደ እሳት ሲማግድ የነበረው ማንን ለመውጋት ነበር? ጦረኞቹ መንትዮች ህወሃትና ህግሓኤ በሌሉበት ደርግ ዴሞክራሲን እንኳ ባያሳካ ቁሳዊ ልማት አያመጣም ብሎ መደምደም ይቻላል? በደርግ አይነት አገዛዝ ቁሳዊ ልማትን ያሳኩ ሀገራት የሉም? ለመሆኑ ደርግን ጦረኛ በማድረጉ ሥራ የተወጠሩት ህወሓትና ህግሓኤ በተጠያቂነቱ ረገድ ድርሻ የላቸውም? እስከሚገባኝ ድረስ የደርግ ጦረኝነት ዋነኞቹ መንስኤዎች ህወሓትና ህግሓኤ (ህግድፍ) ናቸው፡፡ በመሆኑም የሁለቱ ጦረኛ ቡድኖች ውጤት የሚለካው ደርግ ሊያደርግ ይችል የነበረውን ነገር በማሳካት ሳይሆን ከደርግ ያጣነውን ዴሞክራሲ በማሳካት ነው፡፡

እነዚህ ቡድኖች ባይወጉት ደርግ መንገድ አልሰራም ያለበትን ድርሰን አላነበብኩም፡፡ ደርግ መንፈሳዊ ልማትን ከሚታከከው መሠረተ ትምህርት ጀምሮ ብዙ የልማት ፕሮግራሞችንና ዘመቻዎችን ነድፏል፡፡ ለተግባራዊነቱም ተንቀሳቅሷል፡፡ ነገር ግን የዛሬዎቹ ገዥዎቻችንና የኤርትራ ገዥዎች የእግር እሳት ሆነውበት ሊያሳካ የሚችልበትን አጋጣሚ አላገኘም፡፡

በዚህ አጋጣሚ እነዚህ ቡድኖች ሀገሪቱን የጦር ቀጠና ያደረጓት ከደርግ ጋር ተመሳሳይ አይነት ውጤት ለማምጣት ከሆነ ደርግን ለመጣል የተከፈለው የህይወት መስዋዕትነት ደርግ እነዚህን ቡድኖች ለመከላከል ከከፈለው የህይወት መስዋዕትነት ያንሳል ማለት ነው፡፡ ይህ ሊባል የሚችለው ቡድኖቹ ሊተኩ የሚፈልጉትን ቡድን የሚዋጉት እርሱ የያዘውን ቦታ ምናልባትም ሊያስገኝ ከሚችለው ግላዊ ጥቅም አንፃር ለመያዝ እንጂ ቦታው በሚሰጠው እድል ብዙዎችን ለመጥቀም አይደለም ማለት ነው፡፡

ይህንን ሀሳብ ለማሳመን አንድ ሁለት ምክንያቶችን ማንሳት በቂ እንኳ ባይሆን ፍንጭ ይሰጣል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በደርግ ዘመን የነበረችው ኢትዮጵያ ሴራ በተሞላበት አካሄድ ከመቶ ሃያ "እኩል" መኮንኖች ወደ አንድና /ብቸኛው መንግሥቱ ኃ/ማሪያም የመጣችበት አካሄድም ውጤትም የሚወገዝ መሆኑ ነበር፡፡ አሁን ያለችው ኢትዮጵያም ተመሳሳይ ዕጣ የገጠማት ናት፡፡ በጣምራ አመራር ከሚያምኑ የህወሓት ታጋይ መሪዎች ወደ "ብቸኛው" የከተማችን ፖለቲከኛ አቶ መለስ ዜናዊ መዳፍ ተጠቅልላለች፡፡ ዛሬ ዛሬ መለስ ዜናዊ ከሌሉ ኢትዮጵያ አትኖርም የሚሉ ወደ ኋላ የሚኖሩ የኢህአዴግ አባላት ብዛት አሸን ሆኗል፡፡ መለስ ዜናዊ "የማይተነትኑት የዕውቀት ዘርፍ፣ የማይሰጡት የመፍትሄ አይነት አይኖርም" የሚሉ ‹ዞምቢዎች› እንደ እንጉዳይ ፈልቷል፡፡ የበሽታውን ዘር የተሰቦ ያክል ተላላፊ ያደረገው ደግሞ ምሁራኑም ጭምር የዚህ ሀሳብ አቀንቃኝ ወደ መሆን መሸጋገራቸው ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የማነሳው ቁሳዊ ልማት ላይ ካታኮሩት ሁለቱ መንግሥታት የትኛው ለባለስልጣኖቹ የግል ምቾት ያደላ ነበር የሚለውን ማየት ነው፡፡ መቼም ኢህአዴግ እድለ ቢስ ከሚያስብለው ዘርፍ አንዱ የዘረጋው የሙስና ስርዓት ነው፡፡ በምልከታዬ በተደጋጋሚ አቶ መለስ ዜናዊ ወይ ክራይ ሰብሳቢነት አሊያም ልማታዊነት ያሸንፋል ብለው ቢደሰኩሩም እንደ መንግሥትም እንደ ግለሰብም የሸንፈታቸው ነገር ከቤታቸው እንደሚጀምር ገልጫለሁ፡፡ ግልፅ ነዉ መቼም፡፡ በ1993 ዓ.ም በደረሰው የህወሃት ክፍፍል መለስ ዜናዊ ቤተሰባዊነት ስርዓቱ ላይ መንሰራፋቱን ለማመላከት በናፓርቲዚም ሲሉ ግምገማ ማካሄዳቸዉ አይዘነጋም፤ ሆኖም ትንበያዉ ሰርቶ ይህ ነገር በቤታቸዉ ለመሆን በቃ፡፡ በመሆኑም በምንም መልኩ መዋጋት እንደማይችሉና እውነትም የመንግሥታቸው አንደኛው እጅ መታሰሩ አግባብ ነው፡፡ አይ አለመታደል መንግሥቱ ኃ/ማሪያምን አሊያም ባለቤታቸው ወ/ሮ ውብአንቺን በሙስና የጠረጠራቸው ማን ነዉ? አብዛኞዎቹ ፀሐፊዎች እንደ ወ/ሮ አዜብ መስፍን ቀጣይ መሪ በሚል አላጪቸውም፤ ይልቅ ለመሪ ሚስትነት ሳይሆን የቁስ ሚስትነት አሊያም የእድር አስተባባሪነት እንደሚመቹ ይናገሩ ነበር፡፡ ኢህአዴግ የመንግሥት ሽፍታ (ዘራፊ) እንዲሆን የትግራይ ገበሬዎች መሞት ነበረባቸው? አቶ መለስ ስልጣን ላይ 21 ዓመታት ሙሉ ቆይተቀው በየደረሱበት የተቃውሞ ድግስ እንድጠብቃቸዉ አይፈልጉም፤ በዚህም መስዋዕትነታቸዉ እንድኳሰስ አይፈልጉም፡፡ ሰሞኑን እንደ አበበ ገላው ካምፕ ዴቭድ የመገኘት እድል ቢገጥመኝ ስርዓቱን «ካኒባሊስትክ» ነው እል ነበር፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ አብዛኛው የታሪኳ ኩራት ከመንፈሳዊ ልዕልና የሚመነጭ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ኢህአዴግ የሚመራው መንግሥታችን ደግሞ ይህንን እንደ ጠላት የሚመለከት ነው፡፡ ይብስ ደግሞ ይህንን በቁሳዊ ልማት ለመተካት ይንቀሳቀሳል፡፡ ኢቴቪ የዚህ ሀሳብ ፊት አውራሪ ነው፡፡ በተጨማሪም የኛን ቁሳዊ እድገት በኤርትራ ውድቀት ልክ የሚስለው ኢቴቪ ኤርትራ በ2012 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) 18% እንዳደገች በአፍሪካ ደረጃ መነገሩን እንዲሁም በአለም አቀፉ የገንዘብ እና የአለም ባንክ የኢትዮጵያ እድገት 6% ብቻ መሆኑን እንደሚሰማ እገምታለሁ፡፡ ሦስትም አራትም ተኩኖ ተቃውሞ ማሰማት በማይቻልበት ሀገር ኢቴቭ አሜሪካውያን «ዎል ስትሬትን ተቆጣጠር» በሚል መርህ አደባባይ ወጡ ለማለት ማን ይቀድመዋል፡፡

እስከማውቀው ምሉዕ ልማት መንፈስን እና ቁስን ያካትታል፡፡ ለተጨማሪ ማብራሪያ አማርቲያን ሴንን ማንበብ በቂ ነው፡፡ ይህ እስካልተሳካ ድረስ ሞት ስለምን አስፈለገ? ልማት ማለትስ ምንድነው? ዴሞክራሲን ካላሳኩና ሙስናን ለማስፈን ለማስፈኑ ደርግ አይሻልም ነበር? በሙስና አላዉቀዉም ነበር፤ ለማንኛውም እነ አቶ መለስን አንድ ነገር ልጠይቅ፡- ‹ደርግን ወደ ጦርነት ባትከቱት መንገድ አይሰራም ነበር? ኮንዶሚኒየም አይሰራም ነበር?

# ከችሎት ትዝብት



ብስራት ወ/ሚካኤል

afrosonb@gmail.com

አይን ሁሉንም ነገር ማየት ፈልጐ ያያል ባይባልም ማየት ተመኝቶ የማያይ ጠልቶ የሚያልፍ ብዙ ሰው አለ፡፡ እንደ አጋጣሚ ማየት የማይፈልጉትን እጅግ አስከፊ ነገር ቢያዩ ምን ይሰማዎታል?

እስኪ በጥናቶች በአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ እምነት ያጣው የፖሊስ ተቋም የፈፀመው አሳዛኝ ድርጊቶች መካከል የተማሪ ሴና መረራ የተከሳሽነት ቃሉን ስሰማ ውስጤ እጅግ አዝኗል፡፡ የእኔ አካሄድ በ "ሽብር" ተጠርጥረው የመከላከያ ምስክር ሊያሰሙ የነበረውን የነ አቶ በቀለ ገርባ የክስ ሂደት ችሎት ለመዘገብ ነበር፡፡

እንደ ሴና አገላለጽ ታሪኩ እንዲህ ነው፡፡ ወጣት ሴና መረራ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ሲሆን ባላወቀው ምክንያት ከዩኒቨርስቲ ውስጥ በፖሊሶች እና ደህንነቶች ተይዞ አርባ ምንጭ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ይወሰዳል፡፡ እዛም ለ3 ቀናት ከቆየ በኋላ ተጠርጣሪ ዜጐች ላይ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና በደል በምርመራ ስም በሚፈፀምበት አዲስ አበባ ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ ይደርሳል፡፡

አዲስ አበባ ሰሜን ሆቴል አካባቢ በሚገኘው ማዕከላዊ እስር ቤት ከገባ በኋላ በሽብር ተግባር መጠርጠሩ ተነግሮት ምርመራ ይደረግበታል፡፡ በምርመራ ወቅት "አንተ የተለዋወጥካቸው መልዕክቶች ከኢ-ሜይል የወጡ ናቸው" ተብሎ በአማርኛ የተፃፉ ሰነዶች ተገኝተው፡ብሃልና የእኔ ነው ብለህ ፅፈህ ፈርም ይሉታል፡፡

ሴና "ፅሑፉ እኔ የተለዋወጥኩት መልዕክት አይደለም፤ አማርኛ መፃፍም ሆነ ማንበብ አልችልም" ሲል መርማሪ ፖሊሶቹ አስገዳጅ የኃይል ርምጃ መውሰዳቸውንም ለፍ/ቤቱ ገልፃሪል፡፡ በወቅቱ ለምርመራ ተራውን ይጠብቅ የነበረ ሌላ ወጣት ግንቦት 2 ቀን 2004 ዓ.ም የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት ቀርቦ ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡

ተማሪ ሴናም "ከኢ-ሜይል የወጣው ፅሑፍ የእኔ ነው" ብለህ ፈርም መባሉንና ይህንንም ፅሁፍ ምርመራ ክፍል ቀን ሙሉ እንዲለማመድ መደረጉን ገልፃሪል፡፡ በመጨረሻም የወጣውን የአማርኛ ሰነድ "የእኔ ነው" የሚለውን በግድ የተለማመደውን ፅፎ መፈረሙን ተናግሯል፡፡

ወጣት ሴና ማንበብና መጻፍ የማይችለውን በአማርኛ የተፃፈ ሰነድ በግዳጅ የእራሱ አድርጐ መፈረሙ አሳዛኝ ነው፡፡ ይህ ሳይታሰብ የተደመጠው የተከሳሽነት እና የምስክርነት ቃል ሁለት ነገሮችን አስታወሰኝ፡፡ የመጀመሪያው በቅርብ ጊዜ ወደ ህትመት ገብታ በህዝቡ (በአንባቢያን) ዘንድ ተቀባይነትንና ተወዳጅነትን ያገኘችው አዲስ ነገር ጋዜጣ በአንድ ወቅት አስደንጋጭም አሳፋሪም ነገር አስነብባናለች፡፡ ጉዳዩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች በተለይ ከኦሮምያ ክልል የሚመጡ አንዳንድ ተማሪዎች የዩኒቨርስቲውን ቅጽ በአግባቡ መሙላት ተስኗቸው መቸገራቸውን ሰምተናል፡፡ የዩኒቨርስቲው ቅጽ የሚሞላው በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ሲሆን ወጣቶቹ በተለይ የአማርኛውን ቅጽ መሙላት አለመቻላቸው ምንን እንደሚያስከትል እናስብ፡፡

ሁሉም ቋንቋዎች ጠቃሚና ተፈላጊ ሲሆኑ ለመልመድ ግን ግዴታን ሳይሆን በውዴታ መሆን ያለበት ይመስለኛል፡፡ ምናልባት የመግባቢያ አድማሱ ይለያይ ይሆናል እንጂ ቋንቋዎች ሁሉ ከጠቀሜታ አንፃር እኩል ናቸው፡፡

በተባበሩት መንግስታት "ዓለም አቀፍ የህፃናት ኮንቬንሽን" ላይ በፈረሙ ሀገሮች ሁሉ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው "ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት አላቸው" ይላል፡፡ ይህን ድንጋጌ ከተቀበሉ ሀገሮች መካከልም ኢትዮጵያ አንዷ ስትሆን ድንጋጌው "መብት አላቸው" የሚለውን የኢትዮጵያ መንግስት "ግዴታ አለባቸው" በሚል ያስገደደ ይመስላል፡፡

በተለይ በኦሮሚያ ክልል ጉዳዩ ጫፍ የወጣ ይመስላል፡፡ ተማሪዎች ቢያንስ በሳምንት 3 ክፍለ ጊዜ ያላቸውን የአማርኛ ትምህርት አንዳንድ ቦታ እንዳይማሩ እንደሚደረግና በአማርኛ ክፍለ ጊዜም ሌላ ትምህርት እንዲማሩ መደረጉን የክልሉ አንዳንድ መምህራንና ተማሪዎች ዛሬም ድረስ ይናገራሉ፡፡ ለመምህራኑም ሌላ የቢሮ ስራ እንደሚሰጣቸውም በመጠቆም፡፡ ለተማሪዎቹ የሚነገራቸውም ምክንያት አማርኛን መማርና መናገር የበታችነት ነው ብለው በማመን እንደሚነግሯቸው ተማሪዎቹ ራሳቸው ይናገራሉ፡፡ ይህንን የሚያንፀባርቁትና የሚያራምዱት ደግሞ የኦህዴድ /ኢህአዴግ አመራሮች እንደሆኑ ይገለፃል፡፡ ይህ ግን የኦሮሚያ ልጆችን መጥቀም ሳይሆን መግደል ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው የአፍ መፍቻ ቋንቋዎችን ማወቅ ያን ሰው እጅግ ተጠቃሚና የበላይ ያደርገዋል እንጂ አይጐዳውም፡፡

ሌላው አማርኛ ቋንቋን አትማር ማለት አማራውን ለመጉዳት ነው ወይንስ ኦሮሞውን? ማንንስ ነው ተጠቃሚ የሚያደርገው? የኦሮሚያ ተማሪ አማርኛን መናገሩ ምን ክፋት አለው? የአማራ ክልል ተማሪስ ኦሮምኛን ጨምሮ ሌሎች ቋንቋዎችን ቢማርና ቢያውቅ ተጠቃሚ መሆኑን መግለፅ አላዋቂነት ነው፡፡

የሚገርመው የኦህዴድ /ኢህአዴግ ባለስልጣናት የኦሮሚያ ልጆች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው እንዳይግባቡ ማድረጉ እውነት ለኦሮሚያ ጥቅም ነውን? በኦሮሞ ስም እንደ አሸን የተፈለፈሉና የኦሮሞን ህዝብ ስቃይ የሚያራዝሙ "የፖለቲካ ፓርቲዎችስ" ምን እያራመዱ ይሆን?

በኦሮሞ ህዝብ ስም የሚነግዱ የኦህዴድም ሆኑ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ራሳቸው ኦሮምኛንና አማርኛን ጨምሮ ሌሎች ቋንቋዎችን አቀላጥፈው እየተናገሩ ኑሮዋቸውን እያቀለሉ መጪውን ትውልድ መግደላቸውን ሳያውቁት አይመስለኝም፡፡

ከተማሪ ሴና የተከሳሽነት ቃል እንደምንረዳው አማርኛን ባለማወቁ የማያውቀውን ሰነድ እንዲፈርም መገደዱ ብቻ ሳይሆን ይህ ወጣት ነገ ከዩኒቨርስቲ ተመርቆ ወደ ስራ ዓለም ሲሰማራ የግድ ኦሮምያ ክልል ውስጥ መገደቡን ያሳየናል፡፡ ሌላው ጥሩ የማስተዳደርና የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ኖሮት ሀገር መምራት ቢፈልግና ዕድሉ ቢሰጠው ከማን ጋ ተግባብቶ ነው የሀገር መሪ የሚሆነው? ወይንስ መጪው የኦሮሚያ ክልል ወጣት ተማሪዎች ለሀገራቸው ባዕድ እንዲሆኑ ታስቦ ይሆን? እዚህ ጋር ለኦሮሞ ህዝብ መብት እንቆረቆራለን የሚሉ "ፖለቲከኞች"፣ ተማሪዎችና ወላጆች መጪው ጊዜ ለአካባቢው ወጣቶች ምን ሊሆን

ወደ ገፅ 12 ይዞራል....

# ቆይታ

የዛሬ እንግዳችን ኤፍሬም ስዩም ይባላል፡፡ ኤፍሬም ደራሲ ሲሆን ከዚህ በፊት በተለይ በሙዚቃ መሳሪያ የታጀበ "ሶሊያና "የሚል የግጥም አልበም ለህዝብ ጆሮ አብቅቷል ፡፡ በቅርቡ ደግሞ "የብርሃን ክንፎች/ ሙዚቃል›› የሚል የግጥም አልበም ለህዝብ ያበቃ ሲሆን በስራዎቹ ዙሪያ ከባልደረባችን ብስራት ወ/ሚካኤል አጭር ቆይታ አድርጓል ፡፡

# የምኒሊክ አናት እና የሸሩባው ትንቢት ግጥሞች ትልቅ ትርጉም ይሰጡኛል

➢ **ኪነ ጥበብ ላንተ ምንድነው?**

በህይወት ውስጥ ያሉትን ሀዘኖች ፣ምሬቶች ፣መከፋቶች መቀየሪያ ነው፤ ወይም ደግሞ የመረረውን ማጣፈጫ ፤በሌላው አቅጣጫ መመልከቻ እና እሚከብደውን ማቅለያ ነው ፤ ወደ አንድ እውነት እና ሀሳብ መንገዣ መንገድ ድልድይ ነው ፡፡ ሌላው ወደ አንድ ዓለም ከሚታየው ወደ ማይታየው በኩል መመልከቻ ነው፡፡

➢ **የግጥም መድብልን በአልበም ደረጃ በማሳተም በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ነህ ልበል?**

ብዙዎች እንደዛ ይላሉ፤ ተቀድቶ በመቀመጥ ብዙ ይኖራል ፡፡ ነገር ግን በሙዚቃ መሳሪያ ታጅቦ ገበያ ላይ በመዋል የመጀመሪያ ነው ይላሉ፡፡

➢ **ከዚህ በፊት "ሶሊያና "የተሰኘ የግጥም አልበም ማሳተምህ ይታወቃል፡፡ ግብረ መልሱ እንዴት ነበር ?**

መልካም ነው ፡፡ ያው ኤፍሬም የሚባል ገጣሚ እንዳለ ከህዝብ ያስተዋወቀኝ ስራ ነውና ጥሩ ነው፡፡ በተለይ የእኔን አመለካከት ምን እደሚመስልም ያንጸባረቀ ነበር፡፡

➢ **በቅርቡ "የብርሃን ክንፎች "ለሚለው ግጥም አልበም ስራ አነሳስቶሀል ማለት ይቻላል ?**

አን፡፡ ሶሊያና ለብርሃን ክንፎች ድልድይ ሆኗል ፤ ባይሆንም አደርገው ነበር፡፡ ምክንያቱም የጀመርኩት ነውና፡፡

➢ **እስኪ "ሙዚቃል" ምንድነው ?**

የራሱ አቅራረብ ኖሮት ግጥም ከሙዚቃ ጋር ሲሰራ ያለ መጠሪያ ነው፡፡ ሙዚቃል ሙዚቃና ቃል ሲ"ጣመሩ የሚገልፅ ስሜት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ሙዚቃው እጣን ቢሆን ግጥሙ እሳት ወይም ግጥሙ እጣን ሲሆን ሙዚቃው እሳት ካልሆነ አንድ ክቡር መዓዛን አሊያም መልንም ሽታን ለማግኘት እጣኑ ብቻ በቂ አይደለም ወይም እሳቱ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ነገር ግን እሳቱና እጣኑ ሲዋሃዱ በተፈለገው ጊዜ መልንም መዓዛን ማግኘት ይቻላል፡፡

ስለዚህ ሙዚቃል የሙዚቃና የግጥም ውህደት የሚፈጥሩትንም ውጤት የብርሃን ክንፎች ብየዋለሁ፡፡

➢ **አዲሱ የብርሃን ክንፎች የግጥም አልበም ከሶልያና በምን ይለያል ?**

በግጥም አልበምነታቸው አንድ ቢሆኑም በይዘትና አቀራረብ ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ ሶሊያና የተሰኘው የግጥም አልበም በአንድ ፒያኖ ብቻ የተ ሰራ ሲሆን አዲሱ የብርሃን ክንፎች ግን በሙሉ የሙዚቃ ባንድ የተሰራ በመሆኑ ከሶሊያና ይለያል፡፡

➢ ግጥሞችህ ሲሰሙ ተፈጥኖርና ፍልሰፍና ላይ ያተኮሩ ይመስለኛል፤ እንዴት ነው?

ይሄ ግድ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ከሁለቱም መውጣት አንችልም፡፡ ተፈጥሮም ሆነ ፍልስፍና ከሌለ ግጥሙን መፃፍ እራሱ ከተፈጥሮና ከፍልስፍ ጋር ይቃረናል፡፡

ስለዚህ ህይወት እንዲኖረው ከፈጥሮ እና ረቂቅ ሐሳብ ወይም ፍልስፍና መውጣት ስለማይቻል ነወ ወደዛ ያተኮሩት፡፡

➢ **አዲሱ ስራህ ላይ ነፋስም መብት አለው ብለሃልና ምን ለማለት ታስቦ እንደሆነ ብትነግኝ፡፡**

በመጀመሪያ ደረጃ ነፋስም መብት አለው የሚለው ስለሰው ልጅ መብት ለመግለፅ አስቤ የሰራሁት ነው፡፡ ምክንያቱም ሰው በመሆንህ ብቻ የመናገርና ሐሳብን በነፃነት የመግለፅ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰዋዊ መብት እንዳለውና ማንም መከልከልና መገደብ እንደማይችል ለማሳየት ነው፡፡

➢ **ኤፍሬም አፍቃሪ ነው ልበል ? ምክንያቱም ፍቅርን የሚገልፁ ጸሁፎቹ በረቀቀ መልኩ አሉና ፤ እስኪ ትንሽ ብትነግረኝ፡፡**

አ አፍቃሪ ነው፡፡ የተነጠለ ፍቅር ግን የለውም፡፡ ለምሳሌ ኤፍሬም ለሀገሩ፣ ህዝቡ እና ለፆታዊ ፍቅር አለው፡፡ ፍቅር ከሌለ ሁሉም ከንቱ ነውና፡፡

➢ የምኒሊክ አናት የሚለው ግጥም ምንን ታሳቢ ያደረገ ነው?

የምኒሊክ ፎቶ ሁሌ ሳየው አንድ ነገር ልሰራ እንደምችል አስብ ነበር፡፡ በተ ለይ አናታቸው ላይ ያለው ጨርቅ ብዙ ያሳስበኝ ነበር፡፡ ነገር ግን እውነት ሆኖ ሴቶች ሻሽ ከማሰራቸው ጋር፣ ሰች ራሳቸውን ሲያማቸው ውሃ አርሰው ጨርቅ ያስራሉ፡፡ ዳግማዊ አጼ ምኒሊክም ያኔ በአድዋ ጦርነት ጊዜና ከዛ በኋላ ስለሀገር ጉዳይ ወይም ስለ ኤርትራ ጉዳይ ያማቸው እንደነበር ለመግፅ ነው፡፡ ስለዚህ ምኒሊክ ከአድዋ ድል ሲመለሱ የራስ ምታታቸው ጀምረ ለማለት ነው፡፡

➢ **የብርሃን ክንፎች ስራህን ማነው አሳትሞ ያከፋፈለልህ?**

ቮንል ሪከርድስ ድርጅት ነው፡፡

➢ ለስራህ ምን ያህል ተከፍሎሃል?

ክፍያ ነፍሳዊና ሥጋዊ ሲሆን በነፍሳዊ በኩል እጅግ በጣም ጥሩ ነው፣ በዚህም ደስተኛ ነኝ፡፡ ዋናው ነገር አንድ ስራ መስራትህ ነው፡፡ በስራው ከተደሰትክ በዋጋውም ደስተኛ ነህ ማለት ነው፡፡

➢ **በመፅሐፍ መልክስ የፃፍከው ስራ አለህ? ካለህ ብትጠቅስልኝ፡፡**

እስንአሁን የለኝም፡፡ በቅርቡ ግን በመፅሐፍ መልክ ለአንባቢያን የሚደርሱ ሥራች አሉኝ፡፡ በተለይ አንዳንድ ሐሳቦችን በጋዜጦች ላይ እየሰራሁ ነው፡፡ ለምሳሌ ግማሽ ቀን የሚል የአጭር ልብወለድ ስብስቦች ስራ አንዱ ነው፡፡ ሌላው ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር የሚለውና ሙሉ ታሪኩን ስናነበው አንድ ወጥ የሆነ ስራ እና 80 ያህል የተለየዩ የራሳቸው ሐሳብ ያላቸው ግጥሞች አሉኝ፡፡ አራተኛው በሲዲ ታትመው ለህዝብ ጆሮ የበቁት ሶሊያና እና



ኤፍሬም ስዩም

የብረሃን ክንፎች የሚለው የግጥም አልበም ውስጥ ያሉትም በመፅሐፍ መልክ ለአንባቢያን እንዲደርሱ ታስቧል፡፡

➢ **ለድምፃውያን የሰጠኸው ግጥምስ የለም ? ወይንስ አልሞከርክም?**

ለህዝቢ ጆሮ አልበቁም እንጂ አሉ፡፡ አንዳንድ ድምፃውያን ለሙዚቃ የሚሆን ግጥም ይጠይቁኛል፡፡ ስሰጣቸው ግን ይከብዳል ይሉኛል፡፡ እኔ ደግሞ ለህዝቡ ተራ ግጥም ፅፌ ማቅረብና ህዝቡን ማሳዘን አልፈልግም እንዳጂ የእውነት ሙዚቃና ግጥምን የሚረዳ ድምፃዊ ናለ መፃፍ እችላልሁ፡፡

➢ **ከግጥም ስራችህ መካከል ለእኔ የተለየ ነው የምትለው የቱ ነው?**

ለእኔ ሁሉም ስራቼ እኩል ናቸው፡፡ ነገር ግን አዲስ የግጥም አልበም ላይ የምኒሊክ አናት እና የሸሩባው ትንቢት ግጥሞች ለእኔ የተለዩ እና ትልቅ ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡

➢ **ለምን?**

ምክንያቱም እነኚህ ስራች ( የምኒሊክ አናት እና የሹሩባው ትንቢት) ገና ወደ ህዝብ ሳይደርሱ ከሌሎች አጫጭር ልብወለድ ታሪኮች በማላውቃቸው ሰች ተነጥቄ ተደብድቤባቸዋለሁ፡፡ ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ በግጥም ስራ የተደበደበ ኢትዮጵያዊ እኔ ሳልሆን አልቀርም፡፡ ስለዚህ ሁለቱ ግጥሞች ለእኔ የተለዩ ናቸው ፤ተ ፈትኜባቸዋለሁና፡፡ እነሱም በህይወቴ ውስጥ አንድ የተለየ ገጠመኝን ሰለጫሩ ለእነሱ የተለየ ስፍራ አለኝ፡፡ ስለዚህ ለእኔ የምኒሊክ አናት እና የሸሩ ባው ትንቢት ግጥሞች ትልቅ ትርጉም ይሰጡኛል፡፡

➢ **የተወሰደብህ ምክንያት ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?**

መገመት ቢያስቸግርም የቀናነት አስተሳሰብ አለመኖር እና እኔን ወደ ኋላ ለማስቀረት ይመስለኛል፡፡

➢ **የሸሩባው ትንቢት ምንድን ነው?**

የሸሩባው ትንቢት ምሳሌ፤ በአንድ ወቅት ኢየሱስ ክርስቶስን ብዙ-ች ሲከሱት፤ አንድን አጋንንት የሚያወጣው በሌላ አጋንንት ስም ነው አያሉ ነበር፡፡ ያኔ እናንተስ በማን ስም ነው አጋንንትን የምታወጡት? ሲል ከሳሹቹን ጠይቋቸዋል፡፡ ከዚያም የተ በታተነችና አንድነት የሌላት መንግስት አትፀናም፣ ትፈርሳለች ብሏቸዋል፡፡ የአጋንንት መንግስት እንኳ ቢሆን አንድነትና ህብረት አለው ፤ የክፋት ዓለም ሰራዊትም ቢሆኑ ለክፋትም ቢሆን ይተባበራሉ፡፡

ወደዚህ ወደ እኛ ዓለም ስንመጣ እርስ በርስ አንድነትና ትብብር የሌለው መንግስት እንደማይፀና እና እንደሚፈርስ ለማመላከት ነው የሸሩባው ትንቢትን የሰራሁት፡፡ ምክንያቱም እኛም ከአጋንንት ያነሰ ሥርዓት ፈጥረን የተበታተነ ሀሳብ ያለውን ህዝብና መንግስት መመስረት ናለመሻት የተነሳ የሰራሁት ነው፡፡

➢ **ለምን ?**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከአጼ ቴድሮስ በፊት የነበረችውንና ከዛ በኋላ ያለቸው ኢትዮጵያ የተለያየ መልክ አላት፡፡ የሰራሁትም በሀገራችን አንድነትና መተባበርን ለማሳየት ናለኝ ጉጉት የተነሳ ነው፡፡ ይህም አንድነታችንና ህብረታችን የማስመሰል ሳይሆን የእውነት ከልብ እንዲሆንም ስለምመኝ የሸሩባው ትንቢትን ፅፌያለሁ፡፡

ሌላው የአንድ ሀገር ታላቅነት የሚገለፀውም የነዋሪቹ ጠንንራ አንድነትና ህብረት ነው፡፡ አፄ ተድሮስም ቢሆኑ ለማንም ሳያደሉና ዜጐችን ሳይከፋፍሉ የሰለጠነ፣ ጠንካራ፣ የተ ከበረና ታላቅ አንድ መንግስትና ህዝብ ለመመስረት ጥረዋል፡፡ ስለዚህ እኔም ይህን ግጥም ልፅፈው ግድ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም እኳን ሰው የመላእክትም ሆነ የሰይጣን ዓለም ነዋሪዎች ህብረትና አንድነት አላቸውና፡፡

➢ **ወደፊት ከኤፍሬም ምን እንጠብቅ?**

የተሰጠውንና የተገለጠለትን ለህዝብ እንደሚያቀርብ መጠበቅ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በጊዜና በይዘት ዘርዝሮ መናገሩ ያን ያህል አስፈላጊ አይመስለኝም፡፡

➢ በመጨረሻ መናገር የምትፈልገውና የቀረ ነገር ከለ ዕድሉን ልስጥህ፡፡

በቅድሚያ እዚህ ላደረሰኝ ፈጣሪ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠልም ለእናቴ፣ ለጓደኞቼና ሥራዬ ወደ ህዝብ እንዲደርስ ለጣሩና ስራ-ቼንም አድምጠው አስተያየትና ድጋፍ ለሰጡኝም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም እንግዳ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

# የብርሃንና ሠላም ማተሚያና የአሳታሚዎች ውይይት በድጋሚ ተቀጠረ

ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ለአሳታሚዎች ባዘጋጀው የውል ሰነድ ላይ የተጀመረው ውይይት መቋጫ ባለማግኘቱ በድጋሚ መቀጠሩን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡ የመረጃ ምንጮቻችን እንደሚሉት "ብርሃንና ሰላም የይዘት ለውጥ ሳያደርግ የቃላት ለውጥ በማድረግ ኢ. ህገመንግስታዊ የሆነውን ሰነድ በድጋሚ ይዞ በመቅረቡ ከአሳታሚዎች ጋር መግባባት አልተቻለም" ሲሉ ይናገራሉ፡፡ "ማተሚያ ቤቱ በህገ መንግስቱ የተከለከለውን ቅድመ ምርመራ በተዘዋዋሪ በውል ሰነድ ላይ በማስቀመጥ የፕሬስ ነፃነትን በመግፈፍ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታውን አደጋ ውስጥ የሚከት አደገኛ አካሄድ በመሆኑ መግባባት ላይ መድረስ አልተቻለም" ሲሉ በቅሬታ ይገልጹታል፡፡

ባለፈው ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም በተደረገው ውይይት የፍኖተ ነፃነት፣ የፎርቹን፣ የሪፖርተር፣ የካፒታል፣ የአዲስ አድማስና የነጋድራስ ጋዜጣ ተወካዩች ተገኝተው ነበር፡፡ ምንጮች እንደሚሉት "በጋራ በመሆን በውል ሰነዱ ላይ 11 ገጽ የህግ ባለሞያ አስተያየት ከማቅረባቸውም በላይ በውሉ ላይ እንድንፈርም የምንገደድ ከሆነ እንደ አሳታሚ በውሉ ላይ እንዲካተትልን የምንፈልገው 3 ገጽ ዝርዝር አቅርበናል፡፡ ማተሚያ ቤቱ ያቀረብነውን የህግ ባለሞያ አስተያየትና የውል ሐሳብ መርምሮ ወደፊት ስብሰባ ለመጥራት ስምምነት ላይ ተደርሶ የዕለቱ ውይይት ተጠናቋል" ተብሎአል፡፡

የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ወክለው በስብሰባው ላይ የተገኙትን የአንድነት ፓርቲ ዋና ፀሐፊ አቶ አስራት ጣሴን እስከአሁን በተደረገው አጠቃላይ ውይይት አስተያየት እንዲሰጡን አነጋግረናቸው ነበር፡፡ ለአቶ አስራት ያቀረብንላቸው ጥያቄ ከብርሃንና ሠላም ጋር አሻሽሎ ባቀረበው ውል ላይ መግባባት ያልቻላችሁበት ነጥብ ምንድነው በማለት ጠይቀናቸው በሰጡን መልስ "በውሉ ላይ በቀጥታ የቅድመ ምርመራ ይዘት ያለው በውል አንቀጽ 10.1 ላይ የተጠቀሰው ጽሑፍ ህግን የተላለፈ ከሆነ የሚለውን ከባድ ወንጀል ስለመሆኑ ከተረጋገጠ በአንቀጽ 10.2 የወጣው ጽሑፍ በተደጋጋሚ ህገ ወጥነቱ በማስረጃ ከተረጋገጠ አታሚው ውሉን ያቋርጣል ይላል፡፡ ውሉ ተራ ጉዳይ አይደለም፡፡ መብትንና ነፃነትን የሚገፍ ነው፡፡ የፕሬስ ነፃነት ጉዳይ ነው፡፡ የፕሬስ ነፃነት ደግሞ ማንም ለማንም የማይሰጠው ማንም ከማንም የማይገፈው ሰው በተፈጥሮው ያገኘው መብት ነው፡፡ ይዘቱን ሳይቀይሩ በቃላት መጫወት በህዝብና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው ላይ ማሾፍ ነው፡፡ አንድ ኃላፊነት ከሚሰማው አንጋፋ ተቋም አይጠበቅም፡፡ ያልታተመ ጽሑፍ እንደመገናኛ ፕሬስ ውጤት አይቆጠርም፡፡ ለፕሬስ ልዩ ጥበቃ ይደረግለታል የሚለውን ህግ ይቃረናል" ሲሉ መልሰዋል፡፡

በማያያዝም አቶ አስራት ጣሴ ሲናገሩ "የውሉ ረቂቅ ኢትዮጵያ በህገመንግስት ያፀደቀችውንና ፈርማ የተቀበለችውን ዓለም አቀፍ ህጐች የሚጥስ ነው፡፡ ብርሃንና ሠላም ሊወስድ የፈለገው ሥልጣን በህግ ለዐቃቢ ህግ ያልተሰጠ ስልጣን ነው፡፡ በህግ ጽንሰ ሐሳብ አንድ ውል ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው 1 ህጋዊ ሲሆን 2. ሞራላዊ ከሆነ 3ኛ የሚቻል ሲሆን ነው፡፡ ብርሃንና ሠላም ያዘጋጀው ውል ግን ህግን የሚጥስ ስለሆነ ሁለተኛ የማይቻል ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምናልባትም ይህንን ህገወጥ ውል እጃችንን ጠምዝዞ ለማስፈረም ከማተሚያ ቤቱ ጀርባ ረጃጅም እጆች ያሉ ይመስለናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ውል ላይ መፈረም ህገወጥ ስለሚያደርግ በምንም መልኩ አሳታሚዎች መፈረም የለባቸውም የሚል እምነት አለኝ" በማለት ይናገራሉ፡፡

ብርሃንና ሠላም የውሉን አንቀጾች አልሰርዝም ብሎ የሚቀጥልበት ቢሄድ አሳታሚዎች ምን አማራጭ አላቸው በማለት የጠየቅናቸው አቶ አስራት ሲመልሱ "ይኸ የመጨረሻው አማራጭ ነው፡፡ እኛ አሁን የምናምነው በህጋዊነት ነው፡፡ ማተሚያ ቤቱ ለህግ ተገዢ ሆኖ የውሉን ሰነድ ያስተካክላል የሚል ተስፋ አለን" ሲሉ መልሰዋል፡፡

## ‹‹ነፃነት በሌለበት አገር ...

ከ ገፅ 1 የዞረ....

ደጋፊና ተቃዋሚ አለመሆናቸውን አስምረውበት የሙያ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ተጋብዘው መምጣታቸውን በመግለጽ የውይይቱን መነሻ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡ ሠፊ የሆነውን የሞያ ትንተና የሰጡት ሁሉም ታዋቂው የኪነጥበብ ባለሞያ አያልነህ ሙላት ነው፡፡

ፀሐፊ ተውኔት ገጣሚና ደራሲ አያልነህ ሙላት እንዳለው « የኪነ ጥበብ መለኪያው እውነትና ውበት ነው፤ ኪነጥበብ የሚያንፀባርቀው የሰው ልጅ በዘመኑ ያፈራቸውን ነው፤ ኪነጥበብ የሚኖረው በራሱ በህብረተሰቡ ውስጥ ነው፤ ኪነጥበብ ያለ ህብረተሰብ ዋጋ የለውም፤ በነፃ ህብረተሰብ ውስጥ ኪነጥበብ ያድጋል» ካለ በኋላ እያንዳንዱን ነጥብ በመተንተን አስረድቷል፡፡ ሌሎች የኪነጥበብ መለኪያ ያላቸውን ነጥቦች ዘርዝሯል፡፡ በማያያዝም አንጋፋው የኪነጥበብ ባለሞያ አያልነህ « የኪነጥበብ ሚናዋ ምንድነው?» የሚለውን ጥያቄ ካነሳ በኋላ ሲመልስ «ኪነጥበብ የልማትና የእድገት ማምጫ መሣሪያ፤ የህብረተሰብ ሃያሲ ከመሆኑም በላይ የጠንካራ ህብረተሰብ መሠረቱ ኪነጥበብ ነው» ብሏል፡፡ «የሚንቀሳቀስ ህብረተሰብ የሚንቀሳቀስ ኪነጥበብ ይፈጥራል፡፡» የሚለው አያልነህ «የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋና ባህል በአንድ ምቹ ግቢ ውስጥ የተለያዩ ቀለማት ያሏቸው አበቦች ተተክለውና ፈክተው ሲታዩ ውበታቸው ተመሳሳይ ነው፡፡» ስል ገልፆታል፡፡

በመቀጠል ማብራሪያውን የቀጠለው ደራሲ አበረ አዳሙ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ተጋብዞ መምጣቱን፣ ማህበሩ ከማንም የማይወግን ማንንም የማይደግፍ ማንንም የማይቃወም ማህበር መሆኑን በመግለጽ ንግግሩን ቀጥሎአል፡፡ ደራሲ አበረ እንዳለው «ኪነጥበብ ትንቢት ተናጋሪ ነው፡፡ ሐዲስ አለማየሁ በትንቢት የገለፁት አበጀ በለው እና ፊታውራሪ መሸሻ አንድ አርሶ አደር የአካባቢውን የፊውዳሉን ባለስልጣናት ሰብስቦና አስሮ ለፍርድ ያቀረበበትን ሂደት» አብራርተዋል፡፡ የኪነጥበብ ባለሞያ ደራሲና የህግ ባለሞያው አበረ አዳሙ እንደዘረዘረው «ሥነ ጥበብ ውበትም ሀብትም ነው፡፡ ወጣቱ በኪነጥበብና በራሱ ህይወት ውስጥ ከመኖር ይልቅ በአውሮፓ እግር ኳስ ደንዝዟል፡፡ የእኛ ቡድን ተሸነፈ፡፡ በእኛ ቡድን ላይ እንዲህ የለ ነገር ተፈፀመ እያለ ጓደኛውን ይደበድባል፡፡ ይገላል፡፡ የእኛ ቡድን ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፡፡ ወጣቱ ወደ ራሱ ማየት አለበት፡፡ ኪነጥበብ ፍቅር ነው፡፡ ኪነጥበብ የመንግሥት ወይም የዜግነት ጉዳይ ሳይሆን የህብረተሰብ ጉዳይ ነው» ብሎታል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የሞያ ልምዱን ያካፈለው ተዋቂው ቀራጺ በቀለ መኮንን ነው፡፡ ቀራጺ በቀለ «ኪነጠበብ እንዳይጠወልግ መጮህ ያስፈልጋል፡፡» በማለት ንግግሩን የጀመረው ቀራጺ በቀለ« ሥልጣኔ ለማምጣት ቁሳዊ ሀብት ብቻውን ውጤት የለውም ቅድሚያ የአእምሮ ነፃነትና የኪነጥበብ እድገት አስፈላጊ ነው» ብሎአል፡፡

በመጨረሻ የሞያ ልምዱን ያቀረበው አንጋፋው ሠዓሊ እሸቱ ጥሩነህ ነው፡፡ ሠዓሊ እሸቱ እንዳለው «ኪነጥበብ ወገንተኛ አይደለም ወሰን ወይም ገደብ የለውም ድንበር ተሻጋሪ ነው፡፡ መጠፎ ሰውና ኪነጥበብ የተገናኙ እለት ኪነጥበብ ይሞታል፡፡ ኢህአዴግ ሲገባ ጥላሁን ገሠሠ ተወግዞ ነበር፡፡ ባድሜ ላይ ሲዘፍን ግን ተወደሰ፡፡ አፈወርቅ ተክሌ ደረግ ሥልጣን ሲይዝ ተወገዘ ትንሽ ቆይቶ ተወደሰ፡፡ በመጨረሻ ክብር አግኝቶ ሞተ፡፡ በዘመኑ ተፈጥሮ በዘመኑ የሚሞት ፕሮግንዳ ብቻ ነው፡፡ ኪነ ጥበብ ዘላለማዊ ነው፡፡ የእድገት መንገድ ጠፍቶ ውድቀት የሚመጣው አባት ልጅን፤ ልጄ የሚያስበው ትክክል አይደለም፤ ልጅ አባቱን፤ አባቴ የሚያስበው ትክክል አይደለም፤ ብሎ ማሰብ ሲጀምር ነው» ብሎአል፡፡

ከፍተኛ የሆነ የታዳሚ ተሳትፎ የታየበት መድረክ ነበር፡፡ ታዳሚው በርካታ አስተያየቶችና ጥያቄዎችን አቅርቦ ከመድረኩ መልስ ተሰጥቶአል፡፡ ታዳሚው በአብዛኛው በሰጠው አስተያየት « ኪነጥበብ ህዝብን ከፍርሃት ማላቀቅ አለበት፡፡ ኪነጥበብ የእውነትና የህብረተሰብ ወገን ወገንተኛ ሊሆን ይገባል፤ በአገራችን ውስጥ ዝምታ ሰፍኗል፡፡ ያለንን እያጣን የሰውን እየቀላወጥን ነው፤ ሚዲያው ስለ አባይ ግድብ ብቻ ሳይሆን» ( ሳይጠብቅ) ስለ አባይ ግድብም ይንገረን ነፃነት በሌለበት ህብረተሰብ ውሰጥ ኪነጥበብ እድገትና ህይወት የለውም፡፡ ሲሉ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ ተሰብሳቢው በመጨረሻም አንድነት ፓርቲ አዳራሽ ተከራይቶ ባለሞያዎችን አሰባስቦ ይህንን የመሰለ ውይይት ማድረግ በመቻላችን እናመሠግናለን፤ ሲሉ አስተያየታቸውን የሰጡ ሲሆን መድረኩን የመሩት ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በበኩላቸው ተጋባዥ የኪነጥበብ ባለሞያዎችን ታዳሚውንና አዳራሹን በመፍቀድ ትብብር ያደረገውን የብሔራዊ ትያትርን በማመስገን ፕሮግራሙን አጠናቀዋል፡፡

የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነቱም ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያላት ኪነ-ጥበብ አንድ አንጓዋ በሆነው ልማት ብቻ ተቀይዳ መታሰሯ እንደሚሳስበው ጠቅሶ ኪነ-ጥበብ ነፃነቷን እስከምትቀዳጅና የህዝብ አንጡራ ሀብት እስከምትሆን ድረስ ተመሳሳይ ውይይቶችን ክርክሮችን በማዘጋጀት እንደሚቀጥልበት የደረሰን መረጃ ይጠቁማል፡፡

## የነዋሪውና ተላላፊው ምሬት ጨምሯል

ብሩክ ከበደ

በቀድሞው አወቃቀር በከፍተኛ 4 ቀበሌ 29 በተለምዶ ከመርካቶ ደቡባዊ ጫፍ ከሚገኘው ጭድ ተራ እስከ ጌጃ ሠፈር በሚያካትተው መንደር የሚኖሩ ነዋሪዎች `ቀን በቀማኞች ማታ በዘራፊዎች መውጫ መግቢያ አተናል` ሲሉ አንዳንድ ነዋሪዎች ለጋዜጣው ዝግጅት ክፍል አቤቱታቸውን አቀረቡ፡፡

እንደ ግለሰቦቹ አባባል ከሆነ በጭድ ተራ አድርጐ በዶቢ ሠፈር በኩል የሚያልፈው መንገድ ከልደታና ለአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ ወደ መርካቶ ለሚያቋርጡ የሚመረጥ በመሆኑ "ገንዘብ፣ ሞባይል፣ የሀብል ነጠቃ ተጧጡፎበት ይገኛል" ካሉ በኂላ "በመንደሩ የሚኖሩ ታዳጊዎችም በዚሁ ንጥቂያና ዝርፊያ ላይ ከአጐራባች ቀበሌዎች ከሚመጡ ጓደኞቻቸው ጋር ተጣምረው ስለሚያከናውኑ ችግሩን የከፋ አድርጐታል" ብለዋል፡፡

የአካባቢው ነዋሪም የጉዳዩን አሳሳቢነት ለፖሊስና ለኢህአዴግ የተለያዩ አደረጃጀቶች አቤት ቢልም ምላሽ ባለማግኘቱ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም በቀበሌ 29 አዳራሽ በመሰብሰብ ምሬቱን አሰምቷል፡፡ በተለይም ለፖሊስ ወንጀለኛውን ከጠቆምን በኂላ አንዳንድ ምግባረ ብልሹ አባላት የጠቋሚውን ስም ለተጠርጣሪው በመንገር ህይወታችንን አደጋ ላይ ጥለውታል የሚለውን ቅሬታ አስደንጋጭ እንደነበር አቤት ባዮቹ ይናገራሉ፡፡

በስብሰባው መጨረሻም በቀበሌ ውስጥ አንድ ግለሰብ ቤቱን ለዲኤስ ቴቪ ማሣይ በሚል ለአንዲት ግለሰብ በያከራይም ግለሰቧ ቁማር የሚቆምርበት፣ ሐሺሽ የሚጨስበት በታዳጊና ወጣቱ የሚበላሽበት በመሆኑ እንዲታሸግ ተወስኖ ውሣኔው ተግባራዊ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ቤት ከመታሸጉ በፊት ህብረተሰቡ ፊርማ አሰባስቦ ለፖሊስ ማስረከቡን የሚናገሩት ነዋሪዎች ፖሊስ በቤቱ ላይ አፋጣኝ እርምጃ ባለመውሰድ ነዋሪው በአንድ ላይ ለመሰባሰብና ለመወሰን መቸገሩን ገልፀዋል፡፡

## ኮንግረስማን ክሪስ ስሚዝ አቶ መለስ በቡድን 8 ጉባኤ መገኘታቸውን አወገዙ

ባለፈው ሳምንት በአሜሪካ በተጀመረው የቡድን ስምንት ሀገራት ጉባኤ ላይ አቶ መለስ ዜናዊ መገኘታቸው ከጉባኤው አላማ ጋር ይቃረናል በማለት የአሜሪካ ኮንግረስ የአፍሪካ የአለም ጤና እና የሰብአዊ መብቶች ንኡስ ኮሚቴ ሊቀመንበር ክሪስ ስሚዝ አወገዙ፡፡

የኒውጀርሲው ኮንግረስማን ክሪስዝሚስ አርብ ዒት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደገለፁት ፕሬዝዳንት ኦባማ የቤኒን፣ የጋና እና የታንዛኒያን መሪዎች ጋር በመሬት ቅርምት እና በሰብአዊ መብት ጥሰት የሚኮነኑትን ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ መጋበዛቸው ከጉባኤው መንፈስ ጋር አይሄድም፡፡ የአቶ መለስ በ1997 በሰላማዊ ተቃዋሚዎች ላይ በፈፀመው ግድያ እና በሰፊው በሚያካሄደው የሰብአዊ መብት ረገጣ ምክንያት ማእቀብ እንዲጣልበት የሚያስችል ረቂቅ አቅርበው እንደነበር ያስታውሱት ኮንግረስማኑ በአሁኑ ወቅት የአቶ መለስ መንግስት ከሰብአዊ መብት እረገጣ ባለፈ ለውጪ ባለሀብቶች የእርሻ መሬት ለመስጠት የገዛ ዜጐቹን በማፍለስ ላይ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ አክለውም በዚህ ስብሰባ ላይ አቶ መለስ መገኘታቸው በኢትዮጵያ ካለው የመሬት ፖሊሲ አንጻር የጉባኤውን አላማ እንደሚፃረር አመልክተዋል፡፡

ኢትዮጵያ በቡድን ስምንት ጉባኤ ላይ መካተት የሚገባት አቶ መለስን ኢትዮጵያውንን ስለሚያስተዳድሩበት ተቀባይነት የሌለው አያያዝና ዜጐቻቸው በምግብ እራሳቸውን እንዳይችሉ ስላደረጋቸው ፖሊሲያቸው ለመሞገት ቢሆን ስሜት ይሰጥ ነበር ብለዋል፡፡

የኮንግረስማኑ ጋዜጣዊ መግለጫ ጨምሮም በቅርቡ የወጡ የሰብአዊ መብት አያያዝ ሪፖርቶች የኢትዮጵያ መንግስት ከ70,000 በላይ ዜጐችን በግዳጅ ወደ ሌላ ቦታ ማፍለሱን እንዲሁም 5,000 አኝዋኮች ወደ ኬንያ መሰደዳቸውን እና 8,000 ያህሉ ደግሞ ወደ ደቡብ ሱዳን መሰደዳቸውን አስታውሷል፡፡

## አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር ህክምና ማግኘት አለመቻላቸው ተገለፀ

በቃሊቲ ማረሚያ ቤት በእስር ላይ የሚኙት የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ/ኢብአፓ/ ፕሬዚደንት አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር ባደረባቸው ህመም ህክምና ማግኘት አለመቻላቸው ተገለፀ፡፡ ቤተሰቦቻቸው ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት ከሆነ «አቶ ዘሪሁን ከአንገት በላይ በተፈጠረባቸው ህመም በማረሚያ ቤቱ ክሊኒክ ታክመው ስለአልተሻላቸው ክሊኒኩ ወደ ሆስፒታል ሪፈር ብሎአቸው ነበር፡፡ ሆኖም ግን ሪፈር ከተሰጣቸው ከአንድ ወር በላይ ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ ወደ ህክምና አልተላኩም፡፡» በማለት በቅሬታ ገልፀዋል፡፡

የአቶ ዘሪሁን ቤተሰቦች እንደሚሉት «መጀመሪያ አካባቢ አይኑን አሞት ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ራሴን ያመኛል ይላል፡፡ በህመም እየተሰቃየ ይገኛል፡፡ ሪፈር ወደተባለበት ሆስፒታል እንዲያደርሱት ሲጠይቅ መኪና የለም፤ አጃቢ አልተገኘም፤ እየተባለ ህክምና ማግኘት አልቻለም፡፡» በማለት በሐዘን ይናገራሉ፡፡ በጉዳዩ ላይ የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር አስተያየት እንዲሰጥበት ያደረግነው ጥረት ለጊዜው አለተሳካም፡፡

# ከችሎት ...

ከ ገፅ 9 የዞረ....

እንደሚችል ከወዲሁ ማጤን ያለባቸው ይመስለኛል፡፡

ልክ እንደ አዲስ ነገር ጋዜጣ ዛሬ እኔም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የሚመሩ እንቁ ልጆች ከኦሮምያ፣ ከደቡብ፣ ከጋምቤላ፣ ከሶማሌ፣ ከአፋር ወይንም ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ይኖራሉ ብዬ አምናለሁ፡፡

በእርግጥ አንድ የማይካድ ነገር አለ፡፡ ማንም ሰው ወይም ተወላጅ የአካባቢውን (የራሱን) ባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክንና ወግ ማሳደግና መጠበቅ ተገቢ ነው፡፡ የሌላውንም ቢሆን እንዲሁ፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው የራሱን መከበር ሲፈልግ መጀመሪ ራሱ ራሱን ማክበር እና ለሌሎች ሰዎችም ክብር መስጠት አለበትና፡፡ አለበለዚያ የሱን መብት ብቻውን እንደያዘ ሳይከበርና ሳያስከብር ይቀራል፡፡

ምናልባት ተማሪ ሴና መረራ አማርኛን አለማወቁ በግድም ይሁን የማያውቀውን ሰነድ ከመፈረም አላገደው ይሆናል፤ ከዚህ የባሰ ችግር ቢመጣስ? አማርኛን እንዳያውቅ መደረጉስ ምን ጠቀመው? ጓደኞቹ የመጪ ተስፋቸውን እውን ለማድረግ የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን ሲገፉ የነገ የሀገሪቱ ተስፋ የሆነው ወጣት ሴና ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ላልተወሰነ ጊዜ ቃሊቲ ማረሚያ ማረፊያው ሆኗል፤ የጓደኞቹ ትምህርት ግን ቀጥሏል፡፡ ይሄኔ ወላጆቹና እህቶች ሴና ተምሮና ተመርቆ ለእነሱም ሆነ ለሀገር አለኝታ ሆኖ ይደርሳል በሚል እየጠበቁት ይሆናል፤ እሱ ግን ዛሬ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ሆኖ ፍርዱን ይጠባበቃል፡፡

በወጣቱ የወደፊት ብሩህ ተስፋ የፈረዱ የመብቶቻቸው ተሟጋች የመሰሉ "ፖለቲከኞችም" የራሳቸውን የጣፈጠ ኑሮ እያጣጣሙ በጠባብ ማዕድ ውስጥ አጕረውታል፡፡ ልክ እንደ ወጣት ሴና ሁሉ ብዙ ወጣቶች በተመሳሳይ መልኩ እየማቀቁ ይሆናል፡፡ የበለጠ ግን እንደኔ በስራ አጋጣሚ ለመታዘብ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት ከመታዘብ አስበውት ቢታዘቡ ብዙ ያያሉና ጋብዣችሁ የዛሬ ትዝብቴን በዚህ አበቃሁ፡፡

# ኢትዮጵያዊነት ትናንት ...

ከ ገፅ 6 የዞረ....

በህዝባቸው ልብ ውስጥ ያኖሩ በመሆናቸው፤ ማንዴላ ደግሞ ለደቡብ አፍሪካ ጥቁር ህዝቦች ነፃነት ዘመናቸውን በሮቢን ደሴት ቢያሳልፉም፣ ለስልጣን ሲበቁም የጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን የበቀል ጐራዴዎች ወደ የሰገባቸው እንዲገቡ አድርገው ጥቁሩን ከነጭ ያስታረቁ፣ ሕዝብ እየወደዳቸው ስልጣናቸውን በገዛ ፍቃዳቸው ያስረከቡ በመሆናቸው ነበር፡፡ እንዲህ ነው አርቲስትነት! በሞቀበት ማሽቃበጥን ኪነጥበብ ትጠየፋለችና፡፡

ጥንት አያቶቻችን አንድነቷና ሉዓላዊ ግዛቷ የተጠበቀችን አገር ለትውልድ ለማሻገር በብርቱ ጥረዋል፡፡ ኢትዮጵያዊነት ኩራታቸውና መለያቸው ነበር፡፡ አገርን የሚቆርስ የባዕድ ወራሪ ሲመጣ ሴቱ ወንዱ ተጠራርተው የሕይወት መስዋዕትነትን ከፍለዋል፡፡ የአገራቸውን ጉዳይ ለድርድር አያቀርቡም ነበር፡፡ ባንዲራዋም ፅኑ አርማቸው ነበር፡፡ ከመመገቢያ ቁሳቁሳቸው እስከ አልባሳቶቻቸው በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለማት ያሸበረቁ ነበሩ፡፡ የቀኝ ገዢዎችን ቅስም በመስበር ኢትዮጵያን የጥቁር ህዝቦች ተምሳሌት አድርገዋታል፡፡ ከአብራካቸው ለሚከፈለው ትውልድ አገርን ለማውረስ በፅኑ መሠረት ጥለዋል፡፡

## እኛና የዛሬዋ ኢትዮጵያ

የዛሬው ትውልድ ዛሬን ህልው ሆኖ እንዲኖር የትናንትናዋ ኢትዮጵያ ዛሬም እንደ ትናንቱ ምሉዕ ሆና ልትቆም ይገባል፡፡ ምሉዕ እንጂ ግማሽ ዜግነት እጣ ፈንታችን ሊሆን አይገባም፡፡ ካለፉት አራት አስርት አመታት ጀምሮ ግን ኢትዮጵያዊነት ፈተና ሆኖብናል፤ የወታደራዊው ደርግ አምባገነን መሪዎች የዜጎችን ደም እንደ ጅረት አፍሰው ህዝቡን የሀዘን ከል አለበሱት፡፡ አገሩን ጥሎ ባህር ማዶ መሄድን እንደ ውርደት የሚቆጥረው ዜጋ ለባዕድ አገር የእንግልት ኑሮ ተዳረገ፡፡ ረሀብና ቸነፈር የአገራችን ልዩ መታወቂያዎች ሆኑ፡፡ የሕዝብን የልብ ትርታ ማድመጥ የተሳነው ደርግ የራሱን የስልጣን ዘመን ለማራዘም ሲታትር በዛሬዎቹ የቤተ መንግስት ሹመኞች በማይታሰብ ሁኔታ ተንኮታኩቶ፣ የእ/ር ቃል "ጅማሬህ ታናሽ ቢሆንም ፍፃሜህ ታላቅ ይሆናል" እንደሚለው በጣት የሚቆጠሩ የደደቢት በረሀ ሽማቂዎች በዓላማ ፅናት ታግለው በማሸነፍ መንግስት ከሆኑ ድፍን 21 ዓመት ሊሞላቸው የቀናት ዕድሜ ቀረቷቸዋል፡፡

አቶ መለስ ዘወትር በሚቀዱት ቦይ የሚፈሰው ኢህአዴግ ገና ከመነሻው ኢትዮጵያዊነትን አራከሰው፡፡ ያለፉትን ነገስታት ጥቃቅን ስህተቶች እየነቀሰ በማጉላት የህዝቡን ስሜት በጥላቻ ሞላው፡፡ ለከፋፍለህ ግዛው እኩይ ዓላማው መሣካት በዘር እና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ የክልል መንግስታትን በማዋቀር የልዩነት መርዝን ረጨ፡፡ ኦሮሞው አማራውን፣ ትግሬው ኦሮሞውን እንዲኮንነው ሁኔታዎችን አመቻቸ፡፡ በተለይም ‹‹ያለፉት ነገስታት የወጡት ከአማራው ብሄር ነው›› በማለት ሌሎች ብሔረሰቦች አማራን በነፍጠኝነት እየፈረጁ እንዲያወግዙት የተከፈተው ዘመቻ ኢትዮጵያዊ አንድነትን ሸረሸረ፡፡ በህገ መንግስቱ ላይ የሰፈረው አንቀፅ 39 ዛሬም በማስፈራሪያነት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የዘር፣ የሀይማኖት፣ የቀለም፣ የባህል ልዩነቶቻችን ውበታችን መሆን ሲገባው መለያያችን ሆኗል፡፡ ዛሬ ትውልዱ ለጋብቻ እንኳን ዘር መቁጠር ጀምሯል፡፡ ባንድ ወቅት አንድ ወጣት የኦሮሞ ልጅ አንዲት ከአማራ ብሄረሰብ የተወለደች ጉብል አፈቀረና ለጋብቻ ደረሱ፡፡ እኔም ወግ ደርሶኝ የነገር አባት ሆኜ ሽምግልና ተላክሁ፡፡ ሁኔታዎች በስምምነት ከተቋጩ በኋላ የአግቢው የቅርብ ጓደኞች ከአማራ ተወላጅ ማግባቱ ከንክኗቸው ኑሮ በቁም ነገር ጠርተውት "ወደ ፊት ኦሮሚያ ስትገነጠል ይህችን ሴት ምን ታደርጋታለህ?" ሲሉ እንደጠየቁትና እሱም "ኦሮሚያ ለመገንጠል ያብቃት እንጂ ወቅቱ ሲደርስ የምወስነውን እወስናለሁ" በማለት እንደመለሰላቸው አጫውቶኛል፡፡ ዛሬ አያሌ ኢትዮጵያውያን ከባህር ማዶ ዜጎች ጋር ትዳር መስርተው እየኖሩ እያየን የዘመናችን መሪዎች በረጩት የመከፋፈል መርዝ ተመርዘን የዘር ሀረግ እንመዛለን፡፡

ህወሓት መራሹ ኢህአዴግ የፌዴራሊዝም አወቃቀር ጭምብል አጥልቆ በዘር ላይ ያዋቀራቸው ክልሎች ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ ሲያደርግ ከበስተጀርባ እነ በላይ ቢተው እና ሰለምን ጢሞን የመሣሰሉ የትግራይ ብሄር ተወላጆች በሞግዚትነት ተመድበውላቸው እንደነበር የማያውቅ ኢትዮጵያዊ የለም፡፡ እንደ ቀድሞው በገሀድ ባይሆንም ከመጋረጃው በስተጀርባ ምግዚትነቱ አሁንም እንዳለ ነው፡፡ ይህ አካሄድ አይደለም በክልል ደረጃ በመንደርና በቀጠና ደረጃ ሳይቀር ሳይቀር ስር ሰድዷል፡፡ በገዛ አገራችን እርስ በርሳችን እንዳንተማመንም ተደርገናል፡፡

ውድ ኢትዮጵያውያን የዛሬዋ ኢትዮጵያ ለጥቂቶች እናት ለእኛ ደግሞ ከፉ የእንጀራ እናት ከሆነች ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ ዛሬ ድህነትና እጦት ቤታችን ገብቶ ስቃያችን በዝቷል፡፡ ጠግቦ መብላት አይታሰብም፡፡ ጤነኛ አካል ኖሮት የሚለምነው ሰው ቁጥር ከእለት እለት እየጨመረ ነው፡፡ ከኑሮ ውድነቱ መከፋት የተነሣ ጦሙን የሚያድረውን ህዝብ ቤት ይቁጠረው፡፡ ጥቂቶች ከሥርዓቱ ጉያ ሥር የተወተፉ ሹማምንት የምዕራቡን ዓለም የቅንጦት ኑሮ ሲኖሩ እኛ ከጣሉት የምግብ ትራፊ ውስጥ እየኳተንን ‹‹ኢኮኖሚው አድጓል ተመንድጓል›› እንባላለን፡፡ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የምንኖር ያላየነውን ጥጋብ እንጂ ጎረቤታችን ስለሆነው ችግር እንድናወራ አይፈቀድልንም፡፡ የወገኖቻችን ስደት ከአመት አመት ቁጥሩ እየጨመረ መጥቶ ኢትዮጵያውያን የአለምን ሪከርድ ጨብጠናል፡፡ ኤርትራ ተገንጥላ የአገራችን ካርታ አንገት የሌላት ወ/ሮ ከመሰለች በኋላም ከመቆራረስ የቦዘነችበት ጊዜ የለም፡፡ በአራቱም አቅጣጫ ተንጣሎ የሚገኘው ለም መሬት እጅግ በሚያስቆጭ ሁኔታ ለባህር ማዶ ዜጎች እየተቸበቸበ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያውያን በተለይም ከደቡብ ህዝቦች ክልልና ከአማራ በመሬት ጥበት ምክንያት የሚያርሱት መሬት አጥተው ሲኳትኑና ወደ ከተማ ሲፈልሱ እየታየ ለሳውዲ አረቢያ እና ለህንድ ገበሬዎች የሥራ እድል መፍጠር ምን የሚሉት ኢትዮጵያዊነት ነው?

## የኢቴቪ ኢትዮጵያ

ከሰማይ የወረደች የምትመስል አረንጓዴ፣ ለምለም እንደ ሰማያዊቷ እየሩሳሌም የጽድቅ አክሊልን የደፉ የልቦለድ አለም ሰዎች የሚኖሩባት የምናብ አለም ኢትዮጵያ፡፡ ለአንድ የመሠረተ ልማት ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ሲጣል በኢቴቪ የሚነገረው በአሃዝ የተደገፈ መረጃ እጅግ አስቂኝ ነው፡፡ "በነዚህ አጭር አመታት ውስጥ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለዚህን ያህል ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል፤ ይህን ያህል የውጭ ምንዛሪ አገሪቱ ታገኛለች፣ ምርቱ ለገበያ ሲቀርብ እጥረቱ በመቶ ፐርሰንት ይቀረፋል . . ." በኢቴቪዋ ኢትዮጵያ የ"ድህነት ታሪክ ይሆናል" መፈክር ይስተጋባል፡፡ በቅርቡ ሪፖርተር ጋዜጣ እንደ ዘገበው ለአመታት የተወራለት የጊቤ ግድብ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ፈሰሰበት ዛሬ ግን አስደንጋጭ ለሆነ ችግር ተዳርጓል፡፡ በኢቴቪ ነጋሪት የተጎሰመለት የግልገል ጊቤ አንድ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ በደለል የመዘጋት አደጋ ከፊቱ ተደቅኗል፡፡ ላለፉት ሁለት ዓመታት ከዕፅዋት (ከተክሎች) ነዳጅ ለማምረት ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ተረክበው ወደ ስራ ከገቡ ሃያ ከሚሆኑ ድርጅቶች ሥራቸውን ለማከናወን የሚውተረተሩት ስድስት ብቻ ናቸው፡፡

የኢቴቪ ኢትዮጵያ በበአላት ሰሞን ጥቂት ሀብታሞች በቤታቸው የሚቆርጡት ጮማና የሚጎነጩት ውስኪ በገሀዱ ኢትዮጵያ ለሚኖሩት ከድህነት የተነሳ ‹‹ለዶሮ ቅርጫ›› ለተዳረጉት ዜጎቿ በኢቴቪ ማዕድ ይቀርባል፡፡ ከኢቴቪ ፋይል እየተመረጠች የምትቀርበው የኢቴቪ ኢትዮጵያ ሁልጊዜ ማዕድዋ ሙሉ ነው፡፡ እነማ ይሆኑ የታደሏት? ለመሆኑ የኢቲቪዋ ኢትዮጵያ ነዋሪዎች ስንት ይሆኑ? 80 ሚሊዮን ህዝብ ወይስ 80 የሚሆኑ የዘሙ ሰዎች?

## የ‹ebs›ዋ ኢትዮጵያ

የ‹ebs›ዋ ኢትዮጵያ እንኳንስ በምድር በሰማይም አቻ የሚገኝላት አይደለችም፡፡ የቡድን ሃያ እና የቡድን ስምንት አገሮች እንኳን እግሯ ስር አይደርሱም፡፡ እንደተስፋይቱ ምድር ማርና ወተት ብቻ የሚፈልቅባት ሳይሆን ቅቤና ጮማ የሚዘንብባት በከበሩ ማዕድናት ተንቆጠቆጠች ‹‹ወይዘሪት ኢትዮጵያ›› ነች፡፡ በጆርዳና ኩቺና በሚዘጋጅ እጅግ ውድና ጣት በሚያስቆረጥሙ ምግቦች በጥጋብ የምንሽሞነሞንባት በባህር ማዶ እውቅ አርቲስቶች ዳንኪራ የምንረግጥባት ከጥጋባችን የተነሳ የቁንጣን ማስወገጃ ህክምና የተደራጀባት የኢቢኤስዋ ኢትዮጵያ፡፡ ይህች ኢትዮጵያ ለእኛ የቅዠት አለም ዩቶፒያ ናት፡፡

## ልጆቻችንና የነገዋ ኢትዮጵያ

ታሪክ የትውልድ ቅብብሎሽ ነው፡፡ የትውልድ ክፍተት (Generation Gap) እንዳይፈጠር ታሪክ በሰንሰለት መሰናሰል ይኖርበታል፡፡ ዛሬ ትናንት በሆነ ቁጥር በታሪክ ይዘከራል፡፡ ዛሬ ከትናንት ይሻላል አልን ነገ ደግሞ ከዛሬ መሻል አለበት፡፡ ከዛሬ የተሻለ ነገን ለትውልድ የማውረስ ሀላፊነቱ ዛሬን ከትናንት የወረስን ዜጎች ነው፡፡

ዛሬ በአገራችን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ተነስተን ስለ ነገዋ ኢትዮጵያ ስንተነብይ ብሩህ ተስፋ ሳይሆን ድቅድቅ ጨለማ ነው የሚታየን፡፡ ዘመነ ኢህአዴግ እያፈራ ያለው ትውልድ ምን ያህል በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ነው? በኢትዮጵያዊነቱ ኩራት እንዲሰማው የተደረገለት ነገር ምን አለ? ጥያቄው ለአቶ መለስና ለሚዘውሩት መንግስታቸው ነው፡፡ ተጠያቂዎቹም የሥርዓቱ አቀንቃኞች ናቸው፡፡

"ድንጋይ መወርወርና አማርኛ ቋንቋ መናገር ክልክል ነው" እየተባለ ማስጠንቀቂያ ተፅፎ በሚለጥፍበት ት/ቤት ከየተማረ ትውልድ የነገዋን ኢትዮጵያ ህልውና መጠበቁ በሰውኛ አስተሳሰብ አዳጋች ቢሆንም ለፈጣሪ ግን የሚሳነው የለም፡፡ ሀይሌ ገ/ስላሴን ከመሰለ ጀግና አትሌት፣ በአለም ዙሪያ ሮጦ ባሸነፈበት አደባባይ የአገሩ ባንዲራ ከፍ ብሎ ሲውለበለብ ኢትዮጵያዊነት ስሜቱ ከውስጡ ገንፍሎ የደስታ ሲቃ ከሚያነባው ኢትዮጵያዊ አብራክ የተከፈሉ ልጆቹ ለአማርኛ ቋንቋና ኢትዮጵያዊያን ባህል የማያተኩሩ ከሆኑ የእነ አቶ መለስና የጋሽ ጃግሬዎቻቸው ልጆች ለምዕራቡ ዓለምና ለእነ ቻይና ባህልና ወግ ከተንበረከኩ፤ እንዲሁም የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርበኛና የሆሊውድ አክተሮች አድናቂ ሆነው ካደጉ፣ የእኔ ቢጤዎች ልጆች ወይም በማንቼስተርና በአርሴናል እግር ኳስ ክለቦችና ተጨዋቾቻቸው ፍቅር ተለክፈው ጨርቃቸውን ጥለው ካበዱ በጫት፣ በሲጋራ፣ በሀሺሽና በመጠጥ ሱስ ተጠምደው ከጀዘቡ፤ ሥራን ንቀው የምዕራባዊያንን ኑሮ ከናፈቁ፤ የዝሙትና የጭፈራ ቤቶች ሰለባ ከሆኑ ዜጎች የነገዋን ኢትዮጵያ ህልውና አደጋ ላይ መሆኑን ከወዲሁ ልንገነዘናው ይገባል፡፡

**ፈጣሪ ልቦና ይስጠን!**

# ይችን ሀገር ለመታደግ ...

ከ ገፅ 5 የዞረ....

1. በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ "ተለጣፊ" ተብለው የሚጠሩት፡፡ እውነትም እነዚህን ፓርቲዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢህአዴግ በአምሳሉ ጠፍጥፎ የሠራቸው ሲሆኑ ሲዳከሙ ገንዘብ እየደጎመ እንዲያገግሙ ያደርጋል፡፡ ስብሰባ ሲጠሩ አዳራሽ ከመፍቀድ ጀምሮ ወጭውን ሸፍኖ አዳራሹ ባዶ እንዳይሆንና እንዳይጋለጡ አባላቱን በማስገባት ያደምቅላቸዋል፡፡ ይህ ስራው ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ምስክር ይሆነዋል፡፡

2. በዘልማድ "ተቃዋሚዎች" እየተባሉ የሚጠሩት፡፡ እነዚህ ይነስም ይብዛ ተበታትነውም ቢሆን ኢህአዴግን በሰላማዊ መንገድ ለመፎካከር የሚጣጣሩ ናቸው፡፡ በመዳፈራቸውም በየማግሥቱ ይደበደባሉ፤ ይታሰራሉ፤ ከሥራ ይባረራሉ፤ ይሰደዳሉ፤

3. ኛዎቹ "የተቃዋሚ ተቃዋሚዎች" የሚባሉት፡፡ እነዚህ አደገኞችና የጭቃ ውስጥ እሾሆች ናቸው፡፡ እንደ ብዙዎች ትንተና ከሆነ እነዚህ በአምስተኛ ረድፍ የተሰለፉ ለእውነተኛ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጠንቆች ናቸው፡፡ አይሰሩም፤ አያሰሩም፡፡ የጎን ውጋቶች ናቸው፡፡ ዋና ተልእኳቸውም ኢህአዴግን ሳይሆን ተፎካካሪዎችን መፎካከር ነው፡፡ በዚህ ተግባራቸው ኢህአዴግ ሊያጠፋቸው አይፈልግም፡፡ ያሻቸውን ቢሉት ከምንም አይቆጥራቸውም፡፡ ግፋ ቢል ጥቂት አምባሳደሮችን ጠርተው መግለጫ ማውጣት ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣሉ ብሎ ኢህአዴግ አይሰጋም፡፡

እነዚህ በአምስተኛ ረድፍ የተቀመጡ የፓርቲ መሪዎች ሌላም ጎልተው የሚታወቁበት ባህሪ አላቸው፡፡ ይኸውም ምርጫ በመጣ ቁጥር ጥምረት፣ ቅንጅት፣ ሕብረት . . . ለመፍጠር ግንባር ቀደም ተዋናዮች ናቸው፡፡ ከምርጫው በኋላ ደግሞ አፍርሶ ለመውጣት የመጀመሪያዎች ናቸው፡፡ ይህንን ሁሉ ድራማ በዚህ 20 ዓመት ውስጥ ሲተውኑ ሕዝብ ይታዘበናል አይሉም፡፡ ዐይኖቻቸውን በጨው የታጠቡ ናቸው፡፡ እኛን ቢገርመንም እነሱን አይገርማቸውም፡፡

እንግዲህ ከሞላ ጎደል በኔ እይታ የፓርቲዎቹ ዓይነትና አሰላለፍ የጠቀስኳቸውን ይመስላሉ? ህዝቡስ ምን ይላል? እንዴትስ ያያቸዋል? ምሁራንስ ምን ትላላችሁ? የኢትዮጵያ ህዝብ እንባና ሰቆቃ ያከተም ዘንድ የየድርሻችሁን አንድ በሉ፤ መላ ዘይዱ፡፡ በተለይ የምሁሩ ዝምታ ያብቃ፤ በምን አገባኝም የምትኖሩት ኢትዮጵያ ስትኖር ነው፡፡ ምንም ይሁን ምን ያለ ምሁራን ቀጥታ ተሳትፎ በዚች ሀገር ላይ መሠረታዊ ለውጥ ሊመጣ አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ የምሁራን ዝምታ ኢህአዴግን እንደፈለገ እንዲፈነጭ አስችሎታል፡፡ የሕግ ሰዎች ድምጣቸው ጠፍቷል፡፡ ድምፃቸው ባለመሰማቱም የፍትህ ሥርዓቱ አፈርድሜ እየበላ ነው፡፡ የሐሰት ክስ፣ የሐሰት ምስክር፣ የሐሰት ውንጀላ ሕጋዊነት እየተላበሱ ናቸው፡፡ በዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ህይወት ሥርዓት ቀውስ እየተፈጠረ ነው፡፡ እምነት እየኮሰመነ ነው፡፡ ምሁራን ይችን ሀገር ለመታደግ ጊዜው አሁን ነው፡፡ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በብሔር መከፋፈል ያብቃ፡፡

ቸር እንሰንብት!!

# አጣብቂኝ ውስጥ የገባው መምህራን ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ ሊያደርግ ነው

በብዙ ውዝግብ ውስጥ ያለው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር አካል የሆነው የአዲስ አበባ መምህራን ማኅበር በመጭው ቅዳሜ ግንቦት 18 ቀን 2004 ዓ.ም ጠቅላላ ጉባኤውን ሊያደርግ መሆኑ ተጠቆመ፡፡

ማኅበሩ በየ4 ዓመቱ ጠቅላላ ጉባኤ በአዲስ አበባ የሚገኙ የመንግስትና የህዝብ ት/ቤቶች መሰረታዊ መምህራን ማኅበር ሊቃነ መናብርትና የአስሩ ክፍለ ከተሞች የመምህርን ማኅበር ስራ አስፈፃሚዎች መሆናቸው ታውቋል፡፡ እነኚህ የጉባዔው አባላትም የፊታችን ቅዳሜ አዳዲስ የአዲስ አበባ መምህራን ማኅበር ስራ አስፈፃሚዎችንና ኦዲትና ኢንስፔክሽን ይመርጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በተለይ አሁን በስልጣን ላይ ካሉት የአዲስ አበባ ማኅበር አመራሮች መካከል ፕሬዘዳንቱ አቶ ይግዛው ብዙአየሁ በጡረታ ምክንያት እና በደንቡ መሰረት ለ12 ዓመት በማገልገላቸው እንደማይወዳደሩ ተጠቁሟል፡፡ ሌሎቹ አመራሮች ግን በዛው እንዲቀጥሉ የኢህአዴግ ፍላጐት በመሆኑ በየክፍለ ከተማው የቅስቀሳ ስራ እየሰሩ እና ተቃውሞ ያላቸውን መምህራንንም እያስፈራሩ መሆኑን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

ይደረጋል ተብሎ በሚጠበቀው ጉባዔው ባለፈው በ "እርከን ማሻሻያ" ጥያቄ ከመንግስት በተሰጠው ምላሽ ቅሬታ በማሰማታቸው የተባረሩ መምህራን ጉዳይ በሰፊው ይነሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ሌላው አሁን በስልጣን ላይ ያለው የአዲስ አበባም ሆነ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር አመራሮች የመምህራንን መብትና ክብር ያስደፈሩ በመሆናቸው እና ከራሳቸው ውጭ የማኅበሩን አባላት ጥቅም ማስጠበቅ ባለመቻላቸው ዳግም ሊመረጡ እንደማይገባ አንዳንድ መምህራን ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ መምህራን ማኅበር በጉዳዩ ላይ አስተያየቱን እንዲሰጠን ጠይቀነዋል፡፡ የማኅበሩ ፕሬዘዳንት ለጊዜው ባለመኖራቸው ማግኘት ባንችልም ም/ፕሬዝዳንቱ መምህር መክብብ በለጠ በበኩላቸው እየተደረገ ያለ ቅስቀሳ አለመኖሩንና ጉዳዩም በየክፍለ ከተሞቹ የሚከናወን መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ሌላው የተባረሩ መምህራን ሌላ የግል ት/ቤት እንኳ እንዳይሰሩ ስማቸው ለየት/ቤቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ መበተኑን በተመለከተ አንስተንላቸው "በዚህ በኩል የደረሰን መረጃ የለም፡፡ በጉዳዩ ላይ እየተነጋገርንበት ነው" ብለዋል፡፡

# ለንደን ኦሎምፒክ ላይ የሚሳተፉ የማራቶን አትሌቶች ዝርዝር ይፋ ሆነ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለ30ኛው የለንደን ኦሎምፒክ ሀገሪቱን ወክለው የሚወዳደሩ ኢትዮጵያውያን የማራቶን አትሌቶችን ስም ዝርዝር ይፋ አደረገ፡፡

ፌዴሬሽኑ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም. በብሔራዊ ሆቴል ባደረገው የፕሬስ ኮንፈረንስ ላይ እ.ኤ.አ. በ2012 ዓ.ም በማራቶን የዓመቱን ምርጥ ሰዓት ያስመዘገቡ ናቸው በማለት ይፋ ያደረገ ሲሆን የሌሎች የርቀት ውድድር ተሳታፊዎች ስም ዝርዝርም እስከ ሰኔ 28 ቀን 2004 ዓ.ም ማጣሪያ ከተደረገ በኋላ ይፋ እንደሚደረግ አስታውቋል፡፡

የዓመቱን ፈጣን ሰዓት ያስመዘገቡ እና በጥሩ አቋም ላይ ያሉ የማራቶን ተወዳዳሪዎች መካከል ከወንዶች አትሌት አየለ አብሽሮ፣ አትሌት ጌቱ ፈለቀ እና አትሌት ዲኖ ሰፈር የተመረጡ ሲሆን አትሌት ማርቆስ ገነቴ እና አትሌት ታደሰ ቶላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠባባቂ ሆነው መመረጣቸው ተገልፃዕል፡፡

ከሴት ተወዳዳሪዎች መካከል አትሌት ቲኪ ገላና፣ አትሌት አሰለፈች መርጋ እና አትሌት ማሬ ዲባባ የተመረጡ ሲሆን አትሌት ብዙነሽ በቀለ እና አትሌት ትርፌ ፀጋዬ 1ኛ እና 2ኛ ተጠባባቂ ሆነው ተመርጠዋል፡፡

በሌሎች ውድድሮች ላይ የሚሳተፉ አትሌቶችንም በተመለከተ የራሳቸውን ፈጣን ሰዓት እንዲያሻሽሉና እንዲያስመዘግቡ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ እንዲሳተፉ ፌዴሬሽኑ ማመቻቸቱን አስታውቋል፡፡

ፌዴሬሽኑ አያይዞም ከአትሌት አሰለፈች ጋር በተያያዘ ራሷን ከውድድሩ አግልላለች የተባለው የተሳሳተ መሆኑንና ይህንንም አትሌቷ የተወራው ውሸት እንደሆነ በመግለፅ ጉዳዩ የሀገር ጉዳይ ስለሆነ ይህን ማድረግ እንደማትችል በፕሬስ ኮንፈረሱ ላይ ተገኝታ አረጋግጣለች፡፡ ከእሷ ጋር በተያያዘ በተወራው ወሬ ማዘኗንም በመግለፅ ፡፡ ሌላው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ አይሳተፍም ተብሎ የሚወራው የተሳሳተ መሆኑንና ከህክምናው መልስ ልምምድ እየሰራ መሆኑም ተገልፃዕል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከጤና አኳያ በልምምድ ላይ ያሉት አትሌቶች በጥሩ ጤንነት እንደሚገኙ በመግለፅ ነገር ግን ለሀገሪቱ ጥሩ ውጤት ያመጣሉ ተብለው የሚጠበቁት አትሌት ኢብራሂም ጀይላን፣ አትሌት ውዴ አያሌው፣ አትሌት እመቤት አንተነህ፣ አትሌት መሰለች መልካሙ፣ አትሌት ደረሰ መኮንን፣ እና አትሌት ቃልኪዳን ገዛኸኝ በህመም ላይ መሆናቸውንና የፌዴሬሽኑንም የብሔራዊ ህክምና ኮሚቴ ክትትል እያደረገላቸው መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ እነኚህም አትሌቶች ከጤና አኳያ እስካሁን የአጠቃላይ ልምምድ አለማድረጋቸው የተገለፀ ሲሆን አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ ከህክምና መልስ ልምምድ እየሰራች ቢሆንም የማጣሪያ ፈጣን ሰዓት ማሟያ ላይ ግን ፌዴሬሽኑ ስጋት እንዳለው ገልፃዕል፡፡

በአጠቃላይ ፌዴሬሽኑ ከሐምሌ 20 እስከ ነሐሴ 6 ቀን 2004 ዓ.ም. ለሚደረገው 30ኛው የለንደን ኦሎምፒክ ውድድር በጥሩ ዝግጅት ላይ መሆኑን በመግለፅ ከሰኔ 19-24 ቀን 2004 ዓ.ም ቤኒን በሚካሄደው የአፍሪካ አትሌትክስ ሻምፒዮና ላይ እና ከሐምሌ 3-8 ቀን 2004 ዓ.ም ለሚደረገው የዓለም ወጣቶች ሻምፒዮና ላይ ሀገሪቱን በመወከል ለሚደረገው ውድድር በዕቅዱ መሠረት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አስታውቋል፡፡

በመግለጫውም የፌዴሬሽኑ ቴክኒካል ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ ዱቤ ጅሎ፣ የቴክኒካል ቡድን መሪ ዶ/ር ይልማ በርታ፣ አሰልጣኝ መላኩ እና ሁሴንን ጨምሮ የሚመለከታቸው የፌዴሬሽኑ አካላት በአንድ ላይ በመሆን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ ከጋዜጠኞችም በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

# አቶ መለስ በገጠማቸው ተቃውሞ አንገታቸውን ደፉ

- ጋዜጠኛ አበበ ገላው አቶ መለስ ላይ ተቃውሞ ሲያቀርብ የሚያሳየው የዩቲውብ
- የቪዲዮ ምስል ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይታይ ተደርጓል የአዲስ አበባ ነዋሪዎች
- ስለጉዳዩ የደረሰኝ መረጃ የለም ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ
- እንዲህ አይነት ነገር ያጋጥማል አቶ በረከት ስምኦን

ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአሜሪካን አገር በገጠማቸው ድንገተኛ ተቃውሞ ከፍተኛ ድንጋጤ እንደፈጠረባቸውና አንገታቸውን መድፋታቸውን የተለያዩ ድረገፆች ዘገቡ፡፡ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ስለጉዳዩ የደረሳቸው መረጃ እንደሌለ ሲናገሩ፤ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ በረከት ስምኦን፣ በአቶ መለስ ላይ የተፈፀመውን ክስተት እውነተኝነት ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ አረጋግጠዋል፡፡

የተለያዩ ድረገፆችና ማህበራዊ ሚዲያዎች በምስል በማስደገፍ ካሰራጪቸው መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ፕሬዝደንት ኦባማ በአሜሪካን በካምፕ ዴቪድ ሬገን ማዕከል ባዘጋጁት በምግብ ዋስትና ላይ የሚመክረው የቡድን ስምንት ዓለም አቀፍ ስብሰባ ላይ ተናጋሪ ከነበሩት አራት መሪዎች መካከል አቶ መለስ አንዱ ነበሩ፡፡ ሦስቱ መሪዎች መልዕክታቸውን በአግባቡ ያስተላለፉ ሲሆን አቶ መለስ ተራ ደርሶአቸው ንግግር ሲጀምሩ ያልተጠበቀና አስደንጋጭ የተቃውሞ ድምጽ ሲቀርብባቸው በፊታቸው ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ ታይቷል፡፡

በስብሰባው አዳራሽ ፊት ለፊት የተቃውሞና የድጋፍ ሰልፍ ታይቷል፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን አቶ መለስ በዚያ ስብሰባ ላይ መገኘታቸውን በማውገዝ የተቃውሞ ሠልፍ ያደረጉ ሲሆን ጥቂት ደጋፊዎቻቸውም ለድጋፍ ሰልፍ ወጥተው እንደነበር ዘገባዎቹ ያሳያሉ፡፡ ይህን ሰልፍ አልፈው ወደ አዳራሹ የገቡት አቶ መለስ፤ የዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች ማህበር አባል የሆነው ጋዜጠኛ አበበ ጠ/ሚሩ የጀመሩትን ንግግር አቋርጦ ተቃውሞውን በድንገት አሰምቷል፡፡ ጋዜጠኛ አበበ ገላው ከአዳራሽ ከወጣ በኋላ ለጋዜጠኞች በሰጠው ማብራሪያ እንደገለፀው "ወደ አዳራሹ ከመግባታችን በፊት ገ/ተንሳኤ ተስፋዬ በርሄ የተባለ የአቶ መለስ ጠባቂ ወደ እኔ ቀርቦ ‹ሀበሻ ነህ እንዴ?› ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ምን አገባህ? አልኩት ‹አይ ኢትዮጵያዊ መስለህኝ ነው› አለኝ፡፡ አይደለሁም አልኩት፡፡ ኢትዮጵያዊ የምሆነው በአገሬ ውስጥ በነፃነት መኖር ስችል ነው አልኩት፡፡ ‹ሄደህ ስላላአላየህ ነው እንጂ አገሪቱ ጥሩ ደረጃ ላይ ደርሳለች፡፡ እናንተ እዚህ ሆናችሁ ዝም ብላችሁ ትጮሃላችሁ› አለኝ፡፡ አንተ የመጣኸው ጌታህን ልትጠብቅ ነው፡፡ እኔ የመጣሁት ደግሞ እውነት ልናገር ነው አንገናኝም ብዬው ጥዬው ሄድኩኝ" ብሎአል፡፡

ጋዜጠኛ አበበ ገላው ቀጥሎ ሲናገርም "አቶ መለስ መናገር ሲጀምሩ እንድናገር እድሉን ባላገኝም ያገኘሁትን ዕድል በመጠቀም አቶ መለስን አጋልጫአለሁ›› ብሏል፡፡ ጋዜጠኛ አበበ ገላው በመጀመሪያ የአቶ መለስን ስም ጠርቶ ሶስት ጊዜ ‹‹...አምባገነን ናቸው፡፡›› ካለ በኋላ እስክንድር ነጋና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ በማለት ጠይቋል፡፡ ቀጥሎም መለስ ነፍሰ ገዳይ ናቸው የሚል ወቀሳውን አቅርቧል፡፡ ያለ ነፃነት የምግብ ዋስትና የሚል ይዘት ያለው አቋሙንም በአዳራሹ አስተጋብቷል፡፡‹‹ ነፃነት! ነፃነት! ነፃነት!›› በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰምቷል፡፡

የጋዜጠኛ አበበ ገላውን ንግግር ፕሬዝዳንት ኦባማና የአሜሪካን ከፍተኛ ባለሥልጣናት እንዲሁም የተቀሩት የቡድን ስምንት ሀገራት መሪዎችና ተሰብሳቢዎች በጠቅላላ በትኩረት ተከታትለውታል፡፡ ‹‹ለእኔ ትልቅ ቀን ነው፡፡ የአቶ መለስን ውሸት ያጋለጥኩበት ነው፡፡ ከእንዲህ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አቶ መለስን እርቃናቸውን ማስቀረት አለብን፡፡ በእርግጥ እርቃናቸውን የቀሩ ሰው ናቸው፡፡›› ብሎአል፡፡

ጋዜጠኛ አበበ ገላው ተቃውሞውን ከገለፀ በኋላ የነበረውን ሁኔታ ሲያብራራ "ንግግሬን እንደጨረስኩ የአሜሪካን ሴኪውሪቲ ሰዎች ፖሊሶችን ጠሩ፡፡ አራት ፖሊሶች መጥተው ወደ አንድ ጥግ አሲዘው ጠየቁኝ፡፡ ‹ምንድነው ያልከው?› አሉኝ፡፡ ምንም አላልኩም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈፀመውን በደል ነው ያጋላጥኩት አልኳቸው፡፡ መንጃ ፍቃዴን ተቀብለው ተመለከቱ፡፡ ከፈለጋችሁ እሰሩኝ አልኳቸው፡፡ ‹አይ አናስርህም› አሉኝ፡፡ እንደያውም አንዱ ፖሊስ ‹እኔ ኢትዮጵያ ሄጄ ነበር፡፡ ምን እንደሚሰራ አውቃለሁ፡፡ የተናገርከው ነጥብ አለው› በማለት ጀርባዬን መታ መታ አድርጐኛል፡፡" ሲል ተደምጧል፡፡ በመቀጠልም "ከስብሰባው እንደወጣሁ የአቶ መለስ አጃቢ ‹ጠብቅ እንገልሃለን› ብሎኛል፡፡ ይህንኑ ለፖሊሱ ነግሬዋለሁ፡፡›› በማለት ተናግሯል፡፡

ከአርብ ለሊት ጀምሮ ለፍኖተ ነፃነት የደረሱ መረጃዎች እንዳመለከቱት ጋዜጠኛ አበበ ገላው አቶ መለስ ላይ ተቃውሞ ሲያቀርብ የሚያሳየው የዩቲውብ የቪዲዮ ምስል ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይታይ ተደርጓል፡፡

በካምዴቪድ ስለተፈጠረው ሁኔታ እንዲያስረዱ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ የጠየቀቻቸው የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ስለ ጉዳዩ የደረሳቸው ምንም አይነት መረጃ እንደሌ ገልፀዋል፡፡

ፍኖተ ነፃነት በመቀጠል ስለክስተቱ እንዲያብራሩ የጠየቀቻቸው የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ በረከት ስምኦን፣ በአቶ መለስ ላይ የተፈፀመውን ክስተት አምነው፣ ‹‹እንዲህ አይነት አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ›› ካሉ በኋላ መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት እንዳልሰጠው ተናግረዋል፡፡ ክስተቱን የሚያሳየው የዩቲውብ መስመር እንዳይታይ ያደረገው እገዳ እንዳልነበረም ገልፀዋል፡፡

# መምህራን በደህንነት ክትትል ሥር እየዋሉ ናቸው

መ/ር ይመር እንግዳ

በቅርቡ በአዲስ አበባና በተለያዩ የክልል ከተሞች መምህራን እስከ ሥራ ማቆም አድማ የዘለቀ ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ ሞክረው ነበር፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ የተነሳ መምህራን በመንግስት ጥርስ ተነክሶባቸዋል፡፡ ለዚህም በፓርላማ ብቸኛው ተቃዋሚ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ ስለ መ/ራን ወቅታዊ ሁኔታ ለጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጥያቄ አቅርበውላቸው ነበር፡፡ ጠ/ሚንስትሩ ገና የመ/ራን ስም ሲጠራ ሁለት እጃቸውን እያወራጩና ከመቀመጫቸው ቁጭ ብድግ እያሉ ነበር መልስ ያልሆነ መልስ ይሰጡ የነበሩት፡፡ "ብቃት የሌላቸው" በማለት ከሳቸው የማይጠበቅ እንደወረደ ሀሳብ በፓርላማው ፊት ተናገሩ፡፡ ወደፊት እንዴት መ/ራንን እንደሚያባርሩም ሴራቸውን ይፋ አደረጉ፡፡ እንዴት ነው ነገሩ? መምህር ማለት አገር ነው፤ መ/ር ተማሪ ነው፤ ተማሪ ወላጅ ነው፤ ወላጅ ደግሞ ህዝብ ነው፤ ህዝብ ደግሞ አገር ነው፡፡ ከአገር ጋር ጠብ መፍጠር ታዲያ የጤና ነው?

መምህራን ምንም እንኳን የነተበ ሸሚዝና የተንሻፈፈ ጫማ ቢያደርጉም የሞራል ልዕልናም ሆነ በዕውቀት ምጡቅነት ኢህአዴግ ካሰማራቸው ካድሬዎችና ከቱባ ባለስልጣኖችና ከላይ እየወረዱ የሚወድቁ ቃላትን እንደ ጥሬ በመልቀም ከሚያስተጋቡት በ99.9% ይበልጣሉ፡፡

ወደ መሪ ርዕሳችን ስንመለስ "ለምንስ ሙብታችሁን ጠየቃችሁ" በማለት በየት/ቤቱ ያሉ መምህራንን በሦስት በመከፈል አንድነታቸውን ለመሸርሸርና ህልውናቸውን ለማጥፋት ብዛት እንጂ ጥራት የሌላቸውን ደህንነቶች ከተመደበባቸው ሰነባብተዋል፡፡ ከላይ የጠቀስኩት ለመ/ራን የተሰጡ ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ጠንሳሽ (master mind)፣ በዚህ ምድብ የሚገኙ መ/ራን በአደገኛነት የተፈረጁና የስም ዝርዝራቸው፣ የተንቀሳቃሽ ስልክ ቁጥራቸውና የመኖሪያ አካባቢያቸው ተመዝግቦ ለበላይ አመራሮች ለክ/ከተማው ት/ት ጽ/ቤቶች፣ ለፀጥታ ኃላፊዎችና ለየወረዳው የት/ት ሹማምንት የተላለፉ ናቸው፡፡ ብዛታቸውም አምስት፣ ስድስት አንዳንዴም እስከ አሥር ይደርሳሉ፡፡ (እንደ የት/ቤቱ ጥበትና ስፋት ይወሰናል፡፡)

እነዚህ መ/ራን ከአካባቢው የመጡ የፖሊስ አዛዦች፣ ከክ/ከተማው የመጡ የት/ት ባለሙያዎች፣ ከወረዳ የመጡ የት/ት ባለሙያዎችና በት/ቤቱ አስተዳደር ፊት እያንዳንዳቸው በተናጠል ቢሮ እየተጠሩ "ከአሁን በኋላ በዚህ ት/ቤት ውስጥ አንዲት ኮሽታ ብትሰማ ከእናንተ ራስ አንወርድም፤ ሌሎች ጓደኞቻችሁ ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ጠይቀዋል፤ ፈርመዋል፤ እናንተም ይቅርታ ጠይቃችሁ ፈርሙና ወደ ሥራችሁ ተመለሱ" የሚል ማስጠንቀቂያና ዛቻ ቢናገሯቸውም ሁሉም መ/ራን መልሳቸው አንድ ነው "የጠየቅነው ሙብታችንን ስለሆነ አሁንም አቋማችን ያው ነው፡፡ የፈለጋችሁትን እርምጃ መውሰድ ትችላላችሁ አንፈርምም" በማለት በአቋማቸው ፀንተው ወጥተዋል፡፡ "ጓደኞቻችሁ ይቅርታ ጠይቀው ፈርመው ሥራ ጀምረዋል" የሚለው አባባል ፍፁም ከእውነት የራቀ ነው፡፡ ለመበታተንና አቋማቸውን ለመሸርሸር የተጠቀሙበት ስልት ነው፡፡ እንግዲህ "እነዚህ መ/ራን ናቸው አድማውን የመሩት" ብለው ስለሚያስቡ ለእያንዳንዳቸው ደህንነት ተመድቦባቸው ከግቢ ወጥተው ከማን ጋር እንደሚገናኙ፣ ከት/ቤት ወጥተው ሌላ የሚሰሩት ሥራ አላቸው ወይስ የላቸውም? እንዴት የስራ ማቆም አድማ ሊያደርጉ ቻሉ? የሚሉትን ሁኔታዎች በመሰብሰብ ላይ መሆናቸውን ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ የተለያዩ ፅጉረ ልውጦች በሻይ ሰዓትና በምሣ ሰዓት ከመ/ራን መዝናኛ ክበብ ተጠቃሚ በመምሰል መረጃ ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ እንዲሁም በት/ቤቶች አቅራቢያ በሚገኙ ካፌዎችና ሬስቶራንቶች የመ/ራን የምሳ መመገቢያ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ቀድመው ተጠቃሚ በመምሰል ተሰግስገው ይጠባበቃሉ፡፡ ታዲያ መ/ሩ ቀድሞ ስለሚያውቃቸው ሁሉን ነገር ዝግ ያደረጉባቸዋል፤ የሚጠቀሙትን ቃል እዚህ ላይ መጥቀስ አልፈልግም፡፡ በነገራችን ላይ መምህራንን የሚጠቁሙና በሃሰት የሚወነጅሉ ጥቂት አጐብዳጅ መ/ራን እንዳሉ መግለፅ እወዳለሁ፡፡ የሚይዙት የክ/ጊዜ መጠን አነስተኛ ሆኖ ስራቸው መረጃ ማነፍነፍ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ መ/ራን "አስጠቂ፣ የበቀቀን፣ እና የባንዳ" በሚሉ ስያሜዎች ይታወቃሉ፡፡

በምድብ አንድ (ጠንሣሽ) የሚገኝ የአንድ መ/ርን ገጠመኝ ልጥቀስና ወደ ቀጣዩ ምድብ እገባለሁ፡፡ መ/ር ያረጋል (ስሙ የተቀየረ) እንዲህ ይላል ‹‹የማታ ክ/ጊዜ (extension class) የመጨረሻውን ክ/ጊዜ ጨርሼ ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ላይ ወደ መኖሪያ ቤቴ እየተራመድኩ ቀጭን ኮረኮንቻማ መንገድ አልፌ ነው ቤቴ የምገባው፤ አካባቢው ፀጥ ብሏል፡፡ ኮረኮንቹን እንደ አጋመስኩ ሁለት ማንነታቸውን በውል ለመለየት ያልቻልኳቸው ወጣቶች አስቆሙኝና ‹መ/ር ያረጋል ነህ አይደል?› አሉኝ፤ አዎ አልኳቸው ‹ለምን አርፈህ ሥራህን አትሠራም?› አሉኝ፡፡ እኔም ምንም እንዳላጠፋሁ ገለፅኩላቸው ‹እኛ ሙሉ መረጃ አለን፤ ደግሞ ትኩራራለህ እንዴ?› በማለት ሁለቱም አንድ አንድ ጊዜ መሃል አናቴን በኩርኩም ገጭተውኝ እየተጣደፉ ከአካባቢው ተሰወሩ፡፡ እኔም አካባቢየን ቃኘሁ፤ ማንም የለም፤ ውርደቴን ማንም አላየም ነበርና አናቴን እያሻሸሁ ቤቴ ገብቼ ተኛሁ፡፡ ከዚያች ቀን ጀምሮ ቤቴ የምገባው ከሰፈር ጓደኞቼ ጋር አሊያም በመንገድ ሰው መኖሩን እያስተዋልኩ ነው፡፡ እስከመቼ እንደዚህ አይነት ኑሮ እንደምኖር የሚውቀው መድኋኒዓለም ብቻ ነው፡፡ ሙብቴን በመጠየቄ፣ ዳቦ በመጠየቄ መንገድ ላይ አስቁመው ብርጭቆ እንደሰበረ ህፃን በኩርኩም ገጩኝ፡፡ ፍርዱን ለፈጣሪ" በማለት ይናገራል፡፡

2. ሁለተኞቹ "አነሣሽ" ይባላሉ፡፡ በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉ መምህራን ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ጥቁር መዝገብ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ቢሮም ተጠርተው አልቀረቡም፡፡ ማስጠንቀቂያም አልተሰጣቸውም፤ ነገር ግን በት/ቤቱ አስተዳደር በአይነ ቁራኛ እለት እለት በረቀቀ ስልት ይቃኛሉ፡፡ አንዳንዴም "ሥራ እንዴት ነው? አይዞአችሁ" በማለት ለማቅረብ ቢሞክሩም፣ "አነሣሾቹ" የሚባሉት ፊት አይሰጧቸውም፡፡

3. "ተከታይ" የሚባሉት ሶስተኞቹ ናቸዉ፡፡ ይኸኛው ምድብ ብዙም ትኩረት አይሰጠውም፡፡ ነገር ግን እንደ ሁለተኛው ምድብ ሳይሆን ለዘብ ያለ ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡ ብዙም አይደለም፤ ግን ሙሉ በሙሉ እምነት አይጠልባቸውም፡፡

ሌላው በአንድ ት/ቤት (ስሙን አልጠቅስም መረጃው በእጄ ይገኛል) ያደረግነው ዳሰሳ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ለመፈተን የምትፈልጉ መ/ራን ተመዝገቡ በተባለው መሠረት ከተመዘገቡት ውስጥ በአድማው የተሣተፈ መምህር አንድም አልተመረጠም፡፡ ያልተሣተፉት ግን ተመርጠዋል፡፡ "በምን መስፈርት ነው እኛ ያልተመረጥነው?" የሚል ጥያቄ ሲጠይቁ "አፈጻጸም አታሟሉም" የሚል መልስ ነው የተሰጣቸው በማለት የስፖርት መ/ር የሆኑት መ/ር ሲሳይ (ስሙ የተቀየረ) ይናገራሉ፡፡ እውነቱን ለመናገር ግን ሙብታቸውን የጠየቁት መ/ራን ብቃት ያላቸው፣ ታታሪዎችና ቅዳሜና እሁድ ሳይቀር ተማሪዎቻቸውን እየጠሩ የማጠናከሪያ ት/ት የሚሠጡ ነበሩ፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል "እውነትን ስቀሏት"፤ "ከፀሐይ በታች ያየሁት ክፉ ነገር አለ÷ እርሱም ከገዢ የሚወጣ ስህተት ነው" እንዳለው ጠቢቡ ሰለሞን (መክ10÷5)፡፡

በመጨረሻም ደህንነቶች ሆይ ለህሊናችሁ እንጂ ለሆዳችሁ አትገዙ፡፡ እነዚህ እናንተ የምታሳድዷቸው መ/ራን ዳቦ ነው የጠየቁት፡፡ መንግስት እንገልብጥ አላሉም፡፡ ቁመው ሲጮሁ ውለው ኩርምት ብለው የሚወድቁ የዚህች ደሃ አገር አለኝታዎች ናቸውና አገራዊ ግዴታችሁን ተወጡ፡፡ ለአገር ደህንነት አደጋ የሚሆኑ ሠርጎ ገቦችን ተከታተሉ እንጂ ስንት የሚሰራ ሥራ እያለ ስለምንስ የአገሪቱን ሀብት በከንቱ ታባክናላችሁ? ለአለቆቻችሁም ንገሯቸው፤ ከኃይል ይልቅ ጥበብ ትበልጣለችና እንዲሁም ጉድጓድን የሚምስ ይወድቅበታልና፤ አበቃሁ፡፡

# ከስካይ ባስ ሰለባዎች ...

ከ ገፅ 8 የዞረ....

- መንግስትና የሚመለከታቸው ባለድርሻ የሚባሉ አካላት ምን ምርመራ በትራንስፖርቱ ላይ አድርገው ምን ውጤት አመጡ?
- በወቅቱ የአደጋውንስ መጠን መቀነስ አይቻልም ነበር ወይ? (ለምሳሌ እሳት አቀጣጣይ ቁሶችን በሕዝብ ማጓጓዣ አለመጫን፣ ከሆነም ደግሞ በድንገት የሚነሳን እሳት በአስተማማኝ ለማጥፋት የሚያስችል ሁኔታና ብቃት ስለመኖሩ ማረጋገጥን የመሳሰሉ እርምጃዎች)
- ከአደጋውስ በኋላ የተገኘውን አስከሬን አያያዝ እና የቀብር አፈፃፀም የአንድን ዜጋ ሰብአዊና ሕጋዊ ክብር የጠበቀ ነበር ወይ? ወይስ ታይታን የተላበሰ? መላው የተጎጂ ቤተሰቦችስ በቀብሩ ላይ እንዲገኙ ተፈልጎ ነበር ወይ?
- በአደጋው ወገኖቻቸው የሞቱባቸው ቤተሰቦች ያለ ጡዋሪ እና ቀባሪ የቀሩ ወላጆች፣ ያለ አሳዳጊና ረዳት የተበተኑ ቤተሰቦች ስለመኖር ያለመኖራቸው ተገቢው ድጋፍ ስለመደረግ ያለመደረጉ የጠየቀ ነበር ወይ?
- ከአደጋው የተረፉ፣ ህክምናና የመንፈስ መረጋጋት እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች ያስታወሰ ነበር ወይ? ሌላው ቀርቶ በገንዘባቸው ታክመው ቢያንስ የተወሰነው ወጪ ለቀጣይ ህክምና ተመላሽ እንዲደረግላቸው የመንግስት ተቋም ከሆነ ሆስፒታል ደረሰኝ ያቀረቡ የአካል ጉዳተኞች፣ በጉዳት አድራሹም ይሁን በቀጠረው የኢንሹራንስ ኩባንያ እንደምንድነው እየተስተናገዱ ያሉት? ቢያንስ መስተንግዶው የሰውን ልጅ ሰብአዊ ክብርና ዋጋ ያገናዘበ ነው ወይ? ድርጊቱስ ህግ ባለበት አገር ይሆናል ተብሎ የሚጠበቅ ነውን? ገና አልጋ ያልለቀቀና በቅጡ ያላገገም እሳት የበላው ጉዳተኛ ወጥቶ ከኩባንያው ወይስ ከኢንሹራንሱ ግብግብ የሚገጥመው? ወገኖቼ ዛሬ ዛሬ ብዞዎቻችን ቁጭትና ፀፀት የሚሰማን በራሳችን ላይ ብቻ ሲደርስ ቢሆንም እስካሁን የሰማችሁትን የተገነዘባችሁት እንደሰው ለሐዘኔታ በቂ ይሆናል ብለን ስለምንገምት፣ ፍርዱን ለህሊናችሁ እንተወዋለን፡፡
- በአጠቃላይ ሰሚውና ተመልካቹ ሕብረተሰብ ከሂደቱ ምን ይማራል? በሚለው ጥያቄ ላይ ከሙያና ከሞራ አኳያ ብንነጋገርበት አግባብ ነው፤ በሚል የተጎጂ ቤተሰቦች አስተባባሪ ኮሚቴ ይህንን አጭር ፓናል አዘጋጅተናል" በማለት ጥያቄዎችን ይዘረዝራሉ፡፡

ከአደጋው የተረፉ አራት ግለሰቦች በስብሰባው ላይ ምስክርነት ሰጥተዋል፡፡ እነሱም አቶ አገኘሁ የተባሉ የህግ ባለሞያ እንዳሉት "የተመደበልን መኪና ፒያሳ ስንደርስ ስለተበላሸ ተለዋጭ መጥቶ ነው ጉዞ የጀመርነው፡፡ መኪናው እጅግ ይፈጥን ነበር፡፡ ፍጥነት እንዲቀንስ ተነግሮት ነበር፡፡ የመኪናው በሮች ሁለት ብቻ በመሆናቸው ለአደጋው መባባስ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ አደጋው ሲደርስ የታጠቅነውን ቀበቶ መፍታት ባለመቻሌ ከወገቤ በላይ ልብሴ ተቃጥሎ ካለቀ በኋላ ቀበቶው ተቃጥሎ እስኪበጠስ ለመቃጠል ተገድጄአለሁ፡፡ የተረፍነው ከኋላ የተቀመጥን ጥቂት ሰዎች ነን፡፡ የካቲት 12 ሆስፒታል 71 ቀን ተኝቼ ታክሜአለሁ፡፡ 3 ጊዜ ቀዶ ጥገና ተደርጐልኛል፡፡ የስካይ ባስ ሰዎች የመጡት ከወር በኋላ ነው፡፡ ኢንሹራንስ የታከምክበትን ማስረጃ ተመልክቶ ከአንድ ሺ ብር በላይ ብንከፍል መንግስት ይቆጣናል ብሎ ከልክሎናል፡፡ ከ30 ሺ ብር በላይ የወጣበትን ህክምና እንዴት አንድ ሺ ብር ብቻ ይባላል፡፡ የታከምኩት መንግስት ሆስፒታል ውስጥ ነው፡፡ የተቃጠልነው ሳያንሰን በውሸት መቃጠል የለብንም" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሌላው ከአደጋው የተረፉት መሠረት መንግስቴ የተባሉ ወጣት በበኩላቸው "3 ኪ.ሜ እንደ ተጓዝን የመጀመሪያው መኪና ተበላሸ፡፡ የሁለተኛው መኪና ሹፌር ከተኛበት ተቀስቅሶ መምጣቱን ሰምተናል፡፡ ምናልባትም ሲገለበጥ ተኝቶ እየነዳ ሊሆንም ይችላል፡፡ መኪናው ሲገለበጥ የፍንዳታ ድምጽ ሰምቼአለሁ፡፡ መኪናው ወይ ሲሊንደር ጭኗል ወይም ሌላ አደጋ ገጥሞታል፡፡ የአውቶቢሱ አሠራር ወጥ በመሆኑ ከአደጋ በኋላ ሰዎች ራሳቸውን እንዳያድኑ አስተዋጽኦ ያደርጋል" ብለዋል፡፡

በስብሰባው ላይ የተገኙ የአደጋው ሰለባ ቤተሰቦች በእያንዳንዱ ሰው ንግግር መካከል መሪር ለቅሶ ሲያለቅሱ የቆዩ ሲሆን አዳራሽ ገብተን ዝግጅቱ እስከተጠናቀቀበት ሰዓት ድረስ ለቅሷቸውን ያላቋረጡ አረጋውያን ነበሩ፡፡ በአደጋው ውስጥ የአሜሪካን፣ የእንግሊዝ፣ የአውስትራሊያ፣ የእስራኤልና፣ የሱዳን ዜጐች ከመኖራቸውም በላይ ዶክተሮች፣ መሐንዲሶች፣ ኢንጂነሮች፣ የሒሳብ ባለሞያዎች፣ የኮንፒውተር ባለሞያዎች እንዲሁም የአገሪቱ መሪ መሆን የሚችሉ ወጣት ምሁራን እንደነበሩበት በስብሰባው በፀፀት ሲነገር ነበር፡፡

ፓናል ውይይቱ ሰፊ ነጥቦችን የዳሰሰ፤ በርካታ ጥያቄዎችን የጫረ ቢሆንም ሁሉንም በዚህ ጽሁፍ ማካተት አይቻልም፡፡ ከፓናል ውይይቱ በመነሳት ከዚህ ቀደም በአገራችን ካየነው ብሔራዊ ሀዘን አንፃር ለእነዚህ ሰዎች ብሔራዊ ሐዘን ለምን አልታወጀላቸውም? ብሔራዊ አዋጅ እንዲታወጅ መስፈርቱ ምንድነው? አደጋው ለምን የመንግስት ሚዲያ ሽፋን ተከለከለ? ወይስ በአጋጣሚ የተከሰተ ይሆን? በፓናል ውይይቱ ላይ እንዲገኙ የተጠሩት ምርመራውን የያዙት አካላት ለምን ቀሩ? ለተፈጠረው አደጋ የስካይ ባስ አ/ማ ኃላፊነቱን መውሰድ ነበረበት? መውሰድ ከነበረበት ለምን ኃላፊነቱን አልወሰደም? መውሰድ ካልነበረበት ማነው መውሰድ ያለበት? የሚሉትን ጥያቄዎች ለማንሳት ተገደናል፡፡ የአደጋው ቤተሰቦች በተደጋጋሚ እንደሚሉት "ከአደጋው ጀርባ ማነው ያለው? የኢትዮጵያዊነት መስፈርቱስ ምንድነው?" የሚሉ ሐሳቦችና ጥያቄዎች ተንሸራሸረዋል፡፡

የሰለባው ቤተሰብ ተወካይ በተደጋጋሚ እንደሚገልጹት የተሳፋሪዎች ቁጥር በውል ባይታወቅም ሹፌሩና ረዳቶቹን ሳይጨምር 47 ሰዎችን ጭኖ ነበር፡፡ የሟቾች ቁጥጥር በትክክል ባይታወቅም ምናልባትም 42 ሰዎች ሳይሆን እንደማይቀሩ ይናገራሉ፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩን ያጣራው የመንግሥት አካል ስለተሳፋሪዎችም፣ ስለሟቾችም ትክክለኛ ቁጥር የሰጠው ይፋዊ ቁጥር ባለመኖሩ ነው፡፡

አደጋው ከተፈፀመ ነገ 4 ወሩ ነው፡፡ ምርመራውን ያጣራው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ወረጃርሶ ወረዳ ፖሊስ ነው፡፡ የምርመራ ውጤቱን ለምን መግለጽ አልፈለገም? ምርመራውን ካላጠናቀቀ ለአደጋው ሰለባ ቤተሰቦች ለማሳወቅ ምን ቸገረው? ምርመራውን ለማጣራት እውነት አራት ወር ሊፈጅ ይችል ይሆን? የሟቾች ቤተሰቦች በሌሉበት ቀብሩ ለምን ተፈፀመ? ኢንሹራንስ በህይወት የተረፉትን ለምን መታደግ አቃተው? በስብሰባው ላይ በተደጋጋሚ ሲነገር የሰማነው የባህልና የሥነ ምግባርም ችግር ነው፡፡ የአደጋው ሰለባ ቤተሰቦች አደጋውን ፈልገው አለመጡትም በየቦታው ሲሄዱ ለምን ተገቢውን መስተንግዶ ተነፈጋቹ? ከአደጋው ጀርባ ምን አለ? ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት መልስ ቢሰጡበት መልካም ነው፡፡

# በአዳራሽ ባለቤቶችና በኢህአዴግ የተፈጠረ የሰይጣን ቀለበት መሰበር አለበት

‹‹የሰይጣን ቀለበት›› ያልነው ፈረንጆች ‹‹Vicious Circle›› የሚሉትን ነው፡፡ የሰይጣን ቀለበት የሚፈጠረው ነገሮች እርስበራሳቸው ቁልፍልፍ ብለው ሊፈታ የሚገባ ችግር ሳይፈታ ሲቀር ነው፡፡

አንድ አጭርና ቀላል ምሳሌ እንውሰድ፡፡ ወጣት ማሞ (የፈጠራ ስም ነው) ቤትና ቋሚ አድራሻ የለውም፡፡ ሥራ ለመያዝ የሚያስችል መጠነኛ እውቀት አለው፡፡ ሆኖም በሆነ ምክንያት ህይወቱ ተቃውሶ የጎዳና ተዳዳሪ ሆኗል፡፡ አቶ ማሞ አንድ ቀን ለሥራ ፈላጊዎች የወጣ የሥራ ማስታወቂያ ያያል፡፡ እድሉን ቢያገኝ ሥራው ሊሠራው የሚችለው አይነት ነው፡፡ እንደማንኛውም ሰው ያመለክታል፡፡ ለጥያቄ ሲቀርብ ቋሚ አድራሻ ተጠየቀ፡፡ ‹‹የጎዳና ተዳዳሪ ነኝ ቤት የለኝም፤ ቋሚ አደራሻ የለኝም›› አላቸው፡፡ ቋሚ አድራሻ ከሌለህ ጉዳይህን ልንመለከትልህ አንችልም ይሉታል፡፡ ስለዚህ ሥራ ለመያዝ አልቻለም፡፡ የሰይጣን ቀለበቱ የሚመጣው እዚህ ላይ ነው፡፡ ቋሚ አድራሻ ከሌለው ሥራ ማግኘት አይችልም፡፡ ሥራ ካልያዘ ደግሞ ደመወዝ አግኝቶ ቤት ለመከራየትና ቋሚ አድራሻ ማግኘት አይችልም፡፡

የሰይጣን ቀለበቱ አንድ ቦታ ላይ መሰበር አለበት፡፡ ይኸኛው የሰይጣን ቀለበት የሚሰበረው በሁለት መንገድ ብቻ ነው፡፡ አንዱ መንገድ ቀጣሪው አካል ደፍሮ ወጣት ማሞን ያለ ቋሚ አድራሻ መቅጠር ሲችል ነው፡፡ ሌላው መንገድ ደግሞ ቤት አከራዮች ገንዘብ ሳይከፈላቸው ለወጣት ማሞን ቤት ማከራየት ሲችሉ ነው፡፡ አንዱ ችግር ቢፈታ ሌላውም ችግር ይፈታል፡፡ አንዱ ችግር ካልተፈታ ሌላውም ችግር አይፈታም፡፡ አንድነት አዳራሽ መከራየትን አስመልክቶ አሁን የገጠመው ይህን የመሰለ የሰይጣን ቀለበት ነው፡፡

የአዳራሽ ባለቤቶችና የኢህአዴግ ባለሥልጣናት እንዴት ነው የሰይጣን ቀለበቱን እየፈጠሩ ያሉት? የችግሩን አመጣጥ እንከታተል፡፡ ለምሳሌ አንድነት በአዲስ አበባ አንድ ሕዝባዊ ስብሰባ ለማካሄድ ያቅዳል፡፡ እቅዱን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ስብሰባውን ከምታካሂዱበት ቦታ አዳራሹን ለመከራየታችሁ የጽሁፍ ማስረጃ ካላመጣችሁ እውቅና አንሰጥም ይላል፡፡ የአዳራሹ አከራዮች ደግሞ ከከተማ አስተዳደሩ የእውቅና ማስረጃ (እነሱ ‹ፈቃድ› ይሉታል) ካላመጣችሁ አናከራይም ይላሉ፡፡ እዚህ ላይ ነው ሰይጣናዊ ቀለበቱ የሚፈጠረው፡፡ እውቅና ለማግኘት የስብሰባ ቦታ ማግኘት ማስፈለጉ፤ የስብሰባውን ቦታ ለማግኘት ደግሞ የአስተዳደሩ እውቅና ማግኘት ማስፈለጉ፡፡ ኢህአዴግ አንድነት ከህዝብ ጋር እንዳይገናኝ የፈጠረው የመሰናክል ስልት ይህን ይመስላል፡፡ የዚህ ዓይነት አካሄድ ዙሪያውን ቅንነት የጎደለው አካሄድ ነው፡፡ ይሄ የሰይጣን ቀለበት አንድ ቦታ ላይ መሰበር አለበት፡፡ እንዴት እንደሚሰበር ከመነጋገራችን በፊት ግን ስለ ሁለቱ ወገኖች ማለትም ስለ ባለአዳራሾቹና ስለኢህአዴግ ስትራተጂ ትንሽ ማለት ይኖርብናል፡፡

ከአዳራሽ አከራዮች እንጀምር፡፡ በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን፡፡ አንደኛው ወገን በኢኮኖሚው የአገልግሎት ዘርፍ ተሰማርተው፤ ፈቃድ አውጥተው ለህዝብ አገልግሎት ለመስጠት እና ትርፍ ለማግኘት የተዘጋጁ የግል ድርጅቶች (ባለሆቴሎች) ናቸው፡፡ ግዴታዎች እንዳሉባቸው ሁሉ መብቶችም አሏቸው፡፡ ከግዴታዎቻቸው አንዱ ተገቢውን ግብር ለመንግሥት መክፈልና ለህዝብ አገልግሎት መስጠት ሲሆን ከመብቶቻቸው አንዱ ደግሞ ከንግድ እንቅስቃሴያቸው ትርፍ አግኝቶ መጠቀም ነው፡፡

ሁለተኛው ወገን የመንግሥት ወይም የሕዝብ አዳራሾች ናቸው፡፡ እነዚህ አዳራሾች የሕዝብ እንደመሆናቸው ሕዝባዊ ስብሰባን አስመልክቶ በነፃ አሊያም በመጠነኛ ክፍያ አገልግሎት መስጠት ያለባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ የግልም ሆነ የሕዝብ አዳራሽ አስተዳዳሪዎች አንድ የጋራ ችግር አለባቸው፡፡ ሁለቱም አዳራሾቻቸውን ለተቃዋሚዎች ለማከራየት ይፈራሉ፡፡ የፍርሀታቸው ምንጭ ደግሞ ኢህአዴግ ነው፡፡ በቀል፤ውቀሳ፤ ቁጣ ይፈራሉ፡፡

የግል አዳራሽ ባለቤቶች አዳራሾችን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ብናከራይ የተለያየ ችግር ይደርስብናል፣ ድርጅቶቻችን ለጥቃት ይጋለጣሉ ብለው ይፈራሉ፡፡ ማነው የሚያስፈራራችሁ? ተብለው ሲጠየቁ በግልጽ አይናገሩም፡፡ አንዳንዶቹ "ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች ስልክ እየደወሉ ያስፈራሩናል ወይም ቢሮ ድረስ እየመጡ ከየትኛው የመንግሥት አካል እንደመጡ ገልፀውም ሆነ ሳይገልፁ አዳራሽ ለተቃዋሚዎች እንዳናከራይ ያስጠነቅቁናል" ይላሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ባለአዳራሾች አዳራሽ ካከራዩና የኪራይ ገንዘብ ከተቀበሉ በኋላ ‹‹ከላይ የሚመጣውን ጫና አልቻልነውም እና ገንዘባችሁን ውሰዱ›› ይላሉ፡፡ የሕዝብ አዳራሾችን በተመለከተ በተለይ ራሳችው ትንንሽ ካድሬዎች ከሆኑ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ካላቸው ጥላቻ ወይም ለበላይ ካድሬ አለቆቻቸው ታማኝነታቸውን ለማሳየት ካላቸው ፍላጎት፤ ራሳቸ አምባገነን ከለካይ ይሆናሉ፡፡

ወደ ኢህአዴግ ስንመጣ ራሱን « አውራ ፓርቲ» ነኝ ብሎ አርባ አመት ለመግዛት ቆርጦ እንደተነሳ በተለያዩ መንገዶች አሳውቆናል፡፡ ለይስሙላ የመድበለ ፓርቲ ስርአት አውጆ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተጠናክረው እንዳይወጡ ያልተጣለባቸው መሰናክል የለም፡፡ ከመሰናክሎቹ አንዱ እውነተኛ ተቃዋሚዎች ወደ ሕዝቡ እንዳይገቡና ከሕዝቡ ጋር እንዳይወያዩ የመሰብሰቢያ አዳራሽም ሆነ አደባባይ መከልከል ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ክልከላው በይፋ አይደለም፤ በስውር ነው፡፡ ቅን ያልሆነ አካል ሥራዎችን በስውር መሥራት ይውዳል፡፡

ሕዝባዊ ስብሰባን ማሳወቅን በተመለከተ ሕጉ ምን ይላል? ለምሳሌ በአዲስ አበባ በአንድ ፓርቲ ሕዝባዊ ስብሰባ ለማድረግ ሲያቅድ የስብሰባውን አላማ፣ የሚካሄድበትን ቦታና ሌሎች ተፈላጊ መረጃዎችን አክሎ እውቅና እንዲሰጠውና ትብብር እንዲደረግለት በአዲስ አበባ መስተዳድር ለሚመለከተው ክፍል በጽሁፍ ያመለክታል፡፡ ማመልከቻው የደረሰው ክፍል በህጉ መሠረት በ12ሰዓት ውስጥ እውቅና ይሰጣል፡፡ ስብሰባው በተባለው ቀንና ቦታ እንዳይካሄድ የሚያደርግ በቂ ምክንያት ካለው በሌላ ጊዜና ቦታ እንዲካሄድ በጽሁፍ ይገልፃል፡፡ ይህ እንግዲህ ህጋዊው አካሄዱ ነው፡፡ አለመታደል ሆኖ ግን ይህ ህጋዊ ሂደት ብዙውን ጊዜ ያለ ጥናት፣ ያለ ክርክር፣ ያለጭቅጭቅ፤ ያለንትርክ በተግባር ተከብሮ አያውቅም፡፡ የኢህአዴግ ሹማምንት ህጉን እንዳሻቸው ይሸሩታል፡፡ በ12 ሰዓት ውስጥ መልስ መስጠት ሲገባቸው ስብሰባና ሌላም ምክንያት እየተሰጠ ቀናትን ያሳልፋሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጭራሹን መልስ አይሰጡም፡፡ ከዚያም አልፈው ሕግ የማይፈቅድላቸውን ግዴታ ይጥላሉ፡፡ ለምሳሌ "ተቃዋሚዎች አዳራሹን ከአከራያቸው ድርጅት ለማከራየቱ የጽሁፍ ማስረጃ አምጡ" ብለው ይጠይቃሉ፡፡ ይህ ህገወጥ ጥያቄ ነው፡፡ አመልካቹ በማመልከቻው ስብሰባውን የሚያካሂድበትን ቀንና ቦታ በትክክል ከገለፀ ከአከራዩ በጽሁፍ የተሰጠ ማስረጃ አቅርብ የሚል ህግ የለም፡፡ ነገር ግን በኢህአዴግ ሥርዓት ብዙውን ጊዜ ሥራዎች የሚሰሩት በአንባገነንነትና በጉልበት፤ በሕግ ሳይሆን በባለሥልጣን ፍላጎት ስለሆነ ይህን ጥያቄ ካላሟላችሁ እውቅና አንሰጥም ይባላል፡፡ ይህ ጠያቂ የሌለበት የሚመስል የማንአለብኝነት አሰራር ነው፡፡ የሰይጣናዊው ቀለበት መፈጠር ምክንያትም ይሄው ነው፡፡

ፈሪና አስፈራሪ ባሉበት ሥርዓት ህጎችና መብቶች ምስቅልቅላቸው ይወጣል፡፡ የግል አዳራሽ ባለቤቶች ንብረታቸውን አከራይተው የመጠቀም ህገ መንግሥታዊ መብታቸውን ማስከበር ሲገባቸው በመፍራታቸውም ድርብ ተጠቂ ይሆናሉ፡፡ መብታቸው ይጣሳል፤ ገቢም ያጣሉ፡፡ አስፈራሪዎችም እኩይ የማስፈራራት ድርጊታቸው የልብ ልብ እየሰጣቸው ህግን መጣስና የዜጎችን መብት መግፈፍንም የዘወትር ድርጊታቸው ያደርጉታል፡፡ ይህ አደገኛ ሁኔታ መቀጠል የለበትም፡፡

ባለአዳራሾችና የኢህአዴግ ባለስልጣናት የፈጠሩት የሰይጣን ቀለበት ቀደም ሲል እንደተገለፀው አንድ ቦታ ላይ በአስቸኳይ መሰበር አለበት፡፡ መሰበር ያለበትም በሁለት መንገዶች ነው፡፡ አንደኛውና የመጀመሪያው የፍርድ ቤት ሂደት ነው፡፡ የግል ባለአዳራሽ ድርጅቶች የንግድ ፈቃድ ሲያወጡ ለሕዝብ አገልግሎት ለመስጠት ቃል ገብተው ነው፡፡ ያለበቂ ምክንያት አገልግሎት አንሰጥም ካሉ ቃላቸውን አልጠበቁም፤ ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡ ስለዚህ በህግ መጠየቅ አለባቸው፡፡ ማስፈራሪያም ሆነ ማስጠንቀቂያ ከደረሳቸው ያስፈራራቸውንም ሆነ ያስጠነቀቃቸውን ግለሰብ ወይም አካል በስምና በአድራሻ የመግለጽ ግዴታ አለባቸው፡፡ አለበለዚያ ሾላ በድፍኑ ማስጠንቀቂያ ወይም ማስፈራሪያ ደርሶኛል በማለት ብቻ ከተጠያቂነት ሊያመልጡ አይችሉም፡፡ ፍርድ ቤት ቀርበው መጠየቅ አለባቸው፡፡

የመንግሥትና የሕዝብ አዳራሾች የተሰሩትም ሆነ የሚተዳደሩት በሕዝብ ሀብት ነው፡፡ ስርዓት ባለው ሁኔታ ለህዝብ አገልግሎት መዋል አለባቸው፡፡ የሕዝብ ሀብት የሆኑ አዳራሾችን ለሕዝብ ጥቅም እንዲውሉ አንፈቅድም የሚሉ ኃላፊዎች ውሳኔው የራሳቸው ከሆነ ሕግ ፊት ቀርበው መጠየቅ አለባቸው፡፡ ክልከላው ከበላይ አካል ከሆነ ያንን የበላይ አካል ማንነት የመግለጽ ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህን ካላደረጉ የችግሩ ምክንያት እነሱ ራሳቸው በመሆናቸው በህግ እንዲጠየቁ መደረግ አለበት፡፡

የኢህአዴግ ባለስልጣናትም ሠላማዊ ሠልፍና ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በመተመለከተ ሕግ የሚጥሱ ከሆነ መጠየቅ አለባቸው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሠላማዊ ሰልፍና ሕዝባዊ ስብሰባ ጥያቄዎችን በተመለከተ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሕጎች በተደጋጋሚ ይጣሳሉ፡፡

እነዚህ ከላይ የተመለከቱት የመብትና የሕግ ጥሰቶች በአግባቡ ፍርድ ቤት ቀርበው ከፍርድ ስርዓቱ በአፋጣኝ መፍትሔ መገኘት አለበት፡፡ የኢህአዴግ የፍርድ ሥርዓት ፈጣን ፍትሕ የማይሰጥ ከሆነ ሕዝብ ታፍኖ መኖር የለበትም እና የመሰብሰብና ሠላማዊ ሠልፍ የማካሄድ ህገ መንግሥታዊ መብት ያላቸው አካላትም ሆነ ሕዝቡ በአጠቃላይ በሁለተኛውና በመጨረሻው መንገድ መጠቀም ነው፡፡ ይሄውም ሥነ ሥርዓትን ጠብቆ አደባባይ መውጣት ነው፡፡ በባለ አዳራሾችና በባለሥልጣናት ሥልታዊ አካሄድ የተፈጠረው የሰይጣን ቀለበት የሚሰበረው በአንድ በኩል፣ የመሰብሰብና ሠላማዊ ሠልፍ የማካሄድ ሕገ መንግሥታዊ መብት የተሰጣቸው አካላት የተሰጣቸውን መብት በፍርድ ሥርዓቱ ማስከበር ሲችሉ ነው፡፡ ይህን ማድረግ ካልቻሉ መብታቸውን የማስከበር ህጋዊና ሠላማዊ ርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡ ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን ለማስከበር የሚከፈለውንም መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ በሌላ በኩል በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 8 መሠረት ሕዝቡ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ነውና ይህን የተፈጠረውን የሠይጣን ቀለበት በሉዓላዊ ሥልጣኑ ለመስበር በሠላማዊ መንገድ አስቸኳይ ርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

በመጨረሻም እነዚህ የሰይጣን ቀለበት ፈጣሪዎችን ሕግ ፊት ለማቅረብ በሚደረገው እንቅስቃሴ ተቃዋሚዎች ጥንካሬው ብቃቱና ዝግጅቱ እንዲሁም ጉዳዩን ከዳር ለማድረስ ቁረጠኝነቱ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በመቀጠልም የኢህአዴግ ባለስልጣናት ለህግ ተገዢ እንዲሆኑና የአዳራሽ ባለቤቶችን ማስፈራራታቸውንና ተቃዋሚዎች ከሕዝቡ ጋር ለመገናኘት በሚያደርጉት ጥረት መሰናክል የመፍጠር ድርጊታቸውን እንዲያቆሙ በዚህ ጋጣሚ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡ አፍኖ በዘላቂነት መግዛት አይቻልም!

ሕዝብን ለማፈን የተፈጠረው የሰይጣን ቀለበት በሕዝብ ሉዓላዊ ሥልጣን መሠበር አለበት!

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ
(አንድነት)

የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ

አዲስ አበባ

# የታክሲና የመንግስት ...

ከ ገፅ 3 የዞረ....

ያካተተ የታሪፍ ማስተካከያ አለመደረጉ ላይ ነው፡፡ ሾፌቹና ረዳቶቻቸው በአማካኝ በቀን ከ100 እስከ 200 ብር ያገኛሉ፡፡ የታክሲ ባለንብረቶችም እንደ መኪናቸው አይነትና አዲስነት ከ130 እስከ 300 ብር በቀን ያገኛሉ፡፡ የነዳጅ ጭማሪው ባይመለከታቸውም የመለዋወጫ መናር አማሯቸዋል፡፡ በአዲስ አበባ የሚገኙት አብዛኞቹ ሚኒባስ ታክሲዎች ያረጁ በመሆናቸው ሾፌሮቹ ቦታ እየመረጡ ለመስራት ለመስራት ይመርጣሉ፤ ሆኖም አዲሱ የዞን ስምሪት እድሉን አልሰጣቸውም፡፡ ከመገናኛ ሜክሲኮ መስመር የሚሰራው ሰለሞን በዞን ስምሪቱ ተጠቃሚ የሆነ የለም ብሎ ያምናል፡፡ "አንተ እውቀትህንና ያለህን ገንዘብ ስለምታውቅ የምትገባበትን ንግድ መወሰን ያለብህ ራስህ ነህ፡፡ ‹ሽንኩርት ልነግድ› ስትል መንግስት ‹ዘይትና ስኳር› ካልሸጥክ ብሎ አይከለክልህም፤ እኛን ግን የፈለንነው ቦታ እንዳንሰራ ተከልክለናል" የሚለው ሰለሞን በሚነዳት በተለምዶ ሀይሲ በሚል የምትጠራ አሮጌ ሚኒባስ ለመኪናዋ አቅም በማይስማሙ ቦታዎች ጭምር እንደሚመደብ ያስረዳል፡፡ በታሪፍ ምጣኔው ላይም ቅሬታ የሚያነሱ ሾፌሮች በርካታ ናቸው፡፡ " የኔ መኪና በሊትር ከአምስት ኪ/ሜ በላይ አትሄድም፤ በቀን ከአራት ቢያጆ በላይ አትነዳም" የሚለው ሌላው አስተያየት ሰጪ ገቢውን ለማስተካከል ሲል ትርፍ እንደሚጭንና መስመር እንደሚቆራርጥ ይናገራል፡፡ ሾፌሮቹ እነዚህን ድርጊቶች በመፈፀማቸው የሚመጣው ቅጣት የሚያሳስባቸው አይመስልም፡፡ "ትራፊክ ከያዘህ እንደ ምንም ብለህ በሳንቲም ትገላገለዋለህ" የሚለው አስተያየት ሰጪው ጉቦው የመጀመሪያ አማራጭ እንዳልሆነ ይናገራል፡፡ "ትርፍ ስትጭን በሌላ አቅጣጫ የሚመጡ ሹፌሮችን መስመር ላይ ትራፊክ መኖሩን ጠይቀህ ነው የምትጭ ነው" ሲል ያክላል፡፡ ሹፌሮቹ እንደሚሉት አንዳንድ ወቅት ላይ ትራፊኮች በዘመቻ ለቅጣት ይወጣሉ፡፡ በዚህ ወቅት ላይ ጉቦ ሰጥቶ ማለፍ ስለሚያስቸግር ሾፌሮቹ ርስበርስ መስመር ላይ ትራፊክ መኖሩን መረጃ ይለዋወጣሉ፡፡ "በቀን የፊት መብራት አብርቶ የሚሄድ ታክሲ ካየሁ ለረዳቴ ትርፍ ሰው ከያዘ እንዲያስተካክል እነግረዋለሁ" የሚለው ሌላው አስተያየት ሰጪ ትራፊኮች ሆነ ብለው ታክሲዎችን እንደሚያሳድዱ ይናገራል፡፡ አቶ ተሾመ ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩት ከሁለት ታክሲዎቻቸው በሚያገኙት ገቢ ነው፡፡ ‹‹ሾፌሮቹ እንደቀድሞው ጥሩ ገቢ ስለማያገኙ መኪኖቻችንን ያለረፍት ያሽራሉ›› የሚሉት አቶ ተሾመ ትርፍ ሲጫንባቸው የመኪኖቹ እድሜ እያጠረ እንደሚሄድ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ጦስም በየጊዜው ለመለዋወጫና ጥገና ከፍተኛ ወጪ እንደሚያወጡም ያስረዳሉ፡፡ የመኪኖቹ ደህንነት፣ የትራንስፖርት እጥረትና የተገልጋዩ እንግልት ብዙም የሚያሳስባቸው የማይመስሉት የታክሲ ሾፌሮች ከተሳፋሪ ጋር እንኪያ ሰላምታ እገጠሙና ከትራፊክ ፖሊሶች ጋር ድብብቆሽ እየተጫወቱ የባለቤቶቹን ገቢ በማሟላት ማታ ይዘው ስለሚወርዱት ገቢ እያሰቡ ሲዳከሩ ይውላሉ፡፡

# አማራን የማሳደዱ ሴራ እንደቀጠለ መሆኑ ተገለፀ

### የአገው ብሔረሰብም ተካቷል

በመተከል ዞን ማንቡክ (ዳንጉር) ወረዳ ለረጅም አመታት የቆዩና በተለያየ ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሄዱ የአማራና የአገው ብሔር ተወላጆች በክልሉ ካድሬዎች ለጅምላ እስራትና ካለምንም ቅድመ ሁኔታ አካባቢውን ለቀው እንዲሄዱ እየተደረገ መሆኑን ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡

በተለይም ማንቡክ (ዳንጉር) ወረዳ የአማራና የአገው ተወላጆች ለጅምላ እስራት መዳረጋቸውን ተከትሎ የወረዳው የሃይማኖት አባት ዜጎች የታሰሩበት እስር ቤት ድረስ በመሄድ "ወዶ አማራና አገው ሆኖ የተፈጠረ ሰው የለም፤ እንዲሁም በፍላጐት ጉሙዝና ሽናሻ ሆኖ የተፈጠረ የለም፡፡ ሁላችንም የእግዚአብሔር የእጅ ስራዎች ነን፤ ስለዚህ የታሰሩ ዜጎች በአስቸኳይ ይፈቱ!" እያሉ እያለቀሱ ቢለምኗቸውም ለአባ ልመና በፌዝ ምላሽ ሰጥተዋቸዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በመተከል ዞን በሚገኘ ኤዲዳ ቀበሌ ባሏ የተገደለባት የመንታ ልጆች እናት አቅም ስላልነበራቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ጥለዋቸው በመሰደዳቸው ለሚመለከታቸው አቤት ቢሉም "አገርሽ ክልል 6 ሳይሆን ክልል 3 ነው፤ ስለዚህ ወደ አገርሽ ሂጂ" የሚል ምላሽ እንደተሰጣት ተጠቅሷል፡፡

በማንቡክ (ዳንጉር) ዙሪያ አውጃቢስ በረሃ ለአንድ ኢንቬስተር እስከ ሃያ ሺህ ሄክታር ድረስ እየተሰጠ እንደሆነ የገለፁት አንድ የአካባቢው ተወላጅ "ዜጎች በአገራቸው ሰርተው እንዳይበሉ መደረጉ ኢህአዴግ ከዜጎቹ ይልቅ ለባዕዳን ትኩረት መስጠቱ ኢትዮጵያዊነታችን ትልቅ አዘቅት ውስጥ መግባቱን ያመላክታል" ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ይህንን ተከትሎ ገበሬዎች ላም፣ በሬና የተለያዩ የቤት እንስሳት እጅግ ርካሽ በሆነ ዋጋ ለመሸጥ ቢሞክሩም የሚገዛቸው ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ በተያያዘ ዜና በማንዱራ ገነተማርያም ኤሲፃ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ከጉሙዝ ማህበረሰብ ጋር አብረው በፍቅር የሚኖሩ 86 አባወራዎች ውስጥ 82 አባውራዎች ካለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲወጡ መመሪያ መተላለፉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህንን ተከትሎ የጉሙዝ ብሄረሰቦች "እኛ ከአገውና ከአማራ ጋር ለረጅም ዘመን ተስማምተንና በንግድ ልውውጥ ተግባብተን እዚህ የደረስን ሰዎች ነን፤ ለምን እንደሚያስወጡብን አልገባንም፤ እኛ አብረን መኖር እንፈልጋለን" በማለት እየገለፁ ናቸው፡፡ ይህንንም ለማጣራት ወደ ሚመለከተው የአካባቢው የመንግስት

# ማስታወቂያ

አንድነት ፓርቲውን ለማጠናከር የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም የራት ግብዣ ለግንቦት 25 ቀን ማዘጋጀቱንና ዝግጅቱ የሚካሄድበትን የሆቴሉን ስም በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ግንቦት 14 ቀን ታትሞ በሚወጣው ለማሳወቅ ቃል ገብቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በሆቴሎች የፕሮግራም መጨናነቅ ምክንያት የራት ግብዣው ቀን ለሐምሌ 28 ቀን 2004 ዓ.ም መራዘሙን ከታላቅ ይቅርታ ጋር እየገለጽን የሆቴሉን ስምና አድራሻ ከዚያ ወዲህ በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ የምናሳውቅ መሆናችንን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ



# ከአንድ ቀበሌ ወደ ሌላ ሲሄዱ ግብር እንዲከፍሉ መደረጉ ተገለፀ

በደቡብ ክልል ጋሞ ጎፋ ዞን በሚገኘው የዴምባ ጎፋ ወረዳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪዎች ከአንዱ ወደሌላው ቀበሌ ሲሄዱ ግብር እንዲከፍሉ ትእዛዝ መተላለፉ ተገለፀ፡፡

በወረዳው በሚገኙ ዘንጋ እና ካርዛ ቀበሌ ነዋሪዎችና ከብቶቻቸው ሚሻካሬ የሚባለውን ወንዝ ተሻግረው ከመጡ ግብር አስከፍሏቸው በሚል ሚያዚያ 21 ቀን 2004 ዓም በአስተዳዳሪው አቶ ገ/መድህን መጬሎ እና ምክትል አስተዳዳሪው አቶ ጌታቸው በየነ ትእዛዝ መስጠታቸውን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ኬንቾ የሚባል ቀበሌ መገዛ ከሚባል ጋር እንዲሁም ዝልጎ የሚባል ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሉቄ ከሚባል ጋር ነዋሪው ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስድ ትእዛዝ መሰጠቱ ተጠቁማል፡፡ እንደምንጮቻችን መረጃ ከሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች መንግሥት የሾመብን አስተዳዳሪዎች ማህበራዊ ህይወታችንን ሊያናጉትና እርስ በርስ ሊያጣሉን እየሞከሩ ነው ሲሉ ቅሬታቸውን ማሰማታቸው ተገልጿል፡፡

ስለ ጉዳዩ የወረዳው ዋና አስተዳዳር አቶ ገ/መድህን መጬሎ በበኩላቸው በወረዳው ባሉ ቀበሌዎች ለስራ መንቀሳቀሳቸውን ገልፀው የቀረበባቸውን አቤቱታ ግን ሐሰት ነው ሲሉ አስተባብለዋል፡፡ የወረዳው ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ዋና ሰጅን ገ/ማሪያም ዑታ በበኩላቸው በተጠቀሱት ቀበሌዎች በተባለው ዙሪያ የደረሳቸው መረጃ እንደሌለ በተለይ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡

# ወቅታዊ ውይይት

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ

"ወጣቱና የመደራጀት አስፈላጊነት"

በሚል ርዕስ በጥናት ላይ የተመሠረተ የውይይት

ርዕስ አዘጋጅቷል፡፡ የጥናቱ አቅራቢ

የኢኮኖሚ ምሁርና በፖለቲካው ዓለም የዳበረና

የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው

**አቶ ያዕቆብ ልኬ** ናቸው፡፡

የውይይት ቀን ግንቦት 19 ቀን 2004 ዓ.ም

የውይይት ቦታ በአንድነት ጽ/ቤት ግቢ (ቀበና)

የውይይት ሰዓት ከጧቱ 3 ሰዓት ጀምሮ

ሁላችሁም በአክብሮት ተጋብዛችኋል ኑ እንማር፤

እንማማር፡፡

የአንድነት ሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ

# በቦረና የእርከን ሥራ ውጤት ቅሬታ አስነሳ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ቦረና ዞን ቡሌ ሆራ /ሀገረማሪያም/ ወረዳ በተከናወነው የእርከን ሥራ ነዋሪውን ለከፍተኛ ችግር መዳረጉን የዜና ምንጮች ገለፁ፡፡ ምንጮቻችን እንደሚሉት "የእርሻ ቦታዎች፣ የለማ መሬት ለእርከን በመዋሉ ከብቶች ማሰሪያ ተቸግረናል፡፡ ዛፎች እየተቆረጡ የንብ ቀፎ ይወረወራል፡፡" ሲሉ አማረዋል፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች በምሬት እንደሚናገሩት "በዞናችን መልካም አስተዳደር የሚባል ነገር የለም፡፡ የበታች አካላት የሚፈጽሙትን ግፍና በደል አቤት የሚባልበት ቦታ የለም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ለበቆሎ ዘር 219 ብር፣ ለዳፕ ማዳበሪያ 789 ብር ለዩኒሪያ ማዳበሪያ 621 ብር በጠቅላላ 1629 ብር ከፍለን መውሰድ አልቻልንም፡፡ በግድ ካልወሰዳችሁ ብለው እያስገደዱን ነው፡፡ ከብቶቻችን እርከን ተብሎ በተከለለው እርሻ ላይ ከደረሱ 500 ብር ይቀጡናል፡፡" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ነዋሪዎቹ እንደሚሉት "በዚሁ በቡሌ ሆራ ወረዳ ቡሌ ቃኛ መኮኒሳ ማገዳ ቀ/ገ/ማ የውሃ እጥረት ተከስቷል፡፡ በቆሎ ተዘርቶ እየተበላሸ ነው፡፡ የሰጡን ዘር የተበላሸ ዘር ነው፡፡ በውሃ እጥረት አንድ ጀሪካን እስከ አምስት ብር ይሸጣል፡፡ የሙብራት እጥረት ይከሰታል፡፡ ጄኔሬተር ዝግጁ አይሆንም፡፡ በዱዳ ዳዋ ወረዳ አርቢቾ ቀ/ገ/ማ በተመሳሳይ የዘር ችግር የበቆሎ ቡቃያው እየተበላሸ ነው" ሲሉ አማረዋል፡፡

# በምዕራብ አርማጭሆ መንግስትና በነዋሪው መካከል ውጥረቱ ጨምሯል

በሰሜን ጐንደር ዞን ምዕራብ አርማጨሆ ወረዳ መንግስት አርሶ አደሮችን በማፈናቀሉ ምክንያት የተፈጠረው አለመግባባት መንግስት በመስጋቱ ነዋሪዎችን ትጥቅ የማስፈታት ሙከራ ማድረጉ በአካባቢው ውጥረት እንደፈጠረ ምንጮቻችን ጠቆሙ፡፡

መንግስት የምዕራብ አርማጨሆ አርሶ አደሮችን መሬት በማስለቀቅ በተሸነሸኑ መሬቶች ላይ እንዲያርሱ ለማድረግ በወሰደው እርምጃ ምክንያት የተፈጠረው አለመግባባት በነዋሪዎችና በመንግስት መሀከል ውጥረት ከመፍጠሩም በላይ መንግስት መሳሪያችሁን አስመዝግቡ በሚል ሰበብ የነዋሪዎችን መሳሪያ የመንጠቅ ተግባር መፈፀሙንና የሚናገሩት ምንጮቹ በዚህ ሁኔታ የሃያ ሰዎች መሳሪያ መነጠቁን ተናግረዋል፡፡

ምንጮቻችን አያይዘውም ከነዋሪዎቹ የሚነጠቀው መሬት ለሱዳን ባለሀብቶች እየተሰጠ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ አያይዘውም ‹‹ነዋሪዎች በመንግስት እርምጃ ተቃውሞ በማሳየታቸው በአካባቢው ግጭት ሊፈጠር ይችላል የሚል ስጋት አይሏል፡፡›› ብለዋል፡፡ የአካባቢውን ነዋሪዎች ያነጋገሩት ምንጮቻችን እንደገለፁት ውጥረቱ መንግስትን ስላሰጋው የአካባቢው የስልክ ግንኙነት እንዲቋረጥ ተደርጓዋል፡፡

የዝግጅት ክፍላችን ስለ አካባቢው ሁኔታ ለማጣራት የአካባቢው ባለሥልጣናት ጋር ለመደወለወ ጥረት ቢደረግም በአካባቢው የስልክ አገልግሎት በመቋረጡ ሙከራችን ሊሳካ አልቻለም፡፡